አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3586 | ቅዳሜ ነሐሴ 9 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር

## ኢትዮጵያ እየመከረች ነው

# የሀገርን እጣ ፈንታ በውይይት መድረክ

- ለምክክሩ ስኬታማነት ከተመካካሪዎች ባለፈ ሌሎች ባለድርሻ አካላትም ኃላፊነታቸውን መወጣት እንደሚጠበቅባቸው ተጠቁሟል

➔ 6




ፎቶ- ከገፀ ድር
በስምንት የአጀንዳ ርዕሰ ጉዳዮች ሲመካከሩ የቆዩት የአጀንዳ ቡድኖች መግባባት ላይ መድረስ ችለዋል

## ባህል እየሆነ የመጣው አረንጓዴ አሻራ

➔ 5



ፎቶ ከገጸ ድር
የመዲናዋ ነዋሪዎች በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ተሳትፎ ላይ

## ተስፋ አብሳሪው የቡሄ ጨዋታ

➔ 8



ፎቶ፡- ኤ አይ ቻት ጂፒቲ
የልጆች ጭፈራ እና የሙሉሙል ዳቦ ስጦታ ከቡሄ በዓል ክዋኔዎች መካከል ይጠቀሳሉ

## ፍቅር፣ ይቅርታና ተስፋ በወጣቱ ብዕር

➔ 11



ፎቶ- ከገፀ ድር
የፍቃዱ አስራት "የህላዌ ዘለሰኛ" የተሰኘው የግጥም መድብል

# የዲፕሎማሲው አዲስ አቅም

- የኮሪደር ልማቱ አዲስ አበባን ለውጭ ባለሀብቶች፣ ለዲፕሎማቶች እና ለቱሪስቶች ተመራጭ መዳረሻ እያደረጋት ነው

**በሳህሉ ብርሃኑ**

ከተሞች አሁን ላይ በዓለም አቀፍ ፖሊሲ፣ በኢኮኖሚ እና በባህል ዲፕሎማሲ ቀጥተኛ ተሳታፊ እየሆኑ ስለመምጣታቸው የዘርፉ ምሁራን ያብራራሉ። የከተሞች መዘመን፣ የደህንነት እና የጸጥታ መሻሻል እንዲሁም የዘመናዊ ኮንፈረንስ እና የትራንስፖርት ማዕከል መሆን ለሀገራት የዲፕሎማሲ ተጽዕኖ ፈጣሪነት ቀጥተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ፕሮፌሰር ሚሼል አኮንቶ ያስረዳሉ። ፕሮፌሰሩ «City Diplomacy: The Expansion of International

ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ ከገፀ ድር
በአዲስ አበባ እየተከናወኑ ያሉ ልማቶች ዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲ ማዕከልነቷን ከፍ የሚያደርጉ ናቸው




# ከህግ ማስከበር እስከ እሴት ግንባታ

**በቶለሳ መብራቴ**

ፈረንሳዊው የማህበራዊ ሳይንስ ምሁር ፕሮፌሰር ኤሚል ድርክሃይም ማህበረሰቡ የጋራ እሴቶቹን እና የሞራል ልዕልናውን ሲያጣ፣ ግለሰቦች ከሥራ ውጪ አቋራጭ መንገዶችን (እንደ ሌብነትና ማጭበርበር ያሉ ድርጊቶችን) በመከተል ህብረተሰቡን ቀውስ ውስጥ እንደሚከቱት በሰፊው ተንትነዋል።

ኤሚል ድርክሃይም እ.ኤ.አ. በ1893 “The Division of Labour in Society” በሚል ርዕስ ባሳተሙት መጽሐፋቸው የሕግ መከበር እና የጋራ ሞራል (Collective Morality) መዳከም ማህበረሰባዊ መዋዠቅን (Anomie) እንደሚያስከትል ይገልጻሉ። ማህበረሰቡ በጋራ እሴቶች እና በግልጽ የሞራል ደንቦች ካልተሳሰረ፣ ግለሰቦች ሕግን በመጣስ ሌብነትን አቋራጭ የሀብት ማግኛ መንገድ ለማድረግ ይሞክራሉ፤ ስለዚህ በማህበረሰቡ ዘንድ ጠንካራ የሞራል ተቋማት እንደሚያስፈልጉ ይመክራሉ፡፡

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

**አድራሻ** +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ



## ሙስናን መዋጋት ልማትን ማፋጠን ነው!

ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በተለያዩ ዘርፎች የተፋጠነ ልማት ላይ ትገኛለች። ከተሞች እየተለወጡ ነው፤ መንገዶችና የከተማ መሠረተ ልማቶች እየተስፋፉ ነው፤ የሕዝብ አገልግሎቶችም በቀላሉና በፍጥነት እንዲዳረሱ ጥረት እየተደረገ ነው። ይህ ውጤት ተጠናክሮ ይቀጥል ዘንድ ገቢ የመሰብሰቢያ አማራጮችን አሟጦ ከመጠቀም ባለፈ ለሙስና የሚከፍቱ በሮችን መዝጋት፣ ዘላቂ መፍትሔም ማበጀት ያስፈልጋል፡፡

በሙስና ላይ ሊወሰዱ ከሚገባቸው ተግባራት መካከል የሕግ ተጠያቂነት አንዱ ነው። በቅርቡ መንግስት ሌብነትንና ህገ ወጥነትን ለመከላከል ጠንካራ እርምጃ መውሰድ ጀምሯል፡፡ ይህ በበጎ የሚታይና ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባው ነው፡፡

ግንዛቤ ፈጠራ ድርጊቱን የመታገያ አዋጭ መንገድ ነው፡፡ ሙስናን መዋጋት የፖሊስ፣ የፍርድ ቤት ወይም የፀረ-ሙስና ተቋማት ብቻ ኃላፊነት እንዳልሆነ ሕዝቡ ሊገነዘብ ይገባል። ሙስና ሲፈጸም የሚያይ ዜጋ ዝም ማለት እንደሌለበት፣ ሕገ ወጥ ክፍያን መቀበልም ሆነ መስጠት የራሱን ሀገር መጉዳት እንደሆነ ማስገንዘብ ያስፈልጋል።

በተለይ ወጣቱ ትውልድ ሙስናን “ነገሮችን ለማፋጠን የሚያገለግል መንገድ” አድርጎ በተሳሳተ መልኩ እንዳይመለከተው ማስተማር ወሳኝ ነው። በትምህርት ቤት፣ በሥራ ቦታ፣ በሚዲያና በማኅበራዊ መድረኮች ሙስና ምን እንደሆነ፣ በሕዝብ ላይ ምን እንደሚያስከትል፣ ድርጊቱ ሲፈጸም ሲያዩ እንዴት ሪፖርት ማድረግ እንደሚቻል እና ታማኝነት ለልማት ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ማስተማር ያስፈልጋል።

ግንዛቤ ማለት ግን ሰበካ ብቻ አይደለም። ዜጋው ሙስናን እንዲቃወም ከፈለግን ተቋማት ግልጽ መሆን፣ መረጃ ለሕዝብ መድረስ፣ ቅሬታ ማቅረቢያ መንገዶች መታወቅና ሪፖርት የሚያደርግ ሰው ደህንነት መጠበቅ አለበት። የሕዝብ ገንዘብ የት እንደሚውል ማወቅ የዜጋው መብት ከሆነ፣ የሕዝብ ቁጥጥር በራሱ የፀረ-ሙስና መሣሪያ ይሆናል።

ኢትዮጵያ ዛሬ የምትገነባው ልማት የተሻለ ነገን ለማምጣት ነው። ገንዘብ በሙስና ከተበላ ልማቱ ቢኖር እንኳ ፍጥነቱ እና ውጤቱ በሚፈለገው ልክ አይሆንም። በአንጻሩ ገቢን በታማኝነት ሰብስቦ፣ በግልጽነት አቅዶ፣ በብቃት አውጥቶ እና በጥራት ወደ ልማት መቀየር ከተቻለ ዛሬ የምናየውን ለውጥ እጅግ የበለጠ ማፋጠን ይቻላል።

ስለዚህ የሙስና ትግላችን ሁለት ክንፎች ሊኖሩት ይገባል፤ አንዱ የሕግ ተጠያቂነት፣ ሌላው ግንዛቤና የታማኝነት ባህል ግንባታ። አንዱ ካለ ሌላው ከሌለ ትግሉ የተሟላ አይሆንም። ሁለቱን መተግበር ከተቻለ ግን የፀረ-ሙስና ትግሉ ከቅጣት ባለፈ ወደ ዘላቂ የልማት ኃይል ይቀየራል።

ሙስናን መዋጋት ገንዘብን ከመጠበቅ በላይ ነው፤ የሀገርን የልማት ፍጥነት መጠበቅ ነው። የሕዝብን ገቢ ከሙስና ነጻ አድርጎ በአግባቡ መጠቀም ከተቻለ፣ ዛሬ የምናየውን ልማት ነገ ወደ ከፍተኛ ብልጽግና መቀየር ይቻላል። ሙስናን መዋጋት ልማትን ማፋጠን የሚሆነውም ለዚሁ ነው፡፡

# የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## ወደ ውስጣችንም ብንመለከት

**ሳሮን ከጊዮርጊስ**

አዲስ አበባ ላይ በተለያዩ ዘርፎች በተሰሩ ስራዎች አበረታች ውጤት እየተመዘገቡ ነው፡፡ ይህም ከተማዋን ለነዋሪው ብቻም ሳይሆን ለእንግዶች ጭምር ተመራጭና ተስማሚ እንድትሆን አድርጓታል፡፡ ለዚህ ተመራጭነት ካበቋት መካከል ኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማቱን ጨምሮ ከተማዋን የማደስ ስራዎች አካል የሆነው ጽዳት ተጠቃሽ ነው፡፡

ስለ ጽዳት ስናነሳ በቤታችን፣ በደጃችን ብሎም በአካባቢያችን ከምናካሂደው የተናጠልም ሆነ የጋራ ጽዳት በተጨማሪም እንደ ከተማ በዘመቻ መልክ መከናወኑ ለተገኘው ውጤት ያለው አበርክቶ በቀላል የሚታይ አይደለም፡፡

ነገር ግን ዛሬ ለመጻፍ ያነሳሳኝ ከተማዋ ይህን ያህል ጽዱና አረንጓዴ እየሆነች ባለችበት ወቅት የስራ ከባቢያችንን ጽዳት ማድረግ ላይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች አሉ። “ቤቱን ያላየ ደጁን እንዴት ያውቀዋል” እንደሚባለው ሁሉ በአንዳንድ ተቋማት ያለው የጽዳት ጉድለት “የት ነው ያለነው?” ያሰኛል፡፡

አገልግሎት ፈልጌ ጎራ ያልኩበት አንድ ተቋም ወይም መስሪያ ቤት ምንም እንኳን ህንፃው ተገቢውን የቀለም ቅብ የተቀባ ቢሆንም የውስጥ ጽዳቱ ለተገልጋይም ሆነ ለአገልጋይ ምቾት የማይሰጥ ነው፡፡ የአገልግሎት መስጫ ክፍሎቹ ከሚያስተናግዱት የተገልጋይ ብዛት አንጻር በፍጥነት አይጸዱም፣ ቅጥር ግቢው በተለይም የውሀ መውረጃ ቱቦዎች በመዘጋታቸው ከፍተኛ ሽታ አለው፤ የተለያየ ቆሻሻም በቅጥር ግቢው ይስተዋላል፡፡

ጉዳይ ለማስጨረስ በእነዚህ ቦታዎች ስትንቀሳቀሱ ሽታው አፍንጫን የሚሰነፍጥ፣ ከመስሪያ ቤቱ ስምና ተግባር ጋር በፍጹም የማይገናኝ ነው፡፡ ከዚህ አልፎም ከተቋሙ ዋና በር በስተጀርባ (ተገልጋይ የሚገባበት) የተለያዩ የእንጨት እና የብረታ ብረት ቁርጥራጮች ከጥቅም ውጪ ሆነውና ተከማችተው እየበሰበሱና እየዛጉ ይገኛሉ፡፡

ተቋሙ (መስሪያ ቤቱ) ምንም እንኳን በኤጀንሲ አማካኝነት የተቀጠሩ የጽዳት ሰራተኞች ያሉት ቢሆንም ለአገልግሎት በሄድኩባቸው ጊዜያት ያስተዋልኩት የጽዳት ስራ ጥሩ ነው ብሎ ለመናገር አያስደፍርም፡፡

አንዳንድ አገልግሎት መስጫ ተቋማት (መስሪያ ቤቶች) በባህሪያቸው ቶሎ ቶሎ መጸዳት ያለባቸው ይመስለኛል፡፡ ነገር ግን በጽዳት ሰራተኞቹ ላይ ያስተዋልኩት የመሰልቸት ስሜት ነው፡፡ እንዲሁም እኔ ያስተዋልኩት መጸዳጃ ቤት ሴት እና ወንድ የሚጠቀምበት ሆኖ ጽዳትም ሆነ ተጠቃሚው ከተጠቀመ በኋላ የሚደፋው ውሀ የሌለበት ነው፡፡

በከተማችን ደረጃውን የጠበቀ መጸዳጃ እንደ ፆታችን እና አካል ጉዳታችን በአግባቡ ተሰርቶ በአነስተኛ ክፍያ መጠቀም በሚያስችልበት ወቅት ላይ እንገኛለን። ተቋማትም በዚህ ልክ ግቢያቸው፣ አገልግሎት መስጫ አካባቢያቸው ጽዱ እንዲሆኑ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ብዬ አስባለሁ፡፡

ምንም እንኳን እያንዳንዱ የየራሱ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚመለከታቸው አካላት የሚጠበቅባቸውን ያህል ክትትልና ድጋፍ ካላደረጉ እነዚህና መሰል ችግሮች እንዲፈጠሩ ያደርጋል የሚል ሀሳብ አለኝ።

የተቋሙ ሰራተኞች በተለያዩ ጊዜያት በተደረጉ የጽዳት ዘመቻ ተሳትፈዋል ብዬ እገምታለሁ፡፡ ይህን ተነሳሽነት በራስ ተቋማም በማድረግ ቅጥር ግቢውንም ሆነ የተለያዩ አገልግሎት መስጫ ክፍሎችን ማጽዳት ለራስም ሆነ ለተገልጋይ ክብር ነው። ስራውን ባህል ማድረግ ይገባል እላለሁ፡፡

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ**

**እየተዘጋጀች ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ ግንቦት 1985 ዓ.ም ተመሰረተች**

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ግራፊክስ ዲዛይን**
እዮብ ተፈራ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ይግለጡ ዳዴ
አብርሃም ገብሬ
ፋንታነሽ ተፈራ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ

**ዋና አዘጋጅ**
ምህረቱ ፈቃደ
Mehretu@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 34/55

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ
ቶሎሳ መብራቴ

## ከህግ... ከገጽ 1 የዞረ




ፎቶ - ከገፀ ድር
ሙስናንና ብልሹ አሠራርን የሚቃወም ትውልድ መገንባት የሁሉም ኃላፊነት ነው

ፕሮፌሰሩ እንደሚሉት ሌብነትንና ሙስናን መዋጋት የሕግ ማስከበር ተግባር ብቻ አይደለም፤ የአንድ ሀገርን የሥነ-ምግባር መሠረት፣ የማኅበረሰቡን እሴትና የትውልድን አስተሳሰብ የሚወስን የረጅም ጊዜ የለውጥ ሥራ ነው። ሌብነት እንደ አጸያፊና አስነዋሪ ተግባር፣ ታማኝነት ደግሞ እንደ ክብር በማኅበረሰብ እሴት ውስጥ ሲሰርጽ፣ ሕግን ብቻ የሚፈራ ሳይሆን በሕሊናው የሚመራ ዜጋ መገንባት ይቻላል። በዚህ ረገድ በትውልድ ሥነ-ምግባር፣ በትምህርት ሥርዓት፣ በተቋማት ጥንካሬና በሕግ የበላይነት ላይ በትኩረት የሠሩ ሀገራት ከሙስና ጋር በመታገል ብቻ ሳይወሰኑ ትውልዳቸው ሌብነትን እንዲጸየፍ ማድረግ ችለዋል።

በዚህ ረገድ ስሟ በተደጋጋሚ ከሚጠቀሰው ሀገር አንዷ ሲንጋፖር ናት። ሀገሪቷ ቀደም ሲል የሙስናና የሌብነት ችግር የተስፋፋባት እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ። ዛሬ ግን ሲንጋፖር በጠንካራ ተቋማት፣ በሕግ የበላይነት፣ በተጠያቂነትና በጥብቅ የሙስና መከላከያ አሠራር የሚጠቀስ ሀገር ሆናለች። የዜሮ ታጋሽነት (Zero Tolerance) ፖሊሲን በመንግሥትና በማኅበረሰብ መዋቅር ውስጥ በጥብቅ መተግበሯ፣ ሙስናን በሕግ ብቻ ሳይሆን በባህልና በእሴት ደረጃም ለመቃወም የሄደችበት ርቀት ለስኬቷ መሠረት ሆኗል።

ይህ የሲንጋፖር ልምድ የሚያሳየው ሙስናን መዋጋት ወንጀለኛን ከመያዝና ከመቅጣት የሚያልፍ መሆኑን ነው። በሕግ፣ በተቋማት፣ በተጠያቂነትና በሥነ-ምግባር ትምህርት ተደጋጋሚና የተቀናጀ ሥራ ሲሠራ የማኅበረሰብ እሴት ይቀየራል፤ ከዚያም ሕገ-ወጥ ጥቅምን መቀበል እንደ እድል ሳይሆን እንደ ነውር የሚቆጥር ትውልድ ይገነባል። በ2025 የ"Transparency International" የተሰኘ ተቋም Corruption perceptions Index በሚል ርዕስ ባወጣው ሪፖርት ሲንጋፖር ከ182 ሀገራት መካከል 3ኛ ደረጃን መያዟ የዚህ የረጅም ጊዜ ጥረት አንዱ መገለጫ ሲሆን በእስያና ፓሲፊክ ደግሞ 1ኛ ደረጃ ይዛለች።

ህገ-ወጥነት የአንድን ሀገር ኢኮኖሚ ከመጉዳት ባሻገር የማኅበረሰብን የሞራል መዋቅር የሚያፈርስ ጥልቅ ችግር ነው። የመንግሥት አመራሩ፣ ነጋዴው፣ ሠራተኛውና ሌሎች የማኅበረሰብ ክፍሎች ከሌላ ቦታ የመጡ ሳይሆኑ የዚሁ ማኅበረሰብ አካላትና የእሴቶቹ ነፀብራቆች ናቸው። ስለዚህ በሥራ ቦታ የሚፈጸሙ ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን በጥቂት ግለሰቦች ተጠያቂነት ብቻ ለመፍታት መሞከር ችግሩን አይፈታውም። ችግሩን ከመሠረቱ ለማስወገድ ጥልቅ የባህልና የአስተሳሰብ ሽግግር ያስፈልጋል።

በተለይም ለዘመናት ተንሰራፍተው የቆዩ አንዳንድ አጥፊ ብሂሎችና አስተሳሰቦች ለሕገ-ወጥነት መስፋፋት መንገድ ከፍተዋል። "ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል" የሚለው አስተሳሰብ በተለይ አደገኛ ነው። ይህ አባባል የሕዝብንና የሀገርን ሀብት መዝረፍን እንደ ብልህነት፣ ታማኝነትንና በንጹህ መንገድ ማገልገልን ደግሞ እንደ ሞኝነት የሚያስቆጥር የተሳሳተ ሥነ-ልቦና እንዲገነባ ያደርጋል። ስለዚህ ሌብነትን ለመዋጋት ከሕግ በፊት አስተሳሰቡን መዋጋት ያስፈልጋል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ልማት ጥናት መምህርና ተመራማሪ ፕሮፌሰር መሳይ ሙሉጌታ እንደሚገልጹት፣ ዘላቂ የባህል ለውጥ ለማምጣት የማኅበረሰቡ የመጀመሪያ ግንባታ የሚከናወንበት የቤተሰብ ሥርዓት ላይ ትኩረት ሊደረግ ይገባል። ወላጆች ለልጆቻቸው የሚያስተላልፉት የሕይወት መመሪያ በጥረት መኖርን፣ የሌላውን አለመመኘትንና በታማኝነት መኖርን መሠረት ያደረገ ሊሆን ይገባል።

ይህ ከ1ኛ ክፍል ጀምሮ የግብረ-ገብና የሥነ-ምግባር ትምህርት መስጠት መጀመሩ በእሴት ግንባታ ረገድ ያለውን ሚና ያሳያል። ልጆች ታማኝነትን፣ ፍትሃዊነትን፣ ኃላፊነትንና የሕዝብ ሀብትን መጠበቅን እንደ ክብር ሲማሩ፣ ሌብነትና ሙስና እንደ ነውር የሚቆጠሩበት የእሴት መሠረት ይገነባል። ዋናው ግብም ሕግን ብቻ የሚፈራ ትውልድ መፍጠር ሳይሆን፣ ሕግ ባይኖርም ትክክለኛውን ለመምረጥ የሚችል የሥነ-ምግባር ሕሊና ያለው ዜጋ መገንባት ነው።

የሃይማኖት ተቋማትም በዚህ የእሴት ሽግግር ውስጥ ሊኖራቸው የሚችለው ሚና ትልቅ ነው። ሃይማኖታዊ ተቋማት ሰፊ ማኅበራዊ ተፅዕኖ ስላላቸው፣ በሚሰጧቸው ትምህርቶች ውስጥ በሕገ-ወጥ መንገድ የተገኘ ሀብት መንፈሳዊም ሆነ ማኅበራዊ በረከት እንደሌለው በግልጽ ማስተማር ይገባል። ሕገ-ወጥነትን የሚያወግዙና በቅንነት የተገኘን ጥቂት ሀብት የሚያበረታቱ ትምህርቶችን በየመድረኩ በመስጠት፣ የምዕመናንን ሕሊና የታማኝነት ዘበኛ ማድረግ ይቻላል።

የኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ከሰሞኑ በሰጠው መግለጫ፣ መንግሥት የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ለማደናቀፍ፣ የሀገር ሀብት ለመመዝበር እና የዋጋ ንረትና የውጭ ምንዛሬ እጥረት እንዲባባስ ለማድረግ በተደራጀ መንገድ ሲንቀሳቀሱ በነበሩ አካላት ላይ የማያዳግም የሕግ ማስከበር እርምጃ መውሰዱን አሳውቋል።

በዚህም መሠረት ከ7 ሺህ በላይ ሕገ-ወጥ የንግድ ድርጅቶችና መጋዘኖች የታሸጉ ሲሆን፣ በሕገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርና በጥቁር ገበያ ተሳታፊ የሆኑ 169 ግለሰቦች፣ የባንክ ማጭበርበር የፈጸሙ 36 ሰዎች፣ 7 የክሪፕቶ ካረንሲ መተግበሪያዎችና ግብራቸውን የሰወሩ 38 የቤቲንግ ድርጅቶች በሕግ ቁጥጥር ሥር ውለው የባንክ ሒሳባቸው እንዲታገድ መደረጉ ተገልጿል።

በተጨማሪም በዋና ዋና የኢኮኖሚና የአገልግሎት ዘርፎች ውስጥ የተሰገሰጉ ሕገ-ወጥ ተዋናዮችን ለማጽዳት በተካሄደው ሰፊ ኦፕሬሽን ከፍተኛ የመንግሥት አመራሮችና ሌሎች ተጠርጣሪዎች ተጠያቂ መሆናቸው ተገልጿል። በኮንትሮባንድ የወርቅ ዝውውር የተሳተፉ 183 ግለሰቦች፣ በነዳጅ አየር በአየር ሽያጭ የተሳተፉ 38 አመራሮችና ከ650 በላይ ተዋናዮች፣ ጥራት የሌለው ማዳበሪያ ግዢ ጉዳይ የተሳተፉ የግብርና ሚኒስቴር ኃላፊዎች፣ ሕገ-ወጥ የኃይል ሽያጭ የፈጸሙ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አመራሮች፣ በስደትና በሰው ዝውውር ወንጀል የተሳተፉ 8 አመራሮችና 44 ደላሎች፣ እንዲሁም በገቢዎችና ጉምሩክ ዘርፍ ሐሰተኛ ደረሰኝ በማወራረድ ገቢ የሰወሩ 91 ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ሥር መዋላቸው ተገልጿል። መንግሥትም ይህንን የሕግ ማስከበር እርምጃ አጠናክሮ እንደሚቀጥል አሳውቋል።

ፕሮፌሰር መሳይ እንደሚሉት፣ መንግሥት የሁልጊዜ ተግባሩ የሆነውን ሕግ የማስከበር እርምጃ በቁርጠኝነት ማስቀጠል ይኖርበታል። የሌብነትና የሙስና ድርጊት የሀገርን ኢኮኖሚ ከማናጋቱ ባሻገር፣ ከቤተሰብ ጀምሮ በታዳጊዎችና በወጣቶች ዘንድ በአቋራጭ የመበልጸግ የተሳሳተ አስተሳሰብን በማጎልበት ሥነ-ልቦናዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አደጋ እያስከተለ ነው።

በተቋማት ውስጥ የአሠራር ግልጽነት፣ ተጠያቂነትና ዘመናዊ ዲጂታል አገልግሎት መጠናከርም ወሳኝ ነው። የሙስና ቀዳዳዎችን በቴክኖሎጂ መዝጋት፣ የሰው ንክኪን መቀነስና የግብይት ሂደቶችን መቆጣጠር ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን ይገታል።

የግሉ ዘርፍና የነጋዴው ማኅበረሰብም

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

> **ሌብነት ጥዩፍና ነውር፣ ታማኝነት ደግሞ ክብር መሆኑ በማኅበረሰቡ ባህል ውስጥ ሙሉ በሙሉ ሲሰርጽ፣ በሕግ፣ በታማኝነትና በንጹህ አገልግሎት ላይ የተገነባች ጠንካራና የተከበረች ሀገር መፍጠር ይቻላል**

# የዲፕሎማሲው... ከገጽ 1 የዞረ


ፎቶ ከገፀ ድር
በአዲስ አበባ እየተከናወኑ ያሉ ልማቶች ዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲ ማዕከልነቷን ከፍ የሚያደርጉ ናቸው

Relations in the Century of Cities» በተሰኘ ጥናታዊ ጽሑፋቸው ከተሞች የሚያካሂዱት የኮሪደር እና የመሠረተ ልማት ማሻሻያ «ሶፍት ዲፕሎማሲ» (Soft Power) በመሆን የሀገርን በጎ ገጽታ እንደሚገነባ ያመላክታሉ።

የ«Paradiplomacy: Cities and States as Global Players» ጥናታዊ ጽሑፍ ተመራማሪው ሮድሪጎ ታቫሬስ በበኩላቸው እንደሚገልጹት ጽዱ፣ ዘመናዊ እና ማራኪ የሆኑ የከተማ ኮሪደሮች፣ ፓርኮች እና የሕዝብ መዝናኛዎች የሀገርን መልካም ገጽታ ለውጭ ሀገር እንግዶች እና ዲፕሎማቶች ያሳያሉ። እንደዚሁም የከተሞች የትራንስፖርት፣ የሆቴል እና የስብሰባ አዳራሾች መዘመን ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን፣ የከፍተኛ አመራሮች ስብሰባዎችን እና የዲፕሎማሲ መድረኮችን ለማስተናገድ መንገድ ይከፍታል ይላሉ።

አዲስ አበባ ከኒውዮርክ እና ጄኔቫ ቀጥላ የአፍሪካ ሕብረት፣ የፋይናንስና የኢኮኖሚ ኮሚሽን (UNECA) እንዲሁም የበርካታ ዓለም አቀፍ ተቋማትና ኤምባሲዎች መኖሪያ በመሆን የዓለማችን ሦስተኛዋ ታላቅ የዲፕሎማሲ ማዕከል በመባል ትታወቃለች። ይህ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ገጽታዋ ከተማዋን የአፍሪካውያን መገናኛና የዲፕሎማሲ መዲና አድርጓት ቢቆይም፣ ለረዥም ዓመታት ግን ይህን ታላቅ ስሟን የሚመጥን የልማት ደረጃ ላይ ባለመኖሯ በበርካታ ጉዳዮች ስትፈተን ቆይታለች።

በጽዳት እጦት የጎደፉ ጎዳናዎች፣ የትራፊክ መጨናነቅ፣ በቂ የሕዝብ መዝናኛና የእግረኛ መንገድ አለመኖር፣ እንዲሁም ደረጃቸውን ያልጠበቁ መሠረተ ልማቶች የአዲስ አበባ መገለጫዎች ነበሩ። ከዚህ ቀደም ወደ ስብሰባ የሚመጡ መሪዎች ከስብሰባ አዳራሽ ውጭ የሚጎበኙት ማራኪ ስፍራ እምብዛም አልነበረም። በአንዳንድ በውጭ ሀገራት ዲፕሎማቶችና ተቋማት ዘንድ "አዲስ አበባ የአፍሪካ ሕብረት መቀመጫ ለመሆን አትመጥንም፣ መቀመጫው ወደ ሌላ ሀገር ሊዛወር ይገባል" የሚሉ ቅሬታዎችና ጠንካራ ትችቶች እስከመሰንዘር ደርሰውም ያውቃሉ።

አዲስ አበባን አቋርጠው የሚያልፉት ወንዞች፣ በተለይም ቀበና፣ ቦሌ እና ባንቢስ አካባቢ የሚገኙት የከተማዋ የውበት ምንጭ መሆን ሲገባቸው፣ ለዓመታት የኢንዱስትሪና የቤቶች ቆሻሻ ማከማቻ ሆነው ቆይተዋል። ወንዞቹ ዳርቻቸው ቆሻሻ የተከመረባቸው፣ ሽታቸው በአካባቢው ለማለፍ የሚፈታተንና ለበሽታ መፈልፈያነት የተጋለጡ ነበሩ። በዓለም አቀፍ ደረጃ በወንዝ ዳርቻ ልማት የሚለኩ ከተሞች አዲስ አበባን ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያስቀመጧትም፣ እነዚህን የተፈጥሮ ጸጋዎቿን ወደ "ክፍት የፍሳሽ ማስወገጃነት" ቀይራቸው በመቆየቷ ነበር።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ እንደሚገልጹት፤ አዲስ አበባ ለበርካታ ዓመታት በመሠረተ ልማት እጥረትና በቆሻሻ ክምችት የታወቀች፣ ለነዋሪዎቿም ሆነ ለጎብኚዎች የማትመች ከተማ ሆና ቆይታለች። በተለይም በወንዝ ዳርቻዎችና በሰፈሮች ውስጥ ይስተዋል የነበረው የፅዳት ጉድለት የመዲናዋን ዓለም አቀፋዊ ስም የሚመጥን አልነበረም።

ይሁን እንጂ ይህንን ታሪካዊ ክብር ከቀደመው የመሠረተ ልማት ዝቅተኝነት ጋር አዛምዶ የመቀበል አመለካከት በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ፍጥነት እየተቀየረ ይገኛል። ይህንን የቆየ ከተማዋን ነባራዊ ሁኔታ ለመቀየር መንግሥት ቁርጠኛ አቋም በመያዝ፣ ከተማዋን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር ትኩረት ሰጥቶ ሲሰራ መቆየቱን ከንቲባዋ አስገንዝበዋል። ይህም ለውጥ ከተማዋን ከነበረችበት ዝቅተኛ ደረጃ አውጥቶ በዓለም አቀፍ መስፈርት ተወዳዳሪ ለማድረግ ያለመ መሆኑን አብራርተዋል።

ባለፉት ዓመታት የተከናወኑት ሰፊ የከተማ ኮሪደር ልማት እና የወንዝ ዳርቻ ፕሮጀክቶች የከተማዋን ገጽታ ሙሉ በሙሉ ቀይረውታል። በተጨማሪም በአንድ ጊዜ እስከ 10 ሺህ ሰዎችን ማስተናገድ የሚችለው ዘመናዊው አዲስ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማዕከል መገንባቱ፣ የጉባኤ (MICE) ቱሪዝምን በማሳደግ ረገድ ትልቅ አቅም ፈጥሯል። ባለፈው ዓመት ብቻ ከ150 በላይ ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን ማስተናገድ መቻሉ እንዲሁም ታዋቂ የዲጂታል ሚዲያ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች መምጣት የከተማዋን ደኅንነት እና ውበት በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ ዓለም አቀፍ ተመልካቾች አስተዋውቋል።

አዲስ አበባ የአፍሪካ ሕብረት እና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኢኮኖሚ ኮሚሽን መቀመጫ በመሆኗ፣ የከተማዋ የኮሪደር ልማት በተመራማሪው ሮድሪጎ ታቫሬስ የገጽታ ግንባታ ንድፈ-ሐሳብ መሰረት ለኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ አቅም ትልቅ ጉልበት ነው። ተመራማሪው "አንድ ሀገር በአለም መድረክ የሚኖራት ስም የሚቀየረው በባዶ ማስታወቂያ ሳይሆን በተጨባጭ ተግባር ነው" እንደሚለው ሁሉ፣ የኮሪደር ልማቱ በተግባር የከተማዋን መልክ እየቀየረ ይገኛል።

ሰፋፊ የእግር መንገዶች፣ ንጹህ አረንጓዴ ስፍራዎች እና ዘመናዊ የመንገድ መብራቶች መገንባታቸው የከተማዋን ገጽታ ከፍ በማድረግ፣ የዲፕሎማሲ ማዕከላት ጋር እንድትወዳደር እና የውጭ ባለሀብቶችና ዲፕሎማቶች ተመራጭ መዳረሻ እንድትሆን ያደርጋታል የሚሉት ደግሞ የፖለቲካና ዓለምአቀፍ ግንኙነት ተንታኙ አቶ ዳያሞ ዳሌ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፤ የኮሪደር ልማቱ አዲስ አበባን ከነበሩበት የተጨናነቀና ኋላቀር ገጽታ አውጥቶ ወደ ዘመናዊ፣ ፅዱ እና ለኢንቨስትመንት ሳቢ ማዕከላት የመቀየር ትልቅ አዎንታዊ አስተዋጽኦ አበርክቷል።

የኮሪደር ልማት ፕሮጀክት የመንገድ ጥገና ወይም የማስዋብ ሥራ ብቻ ሳይሆን፤ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እና የማኅበራዊ ሕይወት ገጽታ ሙሉ በሙሉ የለወጠ ሥር ነቀል ከተማን የማደስ ሥራ ነው። የከተማ እና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ይፋ ባደረገው መረጃ መሰረት፣ በአሁኑ ወቅት የኮሪደር ልማቱ በአዲስ አበባ ከተገኘው ስኬት በመነሳት ወደ 75 በሚጠጉ የሀገሪቱ ዋና ዋና ከተሞችና ታዳጊ ከተሞች ተስፋፍቷል። ይህም ሀገሪቱ ከተበታተነና ጥራት ከጎደለው የመሠረተ ልማት አሠራር ወጥታ ወደ ዘመናዊና የተቀናጀ የከተሜነት ምዕራፍ መሸጋገሯን ያመላክታል።

የኮሪደር ልማቱ ከዚህ ቀደም የነበሩ የከተሞች መዋቅራዊ ችግሮችን በጥቅሉ የፈታ ሲሆን፣ የኮሪደር ልማቱ ሰፊ የእግረኛ፣ የብስክሌትና የስፖርት ማሳለጫ መንገዶችን፣ አየር ላይና ከመሬት በታች ድልድዮችን እንዲሁም ዘመናዊ የታክሲና አውቶቡስ ማቆሚያዎችን አካቶ ተገንብቷል። በኮሪደር ልማቱ ባዶና ቆሻሻ መጣያ የነበሩ ስፍራዎች ወደ አረንጓዴ መናፈሻዎችና የሕዝብ መዝናኛዎች ተቀይረዋል። ዘመናዊ የመንገድና የህንጻ መብራቶች መገጠማቸው ደግሞ የደህንነት ስሜትን በመጨመር የሌሊት የንግድ እንቅስቃሴ እንዲነቃቃ አድርጓል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንደሚገልጹት፣ የኮሪደር ልማቱ የመንገድ ግንባታ ብቻ ሳይሆን የከተማዋን ደረጃ የሚያሻሽልና የዜጎችን ሥነ-ልቦና ሚያንጽ ስትራቴጂያዊ ፕሮጀክት ነው።

አዲስ አበባን የጎበኙ የተለያዩ ሀገራትና ተቋማት መሪዎችና በከተማዋ የታየውን ፈጣን ለውጥ በግርምት ተመልክተዋል። መሪዎቹ በጉብኝታቸው ወቅት "አዲስ አበባ በየቀኑ መልኳን እየቀየረች ያለች ድንቅ ከተማ ሆናለች" በማለት አድናቆታቸውን ገልጸዋል። በተለይ እንደ ዓድዋ መታሰቢያ ሙዚየም እና የታደሱ አደባባዮችን የጎበኙ እንግዶች፣ ከተማዋ የታሪካዊ ክብር እና የዘመናዊነት ውህድ መሆኗን መስክረዋል። አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲና እንደመሆኗ፣ እንዲህ ውብ እና ፅዱ መሆኗ ለመላው አህጉር ኩራት ነው" የሚለው ሐሳብ በብዙዎቹ ዘንድ ተደጋግሞ ተደምጧል። አዲስ አበባ ለጎብኝዎቿ እያሳየች ያለው አዲስ ገጽታ "የማይቻል የለም" የሚል መልእክት እያስተላለፈ ሲሆን፣ የመሪዎቹ አስተያየትም ይህንኑ እውነታ የሚያጠናክር ሆኖ እናገኛቸዋለን።

አንዳንድ ከተሞች ከድንበራቸው ባለፈ የዓለም ዕጣ ፈንታ የሚወሰንባቸው፣ የታሪክ አቅጣጫ የሚቀየርባቸውና የኃያላን መሪዎች መገናኛ የመሆናቸው ምስጢር በድንገት የሚከሰት አይደለም። አንድን ከተማ ለዓለም አቀፍ ተቋማትና ለመሪዎች ተመራጭ የሚያደርጓት የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። ከተማዋ ያላት አንጻራዊ የሰላም ሁኔታና የደህንነት አስተማማኝነት እንደ ዋነኛ መስፈርት ይወሰዳል። መሪዎች በነጻነት የሚመክሩባት፣ የዲፕሎማሲያዊ ጥበቃና ከለላ የተረጋገጠባት ከተማ ሁልጊዜም የሁለንተናዊ ትብብር መፍለቂያ ትሆናለች።

ከተሞች ለዓመታት የተበላሸ ስማቸውን ለማደስ የልማት ሥራ ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ለማሳየት ኪጋሊን በአስረጅነት ጠቅሰን ጉዳያችንን እንቋጭ። ዛሬ ላይ ዓይነ ግቡ የሆነችው ኪጋሊ ከሦስት አስርት ዓመታት በፊት ጭፍግግ ያለ ገጽታ ያላት መላአከ ሞት ያረበባት ከተማ ነበረች። ይቺ ከተማ በአንድ መጥፎ ቀን በዘር ግጭት ምክንያት ለሆሊውድ ፊልም የቀረበ አስፈሪ ሁነት አስተናግዳ እስከ 1 ሚሊዮን የሚደርሱ ዜጎቿን የቀበረች ከተማም ነበረች። ኪጋሊ ዛሬ ላይ መልኳ ተቀይሯል።

ሩዋንዳውያኑ ጉዳያቸውን በጠረጴዛ ዙሪያ ከበው በመወያየት በዘር ጭፍጨፋ የላሸቀችውን አገር አሁን ወዳለችበት ደረጃ አድርሰዋታል። ሀገሪቱ በምጣኔ ሀብት እንድትዳብር፣ በጤና፣ በቴክኖሎጂ እና በቱሪዝም የላቀች እንድትሆን ጠንክረው ሥራ ስለሠሩም ብዙ አብነቶችን ማንሳት ይቻላል። እ.ኤ.አ. በ2008 የኪጋሊ ከተማ ከተባበሩት መንግሥታት በተሰጠው የ‹Habitat Scroll of Honor› የተሰኘውንና በአፍሪካ የመጀመሪያዋ ያደረጋትን ሽልማት ያገኘችውም ለዚሁ ነበር።

# ባህል እየሆነ የመጣው አረንጓዴ አሻራ

- በከተማ ደረጃ የተተከሉ ችግኞችን በቋሚነት የሚንከባከቡ ወደ 30 ሺህ የሚጠጉ የማህበረሰብ ክፍሎች እንዳሉ ተመላክቷል

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**



ፎቶ፡- ከገፀ ድር

የመዲናዋ ነዋሪዎች በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ተሳትፎ ላይ

አዲስ አበባ ከተማን ጽዱ፣ ውብ እና ለኑሮ ምቹ ለማድረግ እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም ከሚከናወኑት ሰፋፊ የልማት ስራዎች መካከል የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ዋነኛው ነው። ይህንን መርሃ ግብር የህብረተሰቡ የዕለት ተዕለት የባህል አካል ለማድረግ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።

በከተማዋ የአረንጓዴ አሻራን ባህል ከማድረግ አንፃር በዋናነት እየተሰሩ ካሉ የግንዛቤ ስራዎች መካከል የትምህርት ተቋማት፣ የማህበረሰብ አደረጃጀቶች እና የወጣት ማህበራት እንዲሁም የተለያዩ ተቋማት ተሳትፎ እንዲጠናከር መደረጉ ተጠቃሽ ነው፡፡

በተለይም በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የአካባቢ ጥበቃ እና አረንጓዴ ክበቦች መጠናከራቸው ተማሪዎች ከለጋ እድሜያቸው ጀምሮ ችግኝ የመትከል እና የመንከባከብ ባህል እንዲያዳብሩ ከመደረጋቸው ባሻገር ችግኝ መትከልና መንከባከብ ከትውልድ ትውልድ የሚሸጋገር እለታዊ ተግባር እንዲሆን ማስቻሉን ነው አንዳንድ ያነጋገርናቸው ወጣቶች የሚመሰክሩት፡፡

ይህን ሃሳብ የሚያጠናክርልን በዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በአካውንቲንግ ትምህርት ክፍል የሁለተኛ ዓመት ተማሪ የሆነችው ወጣት ፀሃይ አለማየሁ የሰጠችን አስተያየት ነው፡፡ በአዲስ አበባ የአረንጓዴ አሻራን ባህል ከማድረግ አኳያ እየተሰሩ ያሉ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራዎች በእጅጉ የሚበረታቱ ናቸው የምትለው፤ ወጣቷ በተለይ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አከባቢን ፅዱ አረንጓዴና ምቹ በማድረግ ላይ በሚያተኩሩ እንደ አከባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ያሉ ክበባት አረንጓዴ አሻራ የአንድ ወቅት ብቻ ስራ ሳይሆን የዘውትር ተግባር መሆኑን የሚያስገነዝቡ ናቸው፡፡

አከባቢን ውብና አረንጓዴ ማድረግ የሰው ልጆችን ጤና ለመጠበቅ ብሎም አኗኗርን ለማሳመር ብቻ ሳይሆን ለእንሰሳትም ሆነ የአከባቢን ስነ ምህዳር ለመጠበቅ የሚያስችል ነው፡፡ ከዚህ አኳያ አረንጓዴ አሻራ ወቅት ጠብቀን በዓመት አንድ ጊዜ ወይም ክረምት ላይ ብቻ የምናከናውነው ተግባር ሳይሆን ዓመቱን ሙሉ የምናከናውነው ነው ብላለች፡፡

እንደተማሪ ፀሃይ ገለፃ የሰው ልጅ ከፅንሰቱ ጀምሮ ተወልዶ እስከሚያድግ የቤተሰቦቹን ልዩ እንክብካቤ እንደሚሻ ሁሉ ችግኞችም ተተክለው ዛፍ እስከሚሆኑ ድረስ ውሃ ማጠጣት መኮትኮትና በእንሰሳት እንዳይበሉ ከለላ ማድረግ የመሳሰሉ እንክብካቤዎች ያስፈልጋቸዋል፡፡

አቶ አድማሱ ፈለቀ የተባሉ ሌላው አስተየየት ሰጪ በበኩላቸው በእርግጥ ደን ልማትና የአከባቢ ጥበቃ ስራ የቆየ ጅምር ነው ብለው በተለይ ከሚሊኒየሙ ወዲህ በአገር አቀፍ ደረጃ የክረምት ወቅትን በመጠበቅ ተግባራዊ ሲደረግ እንደነበር ነገር ግን የበለጠ ትኩረት ያገኘው አሁን ባለው የለውጥ መንግሥት እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

መንግስት የአረንጓዴ አሻራ በማበረሰቡ ዘንድ የእለት ተግባር እንዲሆን ግንዛቤ ከማስረፅ ባለፈ እራሱ ግንባር ቀደም በመሆን በገጠርም በከተማም ብዙ ችግኞች እንዲተከሉ እያደረገ ነው የሚሉት አስተያየት ሰጪው፤ ብዙኃኑ የህብረተሰብ ክፍል በአከባቢው በተለይም በጋራ መኖሪያ ግቢዎች የተለያዩ አትክልትና ፍራፍሬዎች፣ እንዲሁም ቋሚ ተክሎች መትከል እለታዊ ተግባር እያደረገው መምጣቱን ታዝቤያለሁ ባይ ናቸው፡፡

በኮዬ ፈጬ የጋራ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ሰብለ በላይሁንም አረንጓዴ አሻራ የአንድ ወቅት ብቻ ሳይሁን ዘወትር ልናከናውነው የሚገባ የህይወታችን አንድ አካል ነው ይላሉ። ይህንንም እሳቸው በሚኖሩበት የጋራ መኖሪያ (ኮንዶሚኒየም) ግቢ ለእለት ፍጆታ የሚውሉ እንደ ጎመን፣ ቆስጣ፣ ካሮትና ቀይስር ካሉ አትክልቶች በተጨማሪ ለጥላ የሚያስፈልጉ ችግኞችን ተክለው ከመንከባከብ ባለፈ ከግቢው ማህበረሰብ ጋር በጋራ በመሆን እንደ አቮካዶ፣ ዘይቱን፣ ሸንኮራ፣ ሙዝና ፓፓያ ያሉ ለምግብነት የሚውሉ ቋሚ ተክሎችን በመትከል አከባቢያቸውን ፅዱና አረንጓዴ በማድረግ ተግባራዊ ማድረጋቸውን ነግረውናል፡፡

በአከባቢያቸውም ሆነ እንደከተማ አረንጓዴ አሻራ ባህል ሆኖ መቀጠሉን መታዘባቸውን የሚጠቁሙት ወይዘሮ ሰብለ፤ ክረምት ከበጋ ሳይሉ አትክልቶችን መትከልና መንከባከብ የዘወትር ተግባራቸው መሆኑን ይህን ልማድ ለወደፊቱም አጠናክረው እንደሚቀጥሉ አረጋግጠዋል፡፡

በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ በተለይ ለአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ሃሳባቸውን ያጋሩን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ የፕሮጀክት ስራዎች ቁጥጥርና ህብረተሰብ ተሳትፎ ዳይሬክተር አቶ እሸቱ ሙሉ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር በማህበረሰቡ ዘንድ ባህል ሆኖ እንዲቀጥል የተለያዩ ንቅናቄዎችና ግንዛቤ ማስጨበጥ ስራዎች መሰራታቸውን ነው የሚያረጋግጡት፡፡

እንደ እሳቸው የተተከሉ ችግኞችን መንከባከብን ጨምሮ አጠቃላይ የአረንጓዴ ልማት ስራ ዘላቂ፣ ቀጣይነትና ባለቤት እንዲኖረው ለማድረግ ከቢሮ እስከ ወረዳ የተዘረጋ ተቋማዊ አሰራር አለ፡፡ በዚህ ውስጥ የተቋቋሙት የግንዛቤና የህብረተሰብ ተሳትፎ ባለሙያዎች በየደረጃው ያሉ የማህበረሰብ አደረጃጀቶች በተለይም የወጣት ማህበራት እና የተለያዩ ተቋማት ተሳትፎን በማጠናከርና ክትትል በማድረግ የአረንጓዴ ልማት ባህል ሆኖ እንዲቀጥል ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረጉ ነው፡፡

የወጣቶች በጎ ፈቃድ አገልግሎትም ግንዛቤ ከሚፈጠርባቸው አንዱ ሲሆን ከተማ አቀፍ በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ስራዎች ውስጥ ወጣቶች በግንባር ቀደምትነት እንዲሳተፉ በመደረጉ፣ ወጣቱ ትውልድ ለአካባቢ ጥበቃ ያለው ግንዛቤ በየዓመቱ እያደገ መጥቷል።

ሌላው ደግሞ የመንግሥት፣ የግል ተቋማት እና የህዝብ ለህዝብ የንቅናቄ ስራዎች መጠናከራቸው ሲሆን በዚህ ረገድ የጋራ መድረኮች እና የፓናል ውይይቶች ሰፊ ድርሻ አላቸው ብለዋል። በከተማዋ በየደረጃው በሚገኙ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች፣ የንግድ ማህበረሰቦች እና የሲቪክ ማህበራት መካከል የአረንጓዴ አሻራን አስፈላጊነት የሚገልጹ ውይይቶች እና መድረኮች መዘጋጀታቸውም የዚሁ አካል ናቸው።

ይህ ብቻም ሳይሆን የአምባሳደሮች እና ታዋቂ ሰዎች ተሳትፎ ዘርፉ ባህል ሆኖ እንዲቀጥል የሚያደርግ ሲሆን አርቲስቶች፣ ስፖርተኞች እና ሀገር አቀፍ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች በችግኝ ተከላ መርሃ ግብሮች ላይ በንቃት እንዲሳተፉ በማድረግ ህብረተሰቡን የማስተባበር እና የማንቃት ስራዎች መሰራታቸው አረንጓዴ አሻራ በክረምት መርሃ ግብር ብቻ ሳይሆን በማህበረሰቡ ልቦና ውስጥ የዘወትር ተግባርና ባህል እንዲሆን መንገድ መክፈቱም ይታመናል።

ይህን ባህል አጠናክሮ በማስቀጠል ረገድ ከምንም በላይ ደግሞ የሚዲያ እና የህዝብ ግንኙነት ዘመቻዎች መጠናከር እንዳለባቸው በተለይም በቴሌቪዥን፣ በሬዲዮ እና በህትመት ውጤቶች አማካኝነት ዛፎች ለአካባቢ የሚሰጡትን ፋይዳ፣ የከተማ ግብርናን እና የፓርኮችን ልማት የሚመለከቱ ዶክመንተሪዎች፣ ጽሑፎች እና ማስታወቂያዎች በማስተላለፍ በመገናኛ ብዙኃን ሽፋን መስጠቱ በእጅጉ ጠቃሚ ነው ባይ ናቸው።

በዚህ ረገድ የዲጂታል ሚዲያ እና ማህበራዊ አውታረ መረቦችም ቢሆኑ ሚናቸው በቀላሉ የሚገለፅ አይደለም፡፡ ከተማዋን አረንጓዴ ለማድረግ የሚደረጉ ጥረቶችን የሚያሳዩ አጫጭር ቪዲዮዎች እና መልዕክቶች በማህበራዊ ሚዲያ ገጾች በመለቀቅ ሰፊ ግንዛቤ እየተፈጠረም ነው።

የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብሩ ቀጣይነት እንዲኖረው ከሚደረጉ የቅስቀሳና ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ጎን ለጎን በዘርፉ ላይ የነቃ ተሳትፎ የሚያደርጉ ተቋማትና አከላትን መሸለምና ማበረታታትም ሌላው መንገድ ነው፡፡ ከዚህ አኳያም ጥሩ ለሰሩ ከሰርትፍኬት እስከ ዋንጫ የሚሸለሙበት አግባብ መኖሩን ነው አቶ እሸቱ የጠቀሱት፡፡

እነዚህ ተግባራት በመከናወናቸውም የመጡ ለውጦች አሉ ብለው በተለይም ህብረተሰቡ ያለማንም ጎትጓች ወቅትና ጊዜ ሳይገድበው አከባቢውን መንከባከብና ማልማት ብሎም ዓመቱን ሙሉ የአረንጓዴ አሻራ ስራን ተግባራዊ ማድረግ መቻሉን በበጎ ጎን አንስተዋል።

የማህበረሰቡ ግንዛቤም እለት ከእለት እያደገ በመምጣቱም የከተማዋ ነዋሪዎች የመኖሪያ መንደሮችን ጨምሮ ባሉ ክፍት ቦታዎች ችግኞችን መትከልና መንከባከብ ብቻ ሳይሆን በከተማ ደረጃ የተተከሉ ችግኞችን በቋሚነት የሚንከባከቡና ውሃ የሚያጠጡ ወደ 30 ሺህ የሚጠጉ የማህበረሰብ ክፍሎች መኖራቸውን አስረድተዋል። በማህበረሰቡም ሆነ በተቋማት በአስራ አንዱም ክፍለ ከተማ የተከናወኑ የአረንጓዴ ልማት ስራዎች በገንዘብ ሲተመኑ ከ1 ነጥብ 2 ቢሊየን ብር በላይ ነውም ብለዋል፡፡

# የሀገርን እጣ ፈንታ በውይይት መድረክ

- **ለምክክሩ ስኬታማነት ከተመካካሪዎች ባለፈ ሌሎች ባለድርሻ አካላትም ኃላፊነታቸውን መወጣት እንደሚጠበቅባቸው ተጠቁሟል**

**በስንታየሁ ምትኩ**

የሀገራዊ ምክክር ጉባኤው አባላት ከሐምሌ 8 ቀን 2018 ዓ.ም ጀምሮ በስምንት ዋና ዋና አጀንዳዎች ላይ ምክክር እያደረጉ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የአሰራር ስነ ዘዴ መሰረት ምክክሩ 10 አባላት ካሉት ቡድን ጀምሮ እስከ 500 አባላት ባሏቸው ስምንት የስራ ቡድኖች ድረስ ሲደረግ ቆይቷል፡፡

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ምክትል ዋና ኮሚሽነር ሂሩት ገብረ ሥላሴ ነሐሴ 7 ቀን 2018 ዓ.ም ለመገናኛ ብዙኃን በሰጡት መግለጫ፤ 500 አባላት ያሏቸው ቡድኖች በተወያዩባቸው አጀንዳዎች ዙሪያ መግባባት ላይ በመድረስ ምክረ ሀሳቦቹ ላይ መፈራረማቸውን ገልጸዋል።

በቀጣይም ስምንቱ ቡድኖች ተስማምተው ያዘጋጁቸውን ምክረ ሀሳቦች የሚያጣጥም ቡድን ተቋቁሞ ሥራውን ይጀምራል። በአሁኑ ወቅት አብዛኛው የምክክር ጉባኤ ሥራዎች በመጠናቀቅ ላይ ይገኛሉ። ይህም ለሰላም ግንባታው ተስፋ ሰጪ ጅምር ሲሆን፣ ቀሪ ሂደቶች ካለቁ በኋላ መግባባት ላይ የተደረሰባቸው ምክረ ሀሳቦች ለህዝብ ይፋ ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል።

ይህ የውይይትና ምክክር ሂደት ውጤታማ ሆኖ የሚፈለገው ግብ ላይ እንዲደርስ ሸክሙ በምክክር አዳራሽ ውስጥ ባሉት ተመካካሪዎች ትከሻ ላይ ብቻ የሚወድቅ አይደለም። ከምንጊዜውም በላይ የሁሉንም ባለደርሻ አካላት ትብብርና ተሳትፎ ይጠይቃል። የኮሚሽኑ ዋና ሰብሳቢ መስፍን አርዓያ (ፕሮፌሰር) ነሐሴ 4 ቀን 2018 ዓ.ም በሰጡት መግለጫ፣ የምክክር ጉባኤው ከተጀመረ አንድ ወር የሞላው ሲሆን ሂደቱ በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደና ውጤት እየተገኘበት እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

መስፍን (ፕ/ር) ለተመካካሪዎች፣ አመካካሪዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ባስተላለፉት መልእክትም፣ መከባበር፣ መደማመጥ፣ መነጋገርና ወደመሀል መምጣት የምክክሩ ዋና መርህ ነው፡፡ ተመካካሪዎች ከየአካባቢው ይዘዋቸው የመጡ ብዙ ጥያቄዎች ሊኖሩ ይችላሉ። በመድረኩ ግን ኢትዮጵያን ማዕከል በማድረግ መመካከር እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል፡፡

የሰላምና ደህንነት መምህርና ተመራማሪው አሌክስ ብርሃኑ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፣ ምክክሩ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በመወከል በአዳራሽ እየተመካከሩ ካሉት ባሻገር ሁሉንም ባለድርሻ አካላትና ዜጎች ይመለከታል፡፡ ዜጎች የምክክሩን ሂደት መከታተል እና መረጃ መፈለግ ይኖርባቸዋል። ታዲያ ከዚህ ጋር ተያይዞ በተለያዩ የማህበራዊ ትስስር ገጾችና መድረኮች ዋልታ ረገጥ ሀሳብ እየተንሸራሸረ ይገኛል፡፡ ሀሳብ መንሸራሸሩ ችግር ባይኖረውም፣ ገንቢ በሆነ መልኩ መቅረብ ግን አለበት።

በአሁኑ ወቅት በምክክሩ ሂደት አንደኛው ፈተና ከመረጃ ጥራት ጋር እንደሚያያዝ የሰላምና ደህንነት ምሁሩ አሌክስ ያነሳሉ፡፡ ሰዎች በተለያዩ የማህበራዊ ትስስር ገጾች የተቆራረጠ ቪዲዮ ሊያዩ ወይም ያልተሟላ መረጃ ሊያገኙ ይችላሉ። ያለምንም ማጣራት መረጃውን ሲያጋሩና ሲቀባበሉ ሀሰት የሆነው እንደ እውነት ሊቆጠር ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ ከተነገረበት አውድ ውጪ እየተሰራጨ ህብረተሰቡን ሲያሳስት ይታያል፡፡ ከዚህ አኳያ ሰዎች ማህበራዊ ሚዲያ ላይ የሚመለከቷቸውን መረጃዎች ከማጋራታቸው በፊት ትክክለኛ መሆኑን ቆም ብለው ማሰብ፣ ምንጮችን መለየትና ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል። የተቆራረጠ መረጃ ከመውሰድ ይልቅ ሙሉን በመከታተል ግንዛቤ መጨበጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡




ፎቶ ከገፀ ድር

በስምንት የአጀንዳ ርዕሰ ጉዳዮች ሲመካከሩ የቆዩት የአጀንዳ ቡድኖች መግባባት ላይ መድረስ ችለዋል

የሰላምና ደህንነት ምሁሩ አሌክስ እንደሚገልፁት፣ እየተመካከርንባቸው ያሉ ጉዳዮች ለብዙ ዘመናት የቆዩ ናቸው። የአለመግባባት ምክንያት የሆኑ ሁሉም ችግሮች በጥቂት ሳምንታት ወይም በአጭር ጊዜ ውስጥ ላይፈቱ ይችላሉ። ምክንያቱም በየጊዜው እየተፈጠሩ በመጡ ችግሮች እንደማህበረሰብ በተለያዩ ተቋማት ላይ ያለን የመተማመን ካፒታላችን ተሸርሽሯል፡፡ ከዚህ አኳያ አንዳንድ ጉዳዮች በምክክሩ ሂደት መግባባት ላይ የማይደርስባቸው ከሆነ በሂደት ተቋም ሲገነባ እና መተማመን እየጎለበተ ሲመጣ መፍትሔ ያገኛሉ።

እየተካሄደ ያለው የምክክሩ ሂደት ስኬታማ እንዲሆን ምሁራን፣ የመገናኛ ብዙሃን፣ ሲቪክ ማህበራትን ጨምሮ የሁሉም ባለድርሻ አካል ተሳትፎና ድጋፍ ወሳኝ መሆኑን የሰላምና ደህንነት መምህርና ተመራማሪው አሌክስ ያነሳሉ። ምሁራን ከቡድን ስሜት በመውጣት በመረጃና በማስረጃ ላይ ተመስርተው እውነታን ማጋራት ይጠበቅባቸዋል። የአለመግባባት ምክንያት የሆኑ ችግሮችን ለምሳሌ በታሪክ ዙሪያ ያለውን አለመግባባት በማስረጃ አስደግፎ ማቅረብ፣ የፖሊሲ አማራጮችን ማመላከት እና ህብረተሰቡን ከስሜታዊ ክርክር ወደ ምክንያታዊ ክርክር መምራት አለባቸው። ምሁርነት ታዋቂነትን ሳይሆን ታማኝነት፣ ምክንያታዊነትና ለእውነት መቆምን የሚያስቀድም ነው፡፡

ለምክክሩ መሳካት ሚና ካላቸው አካላት መካከል መገናኛ ብዙሃን ይጠቀሳሉ፡፡ የሰላምና ደህንነት ምሁሩ አሌክስ እንደሚያስረዱት፣ መገናኛ ብዙሃን ልዩነትን፣ መቃቃርን እና ጥላቻን ከሚያባብሱ ይልቅ ሀገራዊ ውይይትን፣ መተባበርን፣ አንድነትን፣ ፍቅርን የሚያጠናክሩ ይዘቶችን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የሚያሰራጩት ይዘት 'የወደፊት የሀገርን ዕጣ ፈንታ የሚገነባ ወይስ የሚያፈርስ ነው' የሚለውን በደንብ መመዘን ይኖርባቸዋል፡፡ በማህበራዊ ሚዲያ የሚሰራጩ ሀሰተኛ መረጃዎችን እና የጥላቻ ንግግሮችንም በደንብ መለየትና እነዚህን ድርጊቶች ለመከላከል ለህብረተሰቡ የመረጃና የሚዲያ አጠቃቀም እውቀት (Media Literacy) መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ሀሰተኛ መረጃዎችን በማጣራት ማረም፣ የምክክሩን መረጃዎች አውድ ለአድማጭ ተመልካች በአግባቡ ማሳወቅ እና የጥላቻ ንግግሮችን ማስቆም ይጠበቅባቸዋል።

> **መገናኛ ብዙሃን ልዩነትን፣ መቃቃርን እና ጥላቻን ከሚያባብሱ ይልቅ ሀገራዊ ውይይትን፣ መተባበርን፣ አንድነትንና ፍቅርን የሚያጠናክሩ ይዘቶችን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል**

የሰላምና ደህንነት ምሁሩ አሌክስ እንደሚገልፁት፣ ከሰፊው የማህበረሰብ ክፍል ሶስት ዋና ዋና ኃላፊነቶች ይጠበቃሉ፡፡ አንደኛው ትዕግስት ሲሆን ምክክር በአጭር ጊዜ ወይም በአራት ዓመት ውስጥ የሚጠናቀቅ ስራ አይደለም፤ ሂደት ነው። በአንዳንድ ሀገራት 15 ዓመት እና ከዚያ በላይ የወሰደበት ሁኔታ አለ፡፡ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ሌላው የሚጠበቅ ኃላፊነት ሲሆን ምክክሩ በአዳራሽ ውስጥ እየተመካከሩ ካሉት ባሻገር ከጀርባቸው ያሉ በርካታ ሚሊዮን ዜጎችን የሚመለከት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ "የእኔ፣ የልጆቼ እና የሀገሬ ጉዳይ ነው" በማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መሳተፍ ይገባቸዋል። እያንዳንዱ ዜጋ የሚናገረው፣ በማህበራዊ ሚዲያ የሚለጥፈው ወይም የሚያጋራው መረጃ ሁሉ ኃላፊነት በተሞላበትና በጥንቃቄ ሊሆን ይገባል።

የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ምሁሩ መኮንን አለሸኝ በበኩላቸው፣ ለምክክሩ ስኬት የባለድርሻ አካላት ተሳትፎና ድጋፍ ወሳኝ ነው፡፡ ከመንግስት ጀምሮ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ምሁራን፣ የፀጥታ ተቋማት፣ የዳኝነት አካላት፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ የንግድ ማህበረሰብ፣ የዲያስፖራ ማዕከላት እንዲሁም የዓለም አቀፍ የልማት አጋሮች ሰላምና ፀጥታን ማስጠበቅ፣ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግን፣ ገንቢ የሆኑ አስተያየቶች ማቅረብን ጨምሮ ለስኬታማነቱ ወሳኝ ሚና እንደሚጠበቅባቸው ለዝግጅት ክፍላችን ተናግረዋል፡፡

ከአፍሪካ እስከ እስያ፣ አውሮፓ እና ላቲን አሜሪካ ያሉ ሀገራት ከገቡበት የግጭት አዙሪት ለመውጣት ሀገራዊ ምክክርን እንደመሳሪያ ተጠቅመዋል። ከሀገራዊ ምክክር የተገኙ ተሞክሮዎች (NATIONAL DIALOGUE፡ Lessons Learned) በሚል ርዕስ ሙሉጌታ ጌቱ (ዶ/ር) እና ማርቆስ ደበበ በጋራ ያጠኑትና በፈረንጆቹ አቆጣጠር 2022 የወጣ ሰነድ እንደሚያመለክተው፣ ሀገራዊ ምክክር በባህሪያቸው አከራካሪ የሆኑና ሁሉንም የሀገሪቱን ዜጎች የሚመለከቱ በርካታ ጉዳዮች ላይ ውይይት የሚደረግበት እንደመሆኑ ለሂደቱ ውጤታማነት የባለድርሻ አካላት ድጋፍና አስተዋፅኦ ወሳኝ ነው፡፡

በአብዛኞቹ ብሔራዊ ምክክሮች መንግሥት ድርብ ሚና አለው። አንደኛ ውጤታማ ውይይት ለማካሄድ ምቹ ሁኔታ መኖሩን ማረጋገጥን ጨምሮ የዕለት ተዕለት የመንግሥት ሥራዎችን የማከናወን ኃላፊነት አለበት። ሁለተኛው ደግሞ መንግሥት የመሠረተው ፓርቲ ወይም ቡድን ከሌሎች የፖለቲካ ቡድኖች ጋር በመሆን የብሔራዊ ምክክሩ ዋና ተሳታፊ ነው። ከዚህ አኳያ በውይይቱ የሚሳተፉ አካላት መንግሥት ለውይይቱ ውጤቶች ቁርጠኛ ይሆናል እንዲሁም ምክረ ሃሳቦቹን በመተግበር ረገድ መሪ ሚና ይጫወታል በሚል እምነት ስለሆነ ይህን መተማመን የሚያሳድጉ እርምጃዎች መወሰድ ይጠበቅበታል። ምክክሩን የሚያስተባብረው አካል ነጻነቱ ተጠብቆ እንዲሰራ ማድረግ፣ የህግ የበላይነትንና መልካም አስተዳደርን ማረጋገጥ፣ ለምክክር ሂደቱ መሳካት የገንዘብና ሎጂስቲክስ ድጋፍ ማድረግ ከመንግስት ከሚጠበቁ ኃላፊነቶች መካከል ይጠቀሳሉ፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ማህበራት፣ የተለያዩ የማህበረሰብ ቡድኖችና ሌሎች አካላትም ለሂደቱ መሳካት ሚና አላቸው፡፡

# የውበትና የህይወት ማዕከል

**• በኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ሥራ ከ230 ሺህ በላይ ዜጎች በጊዜያዊነትና በቋሚነት የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል**

**በስንታየሁ ምትኩ**



ፎቶ፡- በገነት ወንድሙ
በቀበና ወንዝ ዳርቻ ባሉት ሱቆች ዜጎች የተለያዩ ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛሉ

አዲስ አበባ 76 ወንዞችን በጉያዋ ብትይዝም፤ ለግብርናም ሆነ ለሌላ ጥቅም የሚውሉ አልነበሩም፡፡ ቆሻሻ ይጣልባቸው ስለነበር ተፈጥሯዊ ቀለማቸውን አጥተው እንደተቃጠለ ናፍጣ የጠቆሩ፣ የሚሰነፍጥ ሽታ የሚያወጡና የበሽታ ምንጭ የሆኑ፣ በሰው ህይወትና ንብረት ላይ አደጋ የሚያስከትሉ፣ እንዲሁም ህገ ወጥ ተግባር ለሚፈጽሙ በመደበቂያነት የሚያገለግሉ፣ ለደህንነት ስጋት የሆኑ ስፍራዎች ነበሩ፡፡

ምስጋና በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አነሳሽነት ለተጀመረው የወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክት መጀመር ይግባውና፣ ዛሬ ላይ ተቀይረው የአዲስ አበባ የውበት መገለጫ፣ የእረፍት ቦታዎች እንዲሁም የኢኮኖሚ ማዕከላት ሆነዋል። ልማቱ የወንዞችን እና በአካባቢያቸው ያለውን ገጽታ ከማሳመርና ሥነ-ምህዳርን ከመጠበቅ ባለፈ፣ በበርካታ ዜጎች በተለይም ወጣቶች ተጠቃሚ የሆኑበትን ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠሪያ ማዕድ በመሆን ላይ ይገኛሉ። ይህ ሁለገብ ልማት አካባቢያዊ ጽዳትን ከኢኮኖሚያዊ ትርፋማነት ጋር በማቀናጀት ለከተሞች ዘላቂ ልማት ትልቅ ምዕራፍ ከፍቷል።

ከተማዋ ካላት ትላልቅ ወንዞች መካከል ቀበና አንዱ ነው፡፡ የቀበና ወንዝ ከእንጦጦ ፈልቆ ተራራማና ውብ በሆነው መልክዓምድር መካከል በርካታ ሰፈሮችን እያቆራረጠ እስከ አቃቂ ድረስ ይፈስሳል። ይህ ወንዝ በቀደመው ጊዜ ለአዲስ አበባ ነዋሪዎች መዝናኛን ጨምሮ የተለያዩ አገልግሎቶች ሲሰጥ የቆየ፣ የብዙዎች ትዝታና ታሪክ የታተመበት ነው፡፡ በተለምዶ ፈረንሳይ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪ የሆኑት አቶ ደበበ ሀይሉ ለዝግጅት ክፍላችን እንደተናገሩት፣ ወንዙ በድሮ ጊዜ ንፁህ፣ ለመጠጥና ለተለያዩ አገልግሎቶች ሲውል የቆየ ቢሆንም በጊዜ ሂደት እየቆሸሸ መጥቷል። ከላይ ሲታይ ንጹህ ይምሰል እንጂ ውስጡ በሽታ አምጪ በሆኑ የተለያዩ ኬሚካልና ፍሳሾች ተበክሎ ነበር፡፡

ታዲያ በወንዝ ዳርቻ ልማት ወንዙ የፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮች ተዘርግቶለታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በልማቱ ፀድቶ፣ በወንዝ ዳርቻ የአስፋልት፣ የኮንክሪት፣ የእግረኛ፣ የሳይክል መንገዶች፣ የህዝብ መፀዳጃ ቤቶች፣ የስፖርት ሜዳዎች፣ ድልድዮች፣ ግድቦችና የተለያዩ መዝናኛ አገልግሎቶች ተካትተዋል፡፡ ዛፎችን፣ አበቦችን፣ የተለያዩ ቅርጻ ቅርጾችን ጨምሮ ሰዎች እረፍት የሚያደርጉበትና መንፈሳቸውን የሚያድሱበት ስፍራ ሆኗል፡፡

ውብና የአይን ማረፊያ ሆኖ በተሰራው በቀበና ወንዝ ዳርቻ በሚገኘው ትልቅ ግድብ ፊት ለፊት ሱቆች ተገንብተዋል። ነዋሪዎችና አካባቢውን ለመጎብኘት የሚመጡ እንግዶች አረፍ ብለው ግድቡን እየተመለከቱ፤ አሻግረው ድንቅ የሆነውንና አረንጓዴ ለብሶ የሚታየውን ተራራማ መልክአ ምድር እየቃኙ ሻይ ቡና የሚሉባቸው አልባሳትን፣ የስፖርት ትጥቆችን፣ ጌጣ ጌጦችንና የተለያዩ ምርቶችን የሚሸምቱባቸው ሱቆች ይገኛሉ፡፡

**በቀበና ወንዝ ዳርቻ በሚገኘው ትልቅ ግድብ ፊት ለፊት ሱቆች ተገንብተዋል። ነዋሪዎችና አካባቢውን ለመጎብኘት የሚመጡ እንግዶች አረንጓዴ ለብሶ የሚታየውን ተራራማ መልክአ ምድር እየቃኙ ሻይ ቡና የሚሉባቸው፣ አልባሳትን፣ የስፖርት ትጥቆችን፣ ጌጣ ጌጦችንና የተለያዩ ምርቶችን የሚሸምቱባቸው ሱቆች ይገኛሉ**

በወንዙ ዳርቻ ባሉ የንግድ ሱቆች በኪራይ የመሥራት ዕድል ካገኙት መካከል ወይዘሮ ደስታ ደቻሳ አንዷ ናቸው፡፡ የወንዝ ዳርቻው ልጆች ተጫውተውና ቦርቀው የሚያድጉበት፤ ወላጆቻቸው አእምሯቸውን የሚያሳርፉበት፤ የልጆች የነገ ተስፋ የሆነ ደስ የሚል ስፍራ እንደሆነ የሚገልጹት ወይዘሮ ደስታ፣ ከዚህ ቀደም ሱቅ በመከራየት የሻይ ቡና ይሰሩ ነበር፡፡ ሆኖም ቦታው ለሥራ ምቹ እንዳልነበር አብራርተዋል፡፡

አሁን በወንዝ ዳርቻ የሚሰሩበት ሱቅ በማግኘታቸው ደስተኛ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡ እየሠሩበት ያለው ስፍራ ፅዱ፣ ውብና የቱሪስት መዳረሻ በመሆኑ፣ በርካታ ሰዎች ቦታውን ለማየት እየመጡ ነው፡፡ ይህም የተሻለ ገቢ በማግኘት ስራቸውን የሚያሳድጉበት ዕድል እንደሚፈጥርላቸው እምነታቸው ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በእረፍት ቀናት (ቅዳሜና እሁድ) በርካታ ሰዎች ለመዝናናት ወደ አካባቢው ይመጣሉ፤ የተሻለ ገበያም አለው፡፡ ወደፊትም ሥራውን በማስፋት ለሌሎች ወገኖች የሥራ ዕድል የመፍጠር ዕቅድ አላቸው። በአሁኑ ወቅት በከፈቱት ቡና ቤትም (Coffee house) አይስክሬም ለሚሠሩ እና ቡና ለሚያፈሉ ሦስት ወገኖች የሥራ ዕድል ፈጥረዋል፡፡

የወንዝ ዳርቻው ለወይዘሮ ደስታ ብቻ ሳይሆን በጥበቃ፣ በፅዳት፣ አበባና ሳሮችን በመንከባከብ፣ በንግድና በግንባታ ለተሰማሩ በርካታ ወገኖች የሥራ ዕድል ፈጥሯል፡፡ ሌላኛዋ የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው የቀጨኔ አካባቢ ነዋሪ ወይዘሮ ማርታ መሰለ ይባላሉ። እንደ ወይዘሮዋ ገለጻ፣ ከዚህ ቀደም የሚሰሩት ስራ አልነበራቸውም፡፡ ከቀጨኔ መድኃኒዓለም እስከ እንጦጦ ባለው የወንዝ ዳርቻ የተተከሉ ሳርና አበቦችን በመንከባከብ የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸው ከአንድ ዓመት በላይ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ያ የቆሻሻ መጣያና መፀዳጃ የነበረው ወንዝ ከመልማት፣ ፅዱና ውብ ከመሆኑ ባሻገር፣ ለሰዎች የሥራ ዕድል መፍጠር ችሏል፤ በዚህም ደስተኛ ናቸው፡፡

በቀጨኔ በአይነቱ ለየት ያለ አገልግሎት እየሰጡ ያሉት ደግሞ አቶ ሄኖክ ጥላሁን ይባላሉ፡፡ “ፓፒ ፔትስ” የተሰኘ ካፌ በመክፈት ሰዎች ወደ ካፌው ለመዝናናት ሲመጡ ከሚያገኙት አገልግሎት ባሻገር እንደ ድመትና ውሻ ያሉ የቤት እንስሳትም ምግብና የተለያየ አገልግሎት የሚያገኙበት ነው። የካፌው ባለቤት አቶ ሄኖክ እንደገለፁልን፣ እንዲህ ዓይነት ከሰዎች ባሻገር ለእንስሳት ጭምር አገልግሎት የሚሰጥበት ካፌ በምሥራቅ አፍሪካ ሲከፈት በዓይነቱ የመጀመሪያ ነው፡፡

ቦሌ አትላስ አካባቢ ለቤት እንስሳት ምግብና መገልገያ እቃዎችን በመሸጥ ሲሠሩ መቆየታቸውን ያነሱት አቶ ሄኖክ፣ አዲስ አበባ ይበልጥ ዘመናዊነትን እየተላበሰች መምጣቷን በመገንዘብ በአውሮፓና በተለያዩ ዓለማት ያዩትን

ወደ ገጽ 9 ዞሯል

# ተስፋ አብሳሪው የቡሄ ጨዋታ

**በአብርሃም ገብሬ**

ክረምት መግባቱን ተከትሎ ሰዎች የአኗኗር ዘይቤያቸውን በተወሰነ መልኩ መለወጥ ይጀምራል፡፡ በተለይ የሀምሌ እና የነሃሴ ወራት የመጀመሪያ ቀናት የዝናቡ መጠንከር፣ በሰዎች እንቅስቃሴ ላይ ገደብ ይጥላል፡፡ በዚህም ወንዞች ይሞላሉ፡፡ መሬቱ በጭቃ ተለውሶ፣ ጫማና ልብስ ላይ ለመመረግ ይንጠራራል፡፡ ሰማዩ የአህያ ሆድ መስሎ፣ ቁልቁል ሰዎችን ይታዘባል። በዚህ የክረምት ወቅት ተፈጥሮ ራሷ፣ ዝናብ እንደመታት ፍየል ኩርምት ብላ የተኛች ትመስላለች፡፡ የዚህ ሁሉ መነሻ የክረምቱ ድባብ ነው፡፡

ይሄ የጨፈገገው የተፈጥሮ ድባብ ግን ከቡሄ ዋዜማ አንስቶ፣ በጨላለመ ቤት ውስጥ እንደተለኮሰ ላምባ፣ የክረምቱ ጭጋግ እየተገፈፈ መሆኑን ምልክት ያሳያል፡፡ ተፈጥሮ ልምላሜዋና ጸአዳነቷን ታሳያለች፡፡ ለኢትዮጵያውያን ደግሞ አዳጊ ልጆች "ቡሄ ከዋለ የለም ክረምት..." እያሉና በየሰፈሩ እየተዘዋወሩ አዲስ ተስፋን ያበስራሉ፤ መልካም ምኞታቸውንም ይገልጻሉ፡፡

የልጆች የቡሄ ጨዋታ ተስፋን አብሳሪ ነው፡፡ የክረምቱን መገባደድና የአዲስ ዓመት መቃረብን በጨዋታቸው ይናገራሉ፡፡ በሌላ በኩል በህብረተሰቡ ውስጥ ቡሄ ሊጥ ተቦክቶ ሙልሙል ዳቦ የሚጋገርበት ወቅት ነው፡፡ ልጆች በዜማቸው አዲስ የብርሃን ተስፋ እየመጣ መሆኑን ያወሳሉ፡፡

እዚህ ቤት ያላችሁ እንደምን ናችሁ፣

በዓመት አንድ ቀን መጣንላችሁ...

ለቡሄ ሕፃናትና ወጣቶች፣ በቡድን በመሆን 'ቡሄ በሉ' እያሉ ከቤት ወደ ቤት እየተዘዋወሩ ይጨፍራሉ፡፡ በዘፈናቸውና በጭብጨባቸው ውስጥ የደስታ እና ተስፋ ስሜት አለ። ከልጆች ጭፈራ በተጨማሪ ሙልሙል ዳቦ የበዓሉ ሌላኛው ድምቀት ነው። ልጆችም እንዲህ እያሉ ይጨፍራሉ፤

ሆያ ሆዬ ሆ... ሆያ ሆዬ ሆ...

መጣና በዓመቱ

ኧረ እንደምን ሰነበቱ

ሆያ ሆዬ ሆ...

ሆያ ሆዬ ጌታ ጠንበለል

ዝናቡ መጣ ወዴት ልጠለል

አባብዬ ቤት እጠለላለው

ሙልሙል ዳቦዬን ይዤ እሄዳለው...

የቡሄ ጭፈራ የመዝናኛ እና የደስታ ክዋኔ ከመሆን ባለፈ፣ ጥልቅ የሆነ ማህበራዊ አንድምታ አለው። ጭፈራው ሰዎች እርስ በእርስ እንዲገናኙ፣ እንዲተዋወቁ እና ያላቸውን ልዩነት ወደ ጎን በመተው አብረው እንዲደሰቱ ያደርጋል። ልጆች ከማህበረሰባቸው ጋር ያላቸው ትስስር ከፍ እንዲል ይረዳል፡፡ ይህ ደግሞ በህብረተሰቡ ውስጥ ሰላምን፣ ፍቅርን እና መተሳሰብን ያሳድጋል። ጭፈራው የትውልድን እሴት ከአዲሱ ትውልድ ጋር በማገናኘት፣ ባህላዊ እሴቶች እንዲጠበቁ ያግዛል።



ፎቶ፡- ኤ አይ ቻት ጂፒቲ
የልጆች ጭፈራ እና የሙሉሙል ዳቦ ስጦታ ከቡሄ በዓል ክዋኔዎች መካከል ይጠቀሳሉ

የባህልና የኪነ ጥበብ ተመራማሪ ወሰን ባዩ (ዶ/ር)፣ የቡሄ ጨዋታና የክዋኔዎቹ አንድምታን በተመለከተ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት፣ ቡሄ በዋናነት የልጆች ጨዋታ ነው። ልጆች ልባቸው ንጹህ ነው፡፡ ቂም በቀል አያውቁም፡፡ አሁን ተጣልተው አሁን ይታረቃሉ፡፡ ፍቅራቸው እውነተኛ ነው፡፡ በቡሄ ዋዜማ በየሰፈሩ እየሄዱ የክረምቱን መገባደድ በዜማና ጭፈራ ማብሰራቸው ከዚህ ንጹህ ማንነታቸው ጋር ይተሳሰራል፡፡ ልጆች በቡሄ ጨዋታቸው በየደጃፉ ቆመው ለግለሰቡ መልካም ምኞታቸውን በሚገልጹበት ጊዜ፣ ማህበረሰቡም የልጆቹን ጨዋታ እንደተራ ነገር አያየውም፡፡ እንደ አዲስ ተስፋ አብሳሪ አድርጎ ነው የሚመለከተው፡፡ ከዚህ አንጻር የቡሄ ጨዋታና ክዋኔዎቹ ከማህበረሰቡ ህይወትና የወደፊት ተስፋ ጋር ጥብቅ ትስስር አላቸው ሲሉ አጫውተውናል፡፡

የቡሄ ጭፈራ የበዓሉን ትውፊት፣ መንፈሳዊነቱን እና ማህበራዊ እሴቱን አንድ ላይ አጣምሮ የያዘ፣ የደስታ፣ የፍቅር እና የትብብር ምልክት ነው፡፡ በቡሄ በዓል ላይ ጭፈራውን በማየት፣ በዓሉ የሰላምና የደስታ መገለጫ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

የቡሄ ዳቦ የሚሉት ሙልሙል

ኅበዝ ተሰብሰብ ቡሄ እንበል።

ሆያ ሆዬ ጉዴ... እየተባለ የሚጨፈረውም በዓሉ በአንድነት፣ በአብሮነትና በመተሳሰብ የሚከበር መሆኑን ለማመላከት ነው፡፡ የጅራፍ ድምጽ፣ ህብረ ዝማሬ፣ ምርቃትና ሙልሙል ስጦታ ቡሄን አጉልተው የሚያሳዩ ክዋኔዎች ናቸው፡፡

በተጨማሪም የሆያ ሆዬ ግጥሞች ከአካባቢ አካባቢ ሊለያዩ ይችላሉ። ሆኖም ዋናው መልዕክቱ በረከት፣ ፍቅርና አንድነት ላይ ያተኩራል። የቤቱን አባወራና እማወራ ማወደስና ማመስገንም የጭፈራው አካል ነው፡፡

ሰዋሰው ገጸ-ድር በ2015 ዓ.ም የቡሄ በዓል ትውፊትና አከባበርን አስመልክቶ በጻፈው ጹሁፍ ላይ እንደገለጸው፣ ልጆቹ ሆያ ሆየ በሚጨፍሩበት ወቅት ወደ ቤት የሚገቡት ሲፈቀድላቸው ብቻ ነው፡፡ ከዛም በሩ ተከፍቶ እንዲጨፍሩ ሲፈቀድላቸው የቤቱን ጌታና እመቤት በግጥምና በዜማቸው ማወደስና ማሞገሱን ይያያዙታል፡፡ የቤቱን አባወራ ከሚያወድሱባቸው ግጥሞች ውስጥ የሚከተሉትን ስንኞች መጥቀስ ይቻላል።

የኔ ጌታ የሰጠኝ ሙከት
ከግንባሩ ላይ አለው ምልክት

መስከረም ጠባ እሱን ሳነክት

በጌታዬ ቤት በጉልላቱ

ወርቅ ይፍሰስበት ባናት ባናቱ።

የኔማ ጌታ ጌታ ነው ጌታ

ሲቀመጥ ሲያምር ሲቆም ሲረታ።

የኔማ ጌታ የሰጠኝ ላም

አስር ዓመትዋ ኖረች በዓለም...... እያሉ ያወድሳሉ፡፡ በእርግጥ የሚወደሰው አባወራው ብቻ አይደለም፡፡ እመቤቲቱም በግጥምና በዜማ ይወደሳሉ፡፡ በዘፈናቸውና በጭፈራቸውም ቤት ውስጥ ያሉትን የቤተሰብ አባላት በመልካምነታቸው ያደንቃሉ፤ ያሞግሳሉ።

የኔማ እመቤት መጣንልሽ

የቤት ባልትና ልናይልሽ።

የኔማ እመቤት የጋገረችው

የንብ እንጀራ አስመሰለችው።

የኔማ እመቤት ብትሰራ ዶሮ

ሽታው ይጣራል ገመገም ዞሮ...፡፡

ልጆቹ ዘፈናቸውን አጠናቅቀው ከቤት ደጃፍ ላይ ሲደርሱ፣ የቤቱ አባወራዎችና እማወራዎች የሚያቀርቡላቸው ሽልማቶች አሉ። ዋናው ሽልማት ሙልሙል ዳቦ ነው። አሁን አሁን ግን፣ ሙልሙል ዳቦ የመስጠቱ ባህል በተለይ በከተሞች አካባቢ ቀስ በቀስ በገንዘብ እየተተካ መምጣቱን መታዘብ ይቻላል። ብዙ ጊዜ ልጆች ዘፈናቸውን ሲያጠናቅቁ፣ የቤቱ አባወራዎች የገንዘብ ስጦታ በማበርከት ያበረታቷቸዋል።

መጣና በአመቱ

እንደምን ሰነበቱ

ክፈት በለው ተነሳ

ይህን አንበሳ

ክፈት በለው በሩን

የጌታዬን

ሆያ ሆዬ ሆ....

እዚህ ቤቶች እንደምን ናችሁ

በአመት አንድ ቀን መጣንላችሁ

በአመት አንድ ጊዜ ለመጣ እንግዳ

ምሳው ሙክት ነው እራቱ ፍሪዳ

ሆያ ሆዬ ጉዴ

ጨዋታ ነው ልማዴ...

እንደ ወሰን (ዶ/ር) ገለጻ፣ ኢትዮጵያ የራሷ ባህል፣ ዕሴት፣ ወግ...አላት ሲባል እንደ ቡሄ ያሉ የልጆች ጨዋታዎችንም ያካትታል፡፡ ልጆች በየሰው ደጃፍ የቡሄ ዋዜማ ላይ ሲያዜሙና ሲጨፍሩ አንድ ኢትዮጵያዊ ቢመለከታቸው እንግዳ ስሜት አያድርበትም፡፡ ከዚያ ይልቅ ለልጆቹ ሽልማት በመስጠት ተመርቆ ይሄዳል፤ ልጆችም ሰጪውን ይመርቃሉ፤ መልካም ምኞታቸውን ይገልጹለታል፡፡ መሰል የቡሄ ክዋኔዎች ማህበረሰቡ በተለያየ አውድ ዘወትር የሚከውናቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- የምርቃት ባህል ኢትዮጵያውያንን በጋራ የሚያስተሳስራቸው ዕሴት ነው፡፡ አዛውንት ይመርቃል፣ ሴቶች ይመርቃሉ፣ ወጣቶች ይመርቃሉ፣ እንደዚሁም የቡሄ ጨዋታ የሚጫወቱ ልጆችም በዘፈናቸውና በጭፈራቸው አማካይነት በሌላ አውድ ሰጪውን ይመርቃሉ፡፡ ቀጣይ አመት ሳይለያየን ያድርሰን በማለት መልካሙን ሁሉ እንዲገጥማቸው ይመኛሉ፡፡ ከዚህ አንጻር የቡሄ ጨዋታና ክዋኔዎቹ የዚህ የማህበረሰቡ የባህል እሴት ነጸብራቅ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

የቡሄ በዓል፣ ከሃይማኖታዊ ክብረ በዓልነቱ በተጨማሪ፣ ኅብረተሰቡ ማህበራዊ ትስስርን የሚያጠናክርበት ትልቅ አጋጣሚ ነው። በበዓሉ ላይ፣ ጎረቤቶች፣ ቤተሰቦች እና ወጣቶች በጋራ በመሆን ደስታቸውን ያከብራሉ። ይህ ሁሉ የኅብረተሰብ ትስስር እንዲጠናከር ያደርጋል። ይህ በዓል ከነሐሴ ወር መምጣት ጋር ተያይዞ በልዩ ሁኔታ የሚከበር ሲሆን፣ በተለይም በገጠሩም ሆነ በከተማው አካባቢ የሚገኙ ህፃናትና ወጣቶች በጉጉት የሚጠብቁት ነው። የቡሄ በዓል ዋነኛ መገለጫ ከሆኑት ነገሮች አንዱ ደግሞ የሆያ ሆዬ ጭፈራ ሲሆን፣ በዓሉን የሚያደምቅና ትውፊቱን የሚያንጸባርቅ ልዩ ክዋኔ ነው።

በተጨማሪም ቡሄ የክረምቱ ዝናብ እየተጠናቀቀ ወደ ብርሃንና ሞቃታማው ዘመን መሸጋገሪያ በመሆኑ ልዩ ስሜት ይፈጥራል፡፡ በበዓሉ ዕለት የሚሰሙት የልጆች የሆያ ሆዬ ጭፈራዎች የጭጋጋማው የክረምት ወራት መጠናቀቅና ብርሃናማው መስከረም የመምጣቱ ማብሰሪያ ናቸው። ይህ ወቅት ተፈጥሮ ከለመለመችበት እና አዝመራው ከሚደርስበት ጊዜ ጋር በመገጣጠሙ ታላቅ ተስፋን እና ደስታን ይሰጣል።

ከዚህም በላይ ቡሄ የህብረተሰቡን አብሮነት፣ ፍቅርና አንድነት የሚያጠናክር ማህበራዊ እሴት አለው። ህጻናት በቡድን ሆነው ቤቶችን እየዞሩ የሚዘምሩት መዝሙር እና የሚሰጣቸው ስጦታ (ዳቦ ወይም ገንዘብ) በትውልዶች መካከል ያለውን ትስስር ያጠናክራል።

በአጠቃላይ ቡሄ የባህላዊ እሴቶች መገለጫ ሆኖ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲሻገር የቆየ ሀገራዊ ሃብት ነው። የክረምቱን ማለፍ ከማብሰሩም በላይ የኢትዮጵያን ህዝቦች አንድነት፣ ተስፋ፣ መተሳሰብ እና የጋራ ደስታን የሚገልጽ ድንቅ ትዕይንት ነው።

በአቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት ደቻሳ ለሜሳ ኦቾ (ዶ/ር) ስም የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000080208398 የሴሪ ቁጥሩ R -0109789 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 02 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋ በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ተለዋጭ ሰርተፊኬት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ**
**የን/ስ/ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በአቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት ደቻሳ ለሜሳ ኦቾ (ዶ/ር) ስም የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000080208996 የሴሪ ቁጥሩ L -0101658 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 02 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋ በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ተለዋጭ ሰርተፊኬት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ**
**የን/ስ/ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ በቀድሞ ወረዳ 20 ቀበሌ 52 በአዲሱ ወረዳ 06 ቤት ቁጥር --- በካርታ ቁጥር 735/ፐማ/1900/822493/01 ለአቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት/እነ ሁሴን ሣሊያ አደም ተሰጥቷቸው የነበረው ካርታ የጠፋ ስለሆነ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ድረስ አቤቱታ እንዲያቀርብ፡፡ ይዤዋለሁ የሚል ከሌለ ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማት**
**አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

እነ ባቱ ድሪባ ቡልቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 ቦሌ8/14/6/3/4593/00 ሴሪ ቁጥር 027064 የሆነው ይዞታ የቤት ባለቤት ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ**
**የቦሌ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000060502540071107 ሴሪ ቁጥር - 175119 በኪሩቤል ዋለልኝ ከበደ ስም በተቋማችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን እስከ 30 ቀን ድረስ በጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ /ሰርተፊኬት/ እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ**
**የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ታደሰ ማሞ ወልደስላሴ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 06 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000060604332 የሚገኘው የጋራ መኖሪያ ቤት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት /ካርታ ሴሪ ቁ L 0110566 የሆነው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ /የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት / ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ**
**የቦሌ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ዶክተር በየነ ዶዕልቾ ሐስሶ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ካርታ ቁጥር ቦሌ12/243/35-1299/00 ሴሪ ቁጥር 043959 የሆነው ይዞታ የቤት ባለቤት ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ**
**የቦሌ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

አመልካቾች ወ/ሮ ፍሬህይወት ቀነኒ በቀን 5/12/2018 ዓ.ም የተፃፈ ማመልከቻ በካርታ ቁጥር የካ/204004/09 የሴሪ ቁጥር 0118320 የተመዘገበ ኦርጂናል ካርታ የጠፋብኛ በመሆኑ ይሄው ተገልፆ ምትክ እንዳገኝ ለሚመለከተው አካል ደብዳቤ ይፃፍልኝ በማለት በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ አስይዥዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤታችን እንዲያሳውቁ እያልን በጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኃላ ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና**
**አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሪት ፀሀይ ወልዴ ገብረማርያም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 09 ክልል ውስጥ የሚገኘው ይዞታ ካርታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ 034439 የሴሪ ቁጥር 133345 የይዞታ ስፋት 66.56 ካ.ሜ የሆነ በማህደር ውስጥ መገኘት የነበረበት ካርታ ኮፒ የጠፋባቸው በመሆኑ ወጪውን ግለሰቡ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅ እየገለፅን በማንኛውም ምክንያት የጠፋው ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ እስከ 30 ተከታታይ የስራ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ፅ/ቤት እንዲያቀርቡ በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና**
**አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቶ /ወ/ሮ/ወ/ሪት መንሱር ሰኢድ ስም የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000080205819 የሴሪ ቁጥሩ L 053591 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 02 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋ በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ተለዋጭ ሰርተፊኬት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ**
**ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

**ጉዳዩ፡- የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳቅ ይመለከታል**

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ወረዳ 08 በ ዲ.ኤ.ቲ.ዲ ፋሚሊ ሪልእስቴት እና ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ ማህበር ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር የካ/15207/13 እና በቀን 22/07/2013 ዓ.ም የተሰጠ ካርታ መጥፋቱን ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑ የይዞታ ካርታ በጋዜጣ 30 ቀን ውስጥ መብት አለኝ የሚል እና ካርታው መጥፋቱን ግለሰቡ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬትና ምዝገባ መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ማስታወቂያ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን ያገኘው አካል ካለ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባ መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲያሳውቅ እየገለጽን ይህ ባይሆን ለአመልካቹ አዲስ ካርታ ወጪ ተደርጎ የሚሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፤

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ**
**የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

## የውበትና... ከገጽ 7 የዞረ

ተሞክሮ ወደ ከተማዋ አምጥተዋል፡፡ የከተማ አስተዳደሩም ያቀረቡትን ጥያቄ በመቀበል በወንዝ ዳርቻው የሚሰሩበት ቦታ ስላመቻቸላቸው ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡ ወደ ሥራው በተሟላ አቅም ሲገቡ በምግብ ዝግጅትና መስተንግዶ፣ ለቤት እንስሳት ሕክምና፣ እንስሳትን በማጠብ እና ለእነሱ የሚሆኑ ቁሳቁሶችን በመሸጥ ስራ ላይ ለሚሰማሩ 15 ሰዎች የሥራ ዕድል እንደሚፈጥሩ ጠቁመዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮሪደርና ወንዝ ዳርቻ ልማት አስተዳደር ባለሥልጣን አቶ ከድር አደም ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት፤ ቀደም ሲል የከተማዋ ወንዞች ተፈጥሯዊ ወዛቸውን አጥተው ነበር። ከየመኖሪያ ቤቱና ከፋብሪካዎች በሚወጣ ቆሻሻ የተሞሉ፣ የሞቱ እንስሳት ሳይቀር የሚጣልባቸው፣ ሕገ ወጥ ግንባታዎች የተስፋፉባቸው፣ የበሽታና የቆሻሻ ማከማቻ ከመሆናቸውም በላይ የወንጀለኞች መሸሸጊያ ነበሩ።

ወንዞችን ከብክለት ለመታደግ፣ የጎርፍ አደጋ ስጋትን ለማስወገድ፣ ከተማዋን ለነዋሪዎችና ጎብኚዎች ምቹ የማድረግ ዓላማን በመያዝ በተጀመረው የወንዝ ዳርቻ ልማት ያ ጎስቋላ የነበረው ገፅታ ዛሬ ተቀይሯል፡፡ ወደ ወንዞች ቆሻሻ እንዳይገባ የፍሳሽ መስመሮችን የመዘርጋት ስራ በተሳካ ሁኔታ ተከናውኗል። ከዚህም ባሻገር፤ ውብ የአስፋልት፣ የእግረኛና የብስክሌት መንገዶች፣ ድልድዮችና ግድቦች ተገንብተዋል። እንደ መኪና ማቆሚያ፣ የህጻናት መጫወቻ፣ ካፌዎች፣ ሱቆች፣ ሞሎችና ዘመናዊ የህዝብ መፀዳጃ ቤቶች ያሉ አጠቃላይ መሰረተ ልማቶች በመሟላታቸው፤ ቀደሞ የተረሱት የወንዝ ዳርቻዎች ዛሬ የከተማዋ የውበትና የህይወት ማዕከል መሆን እንደቻሉ አቶ ከድር ያስረዳሉ፡፡

ከዚህ ባሻገር የወንዝ ዳርቻ ልማቱ በግንባታ ወቅትና ወደ አገልግሎት ሲገቡ ለበርካታ ወገኖች የሥራ ዕድል ፈጥረዋል። አቶ ከደር እንደገለፁት፣ በኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ሥራ ከ230 ሺህ በላይ ዜጎች በጊዜያዊነትና በቋሚነት የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል። የሚተከሉ ሳሮችን በማቅረብ፣ መልክአ ምድሩን በማስተካከል፣ ሳርና አበባ በመትከልና በመንከባከብ፣ የግንባታ እቃዎችን በማቅረብና በመገንባት፣ በካፍቴሪያዎች፣ በተለያዩ የንግድ ሱቆች፣ በአስጎብኚነት፣ ፎቶ ግራፍ በማንሳት፣ በጥበቃ፣ በፅዳት እና በሌሎች መስኮች የስራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል፡፡

ከዚህ ባሻገር የሥራ ባህል እንዲቀየር ማድረጉንም አቶ ከድር ያነሳሉ። ነጋዴው፣ ሠራተኛው፣ ተቋራጩ፣ አማካሪው፣ አመራሩና ምርት አቅራቢው በሳምንት ሰባት ቀን፤ በቀን ብቻ ሳይሆን በሌሊትም ጭምር እየሠሩ ይገኛሉ፡፡ ይህ ለወደፊት ለሚከናወኑ ሥራዎች ትልቅ አቅም የሚሆን ወሳኝ ለውጥ ነው።

በቅንጅት የመሥራት ልምድ ሌላው ከወንዝ ዳርቻ ልማት የተገኘ ትልቅ ተሞክሮ ነው። ከዚህ ቀደም አራት ተቋራጮች የሚሠሩት ሥራ በአንድ ተቋራጭ እየተሰራ ይገኛል። ይህም የሆነው የመሠረተ ልማት ገንቢ ተቋማት (የመንገድ፣ መብራት፣ ውሃና ፍሳሽ፣ ግንባታ፣ ትራንስፖርት እና ቴሌኮሙኒኬሽን) በቅንጅት በመሥራታቸው ነው፡፡ ከዚህ ቀደም አንዱ የሠራውን ሌላው የሚቆፍርበትንና የሚያፈርስበትን ሁኔታ አስቀርቶ በአንድ ጊዜ መሥራት የሚቻልበትን ሁኔታ በመፍጠር ምርታማነትን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ ተችሏል፡፡

የአዲስ አበባ የወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክት፤ ከተማዋን ከብክለት፣ ከደህንነት ስጋትና ከቆሻሻ ማከማቻነት ወደ ተዋበችና ዘመናዊ የቱሪስት መዳረሻነት ያሻገረ ታላቅ ስራ ነው። ይህ ሁለገብ ልማት የአካባቢ ጥበቃን እና የከተማ ውበትን ከማረጋገጡ ባሻገር፣ እንደ ወይዘሮ ደስታ እና ማርታ ላሉ በርካታ ዜጎች የሥራ እድል እንዲፈጠርላቸው አድርጓል፡፡ ከጽዳትና ጥበቃ ጀምሮ በወንዝ ዳርቻው ባሉ አገልግሎቶች የተፈጠረው የስራ ዕድል ፕሮጀክቱ የከተማዋን ኢኮኖሚ በማነቃቃት የሚጫወተው ሚናም ከፍተኛ ነው፡፡

# የኪነ ጥበብ ድግሶች




ፎቶ- ከገፀ ድር
ከኪነ ጥበብ ዝግጅቶቹ በከፊል

**በጊዜው አማረ**

በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል። ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል መሰናዶዎች ይቀርባሉ፡፡ ከእነዚህ የመጽሐፍት ምረቃ፣ የኪነ ጥበብ አውደ ርዕይ እና የቴአትር መርሃ ግብር ይገኙበታል፡፡ ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

## መጽሐፍት

“ቡናዬ እስኪሰክን” የተሰኘው መጽሐፍ ዛሬ ይመረቃል፡፡ የደራሲ ቤተማርያም ተሾመ የድርሰት ስራ የሆነው አዲስ መጽሐፍ ዛሬ ከሰዓት 8:30 ሰዓት ጀምሮ አራት ኪሎ በሚገኘው ዋልያ መጻሕፍት መደብር ይመረቃል፡፡

በተጨማሪም “የአምራችነት ሰብዕና፤ ቅድመ-ተግባር ማንነት” የተሰኘ አዲስ መጽሐፍ ለንባብ በቃ። መጽሐፉ አንድ ግለሰብ የኢትዮጵያን ታሪክ፣ የኢኮኖሚ ጸባይ፣ ባህል እና ማህበራዊ እሴቶች መነሻ አድርጎ የአምራችነት ሰብዕናውን በመገንባት እንዴት ውጤታማ የቢዝነስ ሰው መሆን እንደሚችል የሚያስገነዝብ ነው፡፡

“የአምራችነት ሰብዕና፤ ቅድመ-ተግባር ማንነት” የተሰኘው ይህ አዲስ መጽሐፍ 52 ምዕራፎች እና 426 ገጾች አሉት። የመጽሐፉ አዘጋጅ አቶ ስንታየሁ ኪዳኔ የታሪክና ባህል ተመራማሪ ሲሆኑ በመምህርነት፣ በልማት ፕሮጀክቶችና የማህበረሰብ ጉዳይ አማካሪነት የረጅም ዓመት ልምድ አላቸው፡፡

በተጨማሪም “የዕድሜ ደመራ” መጽሐፍ ተመርቆ ለንባብ በቅቷል፡፡ የደራሲ ውድአላት ገዳሙ ስራ የሆነው ይህ መጽሐፍ ቀደም ሲል እየተለመደ በመጣው የቅድመ ግዥ (Pre-order) ቻሌንጅ ለሽያጭ ቀርቦ እንደነበረ ይታወሳል፡፡ መጽሐፉ በመጪው የጷጉሜን ወር በዓድዋ ድል መታሰቢያ ይካሄዳል።

## የኬክ አውደ ርዕይ

3ኛው “አዲስ ኬክ እና ቤክ ኤክስፖ” በመጪው ሳምንት ይካሄዳል። በኤክስፖው ላይ ታዋቂ ካፌዎች፣ ዳቦ ቤት እና ኬክ ቤቶች እንዲሁም የኬክ ጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች ይሳተፋሉ። በተጨማሪም የተለያዩ ባለሙያዎች፣ ሼፎች ስለ ኬክ አሰራር እና የዘርፉን አዳዲስ ነገሮች ትምህርት እና ልምድ እንደሚሰጡ የኤቨንት አዲስ መረጃ ያሳያል፡፡ እንዲሁም የተለያዩ ጌሞች፣ የሼፎች ውድድሮች እና ለታዳሚዎች የተለያዩ አዝናኝ እና አስተማሪ ውድድሮች የተዘጋጁ ሲሆን መርሃ ግብሩ ከነሐሴ 15 እስከ ነሐሴ 17 ቀን 2018 ዓ.ም በአዲስ ኢንተርናሽናል ኮንቬንሽን ሴንተር ይካሄዳል። መግቢያው በነፃ በመሆኑ ታዳሚዎች ይህን ኩነት እንዲታደሙ ጥሪ ቀርቧል ፡፡

## የስዕል አውደ ርዕይ

“የሚጤሰው ጠረጴዛ” (The Smoking table) የተሰኘው የስዕል አውደ ርዕይ በዛሬው እለት ለእይታ ይበቃል፡፡ ይህ የስዕል አውደ ርዕይ አፍሪካን ለመቀራመት የተደረገው የበርሊኑን ጉባኤና ተያያዥ ጉዳዮች በጥልቅ ጥበብ የተንጸባረቀበት ነው፡፡ አውደ ርዕይው በዛሬው ዕለት ከቀኑ 9:00 ሰዓት በዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚዬም ለእይታ ይበቃል፡፡

## ሙዚቃ

አዲስ የኢትዮ ጃዝ አልበም ወደ አድማጭ ተመልካች ደረሰ፡፡ “ምስክር” የተሠኘው ይህ አዲስ የሙዚቃ አልበም ትናንት ማታ በናሆም ሬከርድስ አማካኝነት ወደ ህዝብ ደርሷል፡፡ ይህ ስራ በቴዎድሮስ አምዴ በደብል ቤዝ ድራም የተሠሩ 18 የኢትዮ ጃዝ ሙዚቃዎች የያዘ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

ለጥናት እና ዝግጅት በአጠቃላይ 16 ዓመታትን በፈጀው፣ ለሃገራችንም አዲስ በሆነው በዚህ ኦሪጅናል የጃዝ ሙዚቃ አልበም ላይ ከቴዎድሮስ በተጨማሪ በቤዝ ጊታር ዮሐንስ ጦና፣ አብይ ሠለሞን፣ ሄኖክ ተመስገን፣ ዳግማዊ አሊ እና በአጠቃላይ 8 ምርጥ የቤዝ ተጫዋቾች ተሳትፈዋል። የሙዚቃ ባለሙያ ቴዎድሮስ የደብል ቤዝ ድራም አጨዋወትን ያለአስተማሪ የሚያስተምር ባለ 218 ገጽ መጽሐፍም አዘጋጅቶ ለሙዚቃ አፍቃሪያን ማቅረቡ ይታወቃል፡፡

## የቴአትር መርሃ-ግብር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ።

በብሄራዊ ቴአትር ቤት ቅዳሜ 8፡00 ሰዓት “12ቱ እንግዶች” እንዲሁም በ12:00 ሰዓት “በር የሌለው ቤት” ቴአትሮች ይታያሉ፡፡ እሁድ ደግሞ በ8፡00 ሰዓት “ንጉስ አርማሕ” እንዲሁም በ12፡00 ሰዓት ደግሞ “እምዩ ብረቷ” ይታያሉ። ተመልካቾችም ጊዜያቸውን ለመቆጠብ የ“ሁሉ በጄ” መተግበሪያን በመጠቀም ትኬቶችን አስቀድመው መግዛት እንደሚችሉ ተገልጿል።

በአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ ደግሞ “እሳት ወይ አበባ” ዘወትር ቅዳሜ በ11፡00 እንዲሁም “ባልቻ አባነፍሶ” ቴአትር እሁድ በ8:00 ሰዓት የሚታዩ ሲሆን ትኬቱን በኦንላይን የክፍያ ስርዓት መቁረጥ እንደሚቻል ተጠቁሟል፡፡

ቦሌ ፍላሚንጎ በህፃናትና ወጣቶች የቴአትርና ሲኒማ ኮምፕሌክስ ቅዳሜ ጠዋት 4፡00 ሰዓት “አዮ ቦራ” የተሰኘው የአፋን ኦሮሞ ቴያትር ይታያል፡፡ እሁድ ጠዋት 4፡00 ሰዓት ደግሞ “የንባብ ከተማ” የተሰኘው አዲስ ቴአትር ለእይታ ይበቃል፡፡ እሁድ በ8፡00 ሰዓት በቅርቡ ወደ መድረክ የመጣው “ወህኒ አምባ” ቴአትር እንዲሁም 11፡30 ደግሞ “አትጥሪኝ” የተሰኙ ቴአትሮች ለተመልካች ይደርሳሉ፡፡

እንዲሁም በሀገር ፍቅር ቴአትር ረቡዕ በ11፡00 ሰዓት “አሉ” የተሰኘው አዲስ ቴአትር፣ ሐሙስ 11፡30 “ነገሩ አይቆምም”፣ እሁድ በ8፡00 ሰዓት “ሰዴታ” (በአፋን ኦሮሞ) እና በ12፡00 ሰዓት “የመጨረሻው ፍርድ” ለቴአትር አፍቃሪያን ይቀርባሉ፡፡

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር። የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ ከላይ የሚገኘው የመጀመሪያው 5+6=11፣ ቀጥሎ ወደ ቀኝ 6+2=8፣ ሶስተኛ ዙር ላይ የሚገኘው 2+8=10 እያለ ይቀጥላል፡፡ በዚህ ስሌት መሰረት የጥያቄ ምልክቱ የሚገኝበት 9+5=**14** ይሆናል፡፡ ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ የሚገባው ትክክለኛ ቁጥር 14 ነው፡፡




## የዛሬው የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# ፍቅር፣ ይቅርታና አብሮነት በወጣቱ ብዕር

**በጊዜው አማረ**

ወጣትነት ልዩ እና የእምቅ አቅም ባለቤት የሚሆንበት ጊዜ ነው። ምክንያቱም አንድ ማህበረሰብ ከትውልድ ትውልድ የሚያስተላልፈውን እሴት፣ ባህል እና የዕውቀት ቅብብሎሽ የሚያረጋግጠው በወጣቶች ትምህርት፣ ጉልበትና አዕምሮ ነው። ይህ የዕድሜ ክልል በአዲስ ሃይል፣ በፈጠራ ክህሎት እና በማህበራዊ ለውጥ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ግንባር ቀደም ሚና የሚወጡበትም ነው። ምክንያቱም ወጣቶች ለሀገራቸው ሁለተናዊ እድገት የማይተካ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ።

ይህ የዕድሜ ክልል የይቅርታ፣ የተስፋ፣ የልማትና አብሮነት ምንጭም ነው። ወጣትነት የልዩነቶችን ድንበር በማለፍ በጋራ መግባባት እና በአብሮነት ላይ የተመሰረተ ማህበረሰብና ሀገር ለመገንባት ትልቅ አቅም አለው። ያለፉትን ስህተቶች በመማሪያነት በመውሰድ እና ይቅርባይነትን በማሳየት አዲስ ምዕራፍ የመክፈት አቅም ያለው በወጣቱ ትውልድ ውስጥ ነው። የይቅርታ ባህል ባለበት ማህበረሰብ ውስጥ ሰላም እና መረጋጋት ይሰፍናል፤ ይህም ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

በተጨማሪም ወጣትነት የሀገር እውነተኛ ጸጋ እና የሉዓላዊነት ዋስትና ነው። ሀብት የሚለካው በቁሳቁስ ብቻ ሳይሆን የሰዎች አዕምሯዊ እና ሞራላዊ ልዕልና በሚፈጥረው እሴት ጭምር ነው። ወጣቶች በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በኪነ ጥበብ እና በሌሎችም ዘርፎች የሚያስመዘግቡት ስኬት የሀገራቸውን ገጽታ ከፍ የሚያደርግ ነው። ይህንን በዋጋ የማይተመን ጸጋ በአግባቡ መያዝ እና ማልማት ደግሞ ለመጪው ትውልድ የሚተርፍ ትልቅ ፋይዳ ያለው ስራ ነው።

ይሁን እንጂ ይህ እምቅ አቅም ወደ መሬት ወርዶ ውጤት እንዲያመጣ ማድረግ የሚቻለው ተገቢውን ትኩረት እና ዕድል ለወጣቶች ሲሰጥ ብቻ ነው። ምክንያቱም ወጣትነት የነገውን ህልም እውን የሚያደርግ የለውጥ ሞተር ነው። ይህንን ህልም እውን ለማድረግ ወጣቶች በቁርጠኝነት፣ በስነ-ምግባር እና በሀገር ፍቅር ስሜት ሊንቀሳቀሱ ይገባል፤ መንግስት እና ህብረተሰቡም አብረዋቸው ሊቆሙ ይገባል። ተስፋ የሞላበት እና የዳበረ አዕምሮ ያለው ወጣት ሲኖር የሀገር የወደፊት እጣ ፈንታ አስተማማኝ እና ብሩህ ይሆናል ይላል ፒስ ኮርፕስ በተሰኘ ገጸ-ድር ላይ "Youth for Devlopment" በሚል ርእስ የሰፈረው ፅሁፍ።

ይህን መሰረት በማድረግ በየዓመቱ በነሃሴ ወር የዓለም የወጣቶች ቀን ይከበራል፡፡ አላማው ወጣቶች ስለ ሰላም፣ ፍቅር፣ መቻቻል እና የጋራ የወደፊት እጣ ፈንታ እንዲወያዩ ወሳኝ መድረክ ለመፍጠር ነው፡፡

በተጨማሪም ይህ ቀን ወጣቶች በማህበራዊ ልማት፣ በሰላም ግንባታ እና በበጎ አድራጎት ስራዎች ላይ ያላቸውን ንቁ ተሳትፎ እውቅና ለመስጠት፣ ወቅታዊ ችግሮችን በፈጠራ ሃሳብና በትብብር




ፎቶ- ከገፀ ድር
የፍቃዱ አስራት "የህላዌ ዘለሰኛ" የተሰኘው የግጥም መድብል

እንዲፈቱ ለማነሳሳት የሚከበር ነው። የአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍልም ይህን መነሻ በማድረግ ስለፍቅር፣ ሰላም፣ አንድነት፣ ይቅርታና ተስፋ የሚያወሱ የወጣቱ ገጣሚ ፍቃዱ አስራት ስራዎች ላይ አጭር ዳሰሳ አድርጓል፡፡

የኢትዮጵያ ወጣቶች በሀገራቸው ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ከትውልድ ትውልድ ጉልህ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ። ከሰላምና ልማት ስራዎች በተጨማሪ በኪነ-ጥበብ መስክ፣ በድርሰት እና በግጥም ስራዎች አማካኝነት የህብረተሰቡን ማንነት በመቅረጽ፣ ባህልን በማዳበር እና አዎንታዊ ለውጦችን በማምጣት ረገድ የፊት ተሰላፊዎች ናቸው። ወጣቱ ትውልድ በስነ-ጽሁፍ ስራዎቹ ሃሳቡን በመግለጽ እና የሀገርን አንድነትና ሰላም በመስበክ ረገድ የማይተካ ሚና ተጫውቷል፤ እየተጫወተም ይገኛል፡፡

በግጥም እና በድርሰት ስራዎች አማካኝነት ወጣቶች የዘመኑን መልኮች፣ ተስፋዎች እና ህልሞች በብቃት አንጸባርቀዋል። ከዚህም ባለፈ ወጣቱ ትውልድ አዳዲስ የቋንቋ አጠቃቀም ዘይቤዎችን እና ሀሳቦችን በማስተዋወቅ የኢትዮጵያን ስነ-ጽሁፍ ከትውልድ ወደ ትውልድ በማሸጋገር ላይ ይገኛል።

ከእነዚህ ወጣት ደራሲያን መካከል "የህላዌ ዘለሰኛ" የተሰኘ የግጥም መድብል ያስነበበው ፍቃዱ አስራት ይገኝበታል። መጽሐፉ በበርካታ ሃያሲያን ዘንድ አድናቆትን አግኝቷል፡፡ ይዘቱም ፍቅር፣ ተስፋ፣ ይቅርታና አጠቃላይ የሰው ልጆችን ኑረትና ህይወት የሚያትት ነው፡፡

ትኖሪያለሽና

በሌላ መገለጥ በእፎታ ግርግም

ብርሃን ባለበት ጥላ ከቶ አይቅርም

ታውቂዋለሽና

የመተከዝና የጽሞናን አቅም

አልልም አልልም

ሞቶ መነሳት ነው የፍቅራችን ድምድም... በማለት የሰው ልጆች ሕይወት ከደስታና ከብርሃን ጎን ለጎን የፈተናን ጥላ አብሮ የሚሸከም ነው የሚለው ገጣሚው፣ ይሁን እንጂ የጽሞናንና የመተከዝን አቅም ጠንቅቆ የሚያውቅ ልብ፣ ከድካም በኋላ እፎታን ማግኘቱ የማይቀር መሆኑን ይነግረናል። በግጥሙ ውስጥ እንደተገለጸው፣ ብርሃን ባለበት ስፍራ ጥላ አብሮ እንደሚኖር ሁሉ፣ በሕይወት ጉዞ ውስጥ የሚገጥሙ ውጣ ውረዶች የኑሮ ተፈጥሯዊ ከፍታና ዝቅታዎች ናቸው።

ይህ እውነታ በማህበረሰብ ግንኙነትና በፍቅር ዓለም ውስጥም ፍጹም እውነት ነው። ፍቅርና አብሮነት ፈተናዎች ሲገጥሙት የሚፈርስ ሳይሆን፣ ከችግር በኋላ በመጠናከር የሚቀጥል የሕይወት ጎዳና ነው። በመሆኑም የፍቅር እውነተኛ ከፍታና መደምደሚያው ከውድቀት ተነስተው በጋራ አዲስ ተስፋን ማብራት መቻሉ ላይ የተመሰረተ ነው ይለናል፤ ወጣቱ ደራሲ።

የገጣሚ ፍቃዱ አስራት የግጥም ስራዎች እና ሀሳቦች በዋናነት ሰብአዊነትን፣ ሰላምን እና ህብረተሰባዊ ትስስርን የሚያጠናክሩ ጉዳዮች ላይ ያተኩራሉ። በተለይም በገጽ 11 ላይ የሰፈረው ሃሳብ ሀገር፣ ወጣት፣ ህዝብ እና አጠቃላይ ማህበረሰቡ ያለፉ ስህተቶችን በይቅርታ ማለፍ እንደሚገባቸው ያነሳል። ባለፉት ጊዜያት የተፈጸሙ በደሎችን እና ስህተቶችን ይዞ መጓዝ ማህበረሰባዊ እድገትን ወደ ኋላ የሚጎትት በመሆኑ፣ ይቅር መባባል ማህበራዊ መሰረት ሊሆን ይገባል የሚል ሃሳብ ያንጸባርቃል።

በእርግጥም በቀል እና የጥላቻ ትርክት ለየትኛውም ማህበረሰብ ከጉዳት ውጪ የሚያስገኘው ፋይዳ የለም። ገጣሚው እንደሚለው ህዝብ እና ሀገር ወደፊት ለመቀጠል የይቅርታን ድልድይ መጠቀም አለባቸው እንጂ፣ በደሎችን እየቆጠሩና ቁርሾን እያራገቡ የትም መድረስ አይቻልም። ይቅርታ ማድረግ ድክመት ሳይሆን የሰለጠነ ማህበረሰብ መገለጫ እና ትልቅ ጥንካሬ ነው። ማህበረሰቡ ሰላም አግኝቶ ወደ ልማት ፊቱን እንዲያዞር እና ወጣቱ ጉልበቱን ለልማትና ለእውቀት እንዲያስተላልፍ የይቅርታ ባህል አስፈላጊ ነው። ገጣሚው ፍቃዱ አስራት እንዳስቀመጠው፣ የቀድሞ ስህተቶችን በይቅርታ መሻገር አእምሮን ነጻ የሚያወጣ እና ለነገ የተሻለ ተስፋን የሚሰጥ ነው። በውጤቱም፣ ጥላቻን አስወግዶ በይቅርታ ላይ የተመሰረተ ህብረት መፍጠር ዘላቂ ሰላም እና አብሮነትን ለማረጋገጥ ቁልፍ መፍትሄ ነው። ለአብነትም ጥቂት ስንኞችን እንቀንጭብ፡-

ከህሊናህ ጓዳ፣ ለቆለልኸው በቀል

በይቅርታ ተግሳጽ በድህነት ጸበል

ደግመህ ደጋግመህ ደግመህ ተጸበል...።

ገጣሚው ፍቃዱ አስራት በሌሎች የመጽሐፉ ገጾች ላይ የምህረት፣ የይቅርታ እና የፍቅርን እሴቶች በተደጋጋሚ በማንሳት ለአንባቢያን ጠቃሚ መልእክቶችን አስተላልፏል። ማህበረሰብም ሆነ ግለሰብ በየዕለቱ ከሚያጋጥመው አለመግባባት እና ቂም በቀል ራሱን ነጻ አውጥቶ በምህረት መርህ እንዲመራ ያሳስባል። ይቅርታ ሰውን ነጻ የሚያወጣ እና የሕይወት ጎዳናን የሚያቀል ታላቅ ሃይል መሆኑን በስራዎቹ ላይ በግልጽ ያሳያል።

ፍቅር የትዳርም ሆነ የማህበራዊ ትስስር ማዕከል በመሆን ጥላቻንና መከፋፈልን ለማስወገድ ወሳኝ ሚና አለው። ገጣሚው ፍቅርን ከመንፈሳዊ እና ከሞራል አንጻር በመመልከት፣ ሰው ከጥርጣሬና ከቁርሾ ፋንታ በፍቅርና በመተሳሰብ እንዲኖር ይመኛል። የጠላትነትን ግድግዳ በማፍረስ አብሮነትን ማጠናከር የሚቻለው ፍቅርን በልብ ውስጥ ሲያነግስ ብቻ መሆኑን የግጥም ስንኞቹ በግልጽ ያሳያሉ።

.....ይቅር

በምህረት ብረር

ለፍቅራችን ስመር

አለ ያኔ

የህላዌ ወኔ

ወደ ሰላም መስረግ ወደ ውስጥ ምናኔ....፡፡

ከላይ የተጠቀሱት የገጣሚው ስንኞች መልዕክት ለመጪው ትውልድ የሚተላለፉ ትልልቅ የሞራል እሴቶች ናቸው። ወጣቱ ትውልድ ያለፉትን ስህተቶች በመማሪያነት መውሰድ እንጂ፣ በቂም በቀል ተጠምዶ የወደፊት እድሉን እንዳያበላሽ ያስጠነቅቃሉ። በምህረት፣ በይቅርታ እና በፍቅር ላይ የተገነባ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

ኢኮኖሚ

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# አንድ ብርጭቆ ወተት ዋጋው ስንት ነው?

**በይግለጡ ጓዴ**

ወተት ብርጭቆ ውስጥ የሚታይ ነጭ ፈሳሽ ብቻ አይደለም፤ የሕፃናት እድገት፣ የቤተሰብ ጤና፣ የአምራቹ የገቢ ምንጭ እና የሀገር ኢኮኖሚ የሚገናኙበት ዋና የምግብ ሰንሰለት ነው። ወተት ጥራት ያለው ፕሮቲን፣ ካልሲየምና ሌሎች አስፈላጊ የምግብ ንጥረ ነገሮችን በመያዙ ለአጥንትና ለጡንቻ ዕድገት ወሳኝ ድርሻ እንዳለው የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ።

"በመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት የእናት ጡት ወተት ዋና ምግብ ነው" የሚለው ሳይንሳዊ ሀቅ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከዚያ በኋላ ለልጆች ዕድገት ደህንነቱ የተጠበቀ ተጨማሪ ምግብ አስፈላጊ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ደግሞ የላም ወተት ከፍ ያለ ድርሻ አለው። ታዲያ ወሳኙ ጥያቄ "ወተት አለ?" ሳይሆን "ምን ያህል ጥራት ያለው ወተት አለ?" የሚለው ነው።

የወተት ደህንነት ከላሟ ጤናና ከአመጋገብ ጥራት ይጀምራል። ጥሩ መኖ፣ ንጹህ ውሃ፣ የእንስሳት ጤና ክትትልና የተመጣጠነ ምግብ የጥሩ ወተት መሠረቶች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ የጡት ንጽህና፣ የማለቢያ ዕቃዎችና የሠራተኛ ንጽህና፣ ፈጣን ማቀዝቀዣ፣ ንጹህ መጓጓዣና ትክክለኛ ማከማቻ የወተት ጥራት ወሳኝ መለኪያዎች ናቸው።

የተባበሩት መንግሥታት የምግብና ግብርና ድርጅት (FAO) እ.ኤ.አ. በ2023 ባወጣው መረጃ መሠረት ጥሬ ወተት ከታለበ በኋላ በፍጥነት ወደ ዘመናዊ ማቀዝቀዣ ማስገባት የመጀመሪያውን ጥራት ለመጠበቅ ወሳኝ ነው። ይህም ባክቴሪያ እንዳይበዛ፣ ወተቱ ቶሎ እንዳይበላሽና አሲዳማ እንዳይሆን፣ የተፈጥሮ ሽታው፣ ጣዕሙና መልኩ እንዳይቀየር ያግዛል።

ዋና መቀመጫውን በኬንያ ናይሮቢ ያደረገው ዓለም አቀፉ የእንስሳት ሀብት ምርምር ተቋም "Ethiopia National Dairy Development Strategy 2022–2031" በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ. ታህሳስ 2023 ይፋ ባደረገው መረጃ ኢትዮጵያ 70 ነጥብ 3 ሚሊዮን ከብቶች፣ 42 ነጥብ 9 ሚሊዮን በጎች፣ 52 ነጥብ 5 ሚሊዮን ፍየሎች እና 8 ነጥብ 1 ሚሊዮን ግመሎች እንዳሏት ያመለክታል።

የእንስሳት ዘርፉ ከግብርና ምርት 45 በመቶ፣ ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት 18 ነጥብ 7 በመቶ እና ከጠቅላላው የአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ 16 እስከ 19 በመቶ የሚሆነውን አስተዋጽኦ ያደርጋል። የወተት ምርትም በአብዛኛው በላሞች፣ በግመሎችና በፍየሎች ላይ የተመሰረተ ሲሆን ላሞች ትልቁን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

መረጃው ኢትዮጵያ ሰፊና የተለያዩ የእንስሳት ዝርያዎች፣ ለወተት ምርት



ፎቶ፡- ኤ አይ ቻትጂፒቲ

በከተማዋ የወተትን ጥራትና ምርታማነት ከፍ ለማድረግ የተለያዩ ስራዎች እየተከናወኑ ነው

ተስማሚ የሆኑ የተለያዩ የግብርና ሥነ-ምህዳሮች፣ እየጨመረ የመጣ የወተትና የወተት ተዋጽኦ ፍላጎት እና ለዓለም አቀፍ ገበያዎች ባላት ቅርበት ለወተት ልማት ትልቅ አቅም እንዳላት ያሳያል። መንግሥትም እ.ኤ.አ. በ2031 የወተት ምርትን በአራት እጥፍ ለማሳደግ አቅዷል ይላል መረጃው።

በአፍሪካ ያሉ አንዳንድ ከተሞችም ለወተት ጥራት ከፍያለ ትኩረት እየሰጡ ነው። ለአብነትም የሩዋንዳ የደረጃዎች ቦርድ "Dairy Product Certification and Milk Collection Requirements" ሰነድ እንደሚያሳየው በኪጋሊ ከተማ ወተት እንደታለበ በፍጥነት በከተማዋ የወተት ማከማቻ ማዕከላት እንዲመረመርና እንዲቀዘቅዝ ይደረጋል። ኪጋሊና ኬንያን የመሳሰሉ ከተሞችም የጥራት ማስጠበቂያ የክፍያ ሥርዓት፣ የጋራ ማቀዝቀዣ ማዕከላት፣ ዲጂታል የሙቀት ክትትልና የላብራቶሪ ምርመራን በመጠቀም ጥራትን ከምርት መጠን ጋር እያጣመሩ ነው።

አዲስ አበባም ይህንን ሀቅ በመረዳት የወተት ምርትና ጥራት ማሻሻያ ሥራዎችን እያጠናከረች ነው። ዓለም አቀፉ የእንስሳት ሀብት ምርምር ተቋም እ.ኤ.አ. ታህሳስ 2026 "Thriving against the odds through positive deviant behavior: technology adoption and entrepreneurship among dairy farmers in Addis Ababa and Oromia in Ethiopia" በሚል ርዕስ ይፋ ባደረገው መረጃ አዲስ አበባ ለወተት ጥራትና ምርት ሰፊ ትኩረት መስጠቷን ያመለክታል። እንዲሁም እ.ኤ.አ. ጥር 2026 ይፋ ባደረገው ጥናታዊ መረጃ አዲስ አበባና አካባቢዋ የከተማና የከተማ ዳርቻ ወተት ምርት ማዕከል መሆናቸውን ጠቁሟል።

በከተማዋ የሚካሄደው የወተት ልማት ለሕዝቡ የምግብ አቅርቦትን ከማሻሻል ባሻገር ለቤተሰቦች ገቢና ለዜጎች የሥራ ዕድል እየፈጠረ ነው፡፡ ለአብነትም በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ነዋሪ አቶ አባት ባዩ ሰባት የወተት ላሞች ያሏቸው ሲሆን ከሚያልቡ ሶስት ላሞች በቀን ከ45 ሊትር በላይ ወተት ያገኛሉ።

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ነዋሪ አቶ አበራ በየነም ከ22ቱ ላሞቻቸው በቀን 230 ሊትር ወተት ያገኛሉ። በሶስት የመሸጫ ሱቆቻቸውም ለ11 ሴቶችና 8 ወንዶች፣ በአጠቃላይ ለ19 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ችለዋል፡፡

በጉለሌ ክፍለ ከተማ የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሳልፉኮ ሻኖ እንደገለጹት በክፍለ ከተማው አንድ የወተት ላም ክላስተር በመገንባት ተጠቃሚዎችን በአንድ ላይ በማሰባሰብ ድጋፍ እየተደረገ ነው። በእንስሳት ዘርፍ ወደ 20ሺህ ተጠቃሚዎች ሲኖሩ በወተት ዘርፍ 376 ነዋሪዎች ተሳታፊ ናቸው።

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የእንስሳት ሃብት ልማት ቡድን መሪ ወይዘሮ ንግስት አበራ እንደገለጹት ጥራቱ የተጠበቀ ወተት ለማምረት የእንስሳት ሕክምናና ክትባት፣ የመጠለያ ንጽህና፣ ጥራት ያለው መኖ እና የማለቢያ እቃዎች ንጽህና፣ የመስክ የሕክምና፣ የማዳቀል፣ የግብዓትና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ የመረጃ፣ ከገበያ ማስተሳሰርና ስልጠና ድጋፎች በተጨማሪም በወተት ላሞች እርባታ የሴት ጥጃ የመገኘት ዕድልን ለመጨመር የሚያግዝ ቴክኖሎጂ እንዲጠቀሙ እየተደረገ ነው፡፡ በክፍለ ከተማዋም 1 ሺህ 437 በወተት ልማት ዘርፍ የተሰማሩ ሲሆን ከአንድ ላም በቀን በአማካይ ከ15 እስከ 20 ሊትር ወተት ይገኛል ብለዋል፡፡

ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ጋር ቆይታ ያደረጉት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ፀጋ ለማ (ዶ/ር) እንደገለጹት ጥራትና ደህንነት ያለው ወተት ለማህበረሰቡ ለማቅረብ የመኖና መድኃኒት ጥራት ቁጥጥር፣ በእንስሳት እርባታ ውስጥ በሽታ እንዳይገባ፣ እንዳይሰራጭና እንዳይተላለፍ የሚያግዙ የመከላከያ እርምጃዎች፣ የላሞች አያያዝ፣ የወተት ምርት አያያዝና ስርጭት ላይ ስልጠናና ቁጥጥር እየተደረገ ነው። የወተት ጥራት መመርመሪያ መሳሪያዎች ፍተሻና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እየተሰጠ ስለመሆኑም ፀጋ ለማ (ዶ/ር) ተናግረዋል።

እንደ ኃላፊው ገለጻ ከወተት ጥራት፣ ደህንነትና ግብይት ጋር ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በዳሰሳ ጥናት በመለየት የሕግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቷል፤ ይህንን አፅድቆ ወደ ተሟላ ቁጥጥር ለመግባት በሂደት ላይ ነው፡፡ ማህበረሰቡም ጥሬ ወተት የመጠቀም ልምዱን ቀንሶ ፓስተራይዝድ የሆነ፣ ደህንነቱ ተረጋግጦ ሰርቲፋይድ የሆነ ምርት እንዲጠቀም ግንዛቤ እየተፈጠረ ነው።

በከተማዋ 6ሺህ 986 የወተት ላም አርቢዎች እና 29 ሺህ 150 የወተት ላሞች ይገኛሉ። በ2018 ዓመተ ምህረትም 156 ሚሊዮን 574 ሺህ 529 ሊትር የወተት ምርት መገኘቱን የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን መረጃ ያመለክታል።

በርግጥ የወተት ጥራት የምግብ ጉዳይ ብቻ አይደለም፤ የትውልድ ጉዳይ ነው። ጥራት ያለው ወተት የሕፃናትን ጤና ይጠብቃል፣ የቤተሰብን ጤና ያጠናክራል፣ የአምራቹን ገቢ ያሳድጋል፣ ብክነትን ይቀንሳል፣ የሥራ ዕድል ይፈጥራል። ከሁሉም በላይ ግን የዛሬን ሕፃን የነገ ጠንካራ ዜጋ ለማድረግ ከሚያግዙ የምግብ ሥርዓቶች አንዱ ነው፣ ወተት። በመሆኑም የወተትን ጥራት መጠበቅ፣ የነገን ትውልድ መጠበቅ ነውና ከተማዋ የወተት ምርትና ጥራትን ከፍ ለማድረግ እያከናወነች ያለው ዘርፈ ብዙ ተግባር ትልቅ ዋጋ ያለው ነው፡፡

# የክረምት ማጠናከሪያ ትምህርት በልጆች አንደበት

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ሰላም ልጆች፤ እንዴት ናችሁ? በክረምት ለመደበኛ ትምህርታችሁ እንዲያግዛችሁ በበጎ ፈቃድ መምህራን የማጠናከሪያ ትምህርት እየተማራችሁ ነው? አዎ! ከሆነ እያስገኘላችሁ ስላለው ጠቀሜታ ከጓደኞቻችሁ አልያም ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ሀሳብ ተለዋወጡ። እያልን እየተማሩ ያሉ ልጆችን ተሞክሮ በሚከተለው መልኩ አቅርበንላችኋል፡፡



ፎቶ፦ በገነት ወንድሙ

ልጆች የክረምት የበጎ ፈቃድ ማጠናከሪያ ትምህርት በመማር ለመደበኛ ትምህርት እየተዘጋጁ ነው

ቤርሲት ቢያድግልኝ እባላለሁ፡፡ 10 ዓመቴ ነው፡፡ በቀጣይ ዓመት የ4ኛ ክፍል ትምህርት ለመማር በዝግጅት ላይ ነኝ፡፡ የክረምት ጊዜዬንም በሚያዝያ 23 ቅድመ አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የክረምት ማጠናከሪያ ትምህርት እየተማርኩ እገኛለሁ። ከምማራቸው የትምህርት አይነቶች መካከል እንግሊዘኛ፣ ሂሳብ፣ አካባቢ ሳይንስ ይገኙበታል፡፡

ይህን ማድረጌ መደበኛ ትምህርቴን ያቀልልኛል፡፡ ሁሉ ነገር አዲስ እንዳይሆንብኝ ይረዳኛል፡፡ የማንበብና የማጥናት ልምዴ እንዲዳብር ያደርገኛል። ከመደበኛው ትምህርት ውጭ ያለውን የጊዜ አጠቃቀሜን አሻሽሎልኛል።

ናትናኤል ታምሩ እባላለሁ። 7ኛ ክፍል ነኝ፡፡ 13 ዓመቴ ነው። በክረምቱ ወቅት በሚያዝያ 23 ቅድመ አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የክረምት ማጠናከሪያ ትምህርት እየተማርኩ ነው፡፡ ይህ እድል ተፈጥሮልኝ በመማሬ ደስተኛ ነኝ፡፡ የ7ኛ ክፍል የትምህርት አይነቶች የሚሰጡት በእንግሊዘኛ በመሆኑ መደበኛ ትምህርት ስጀምር አዲስ አይሆንብኝም፡፡

በተጨማሪም ውጤቴን ለማሻሻል ያግዘኛል፡፡ የትምህርቱን መቅለልና መክበድ በመለየት ጠንክሬ እንዳነብና ቀድሜ እንድዘጋጅም ፍንጭ ይሰጠኛል። ይህ ክፍል ውስጥ እደግማለሁ ወይም አላልፍም የሚል ስጋትን ይቀንስልኛል። ከተለያዩ ትምህርት ቤቶች የሚመጡ ተማሪዎች ጋርም አዳዲስ ጓደኞችን ተዋውቄበታለሁ፡፡

ፍሬህይወት ዘላለም እባላለሁ። የ6ኛ ክፍል ተማሪ ስሆን 12 ዓመቴ ነው፡፡ በትምህርት ቤቱ የሚሰጠው የክረምት የበጎ ፈቃድ ማጠናከሪያ ትምህርት መደበኛውን ትምህርት ቤተሰቦቼም ስለሚያስጠኑኝና የተማርኩትን ስለሚጠይቁኝ የማንበብ ልምዴ እንዲጨምር አድርጎኛል፡፡

ልጆች የክረምት የማጠናከሪያ ትምህርት እየተማሩ መሆናቸው ለቀጣይ የመደበኛ ትምህርታቸው አጋዥ እንደሚሆናቸው ጓደኞቻችሁ ተናግረዋል፡፡ እየተሰጠ ያለውን ትምህርት የማትከታተሉ ተማሪዎች ይህን ዕድል ሳታባክኑ ብትጠቀሙበት መልካም ነው መልዕክታችን ነው፡፡

## ወዳጅነት ፓርክ፤ በአዲስ አበባ የደስታ ማዕድ



በአዲስ አበባ ከአንድነት ፓርክ አጠገብ የሚገኘው ወዳጅነት ፓርክ ለመዝናናትና ከተፈጥሮ ጋር ጊዜ ለማሳለፍ የሚያምር ቦታ ነው። ፓርኩ በውስጡ የሚያምሩ የአበባ ቦታዎች፣ የእግር መሄጃዎች፣ ሰው ሰራሽ ሐይቅ፣ የውሃ ፏፏቴዎች እና ለተለያዩ ዝግጅቶች የሚያገለግል መድረክ አለው። በሐይቁ ውስጥም ዓሳዎችና ዳክዬዎች ይገኛሉ።

ወዳጅነት ፓርክ ከተከፈተበት ጊዜ ጀምሮ በከተማዋ ከሚጎበኙ ታዋቂ የመዝናኛ ቦታዎች አንዱ ሆኗል። በተለይም ቅዳሜና እሁድ ቤተሰቦች፣ ልጆችና ወጣቶች ለመዝናናት፣ ለመራመድና ውብ ጊዜ ለማሳለፍ ይመጣሉ። ስለዚህ ከተማችንን በምንጎበኝበት ጊዜ ወዳጅነት ፓርክን ማየቱ እንዳይረሳ።

# 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ሲወስዱብኝ የምሰፋ?**

**መልስ፦** ሐ. ጉድጓድ

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**አንድ ጊዜ ተዘርቶ ሁለተኛ የማይዘራ፣ ታጭዶ የማይዘራ፣ ታጭዶ ምርት የማይገኝበት ምንድን ነው?**

ሀ. ስንዴ

ለ. ጸጉር

ሐ. አረም

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ::**

**ከአዲስ አበባ ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ**

# በከተማዋ ዝማኔ ውስጥ የቢሮው ሚና

**በአብርሃም ገብሬ**

በመዲናችን አዲስ አበባ በየጊዜው በሚከናወኑ የከተማ ማሻሻያዎችና የመሰረተ ልማት ስራዎች አማካኝነት ፈጣንና ዘርፈ ብዙ ለውጥ እያደረገች ትገኛለች፡፡ የኢትዮጵያና የአፍሪካ መዲና የሆነችውን አዲስ አበባ ለነዋሪዎቿ የተመቸች፣ ለጎብኚዎቿ ደግሞ ማራኪና ይበልጥ ተወዳዳሪ የማድረግ ጥረት በከፍተኛ ትኩረት እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ይህ የኮሪዶር ልማትን፣ የሕዝብ መዝናኛና የአረንጓዴ ስፍራዎችን ማስፋፋት፣ እንዲሁም ዘመናዊ የከተማ አደረጃጀትን ያካተተው ሁለገብ እንቅስቃሴ፣ የአዲስ አበባን ገጽታ እየቀየረው ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ጉልህ ለውጦች መካከል ዋናው ተግባር ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በየዘርፉ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ አዲስ አበባ በቴክኖሎጂ የላቀች ዘመናዊ ከተማ እንድትሆን እየተደረገ ባለው በዚህ ጥረት፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የራሱን አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል፡፡

ለከተማዋ የቴክኖሎጂ ሽግግር ቁልፍ ሚና እየተጫወተ የሚገኘው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ፣ በአዋጅ ማሻሻያ ቁጥር 79/2015 መሠረት ህጋዊ ህልውና አግኝቶ ተቋቋመ፡፡ በአዋጁ የተሰጡት ከሃያ በላይ ስልጣንና ተግባራት ተቋሙ የከተማዋን አገልግሎት አሰጣጥ በጥናትና በፈጠራ ላይ ተመስርቶ ለውጥ እንዲያመጣ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ይህን ታላቅ ተልዕኮ በብቃት ለመወጣት አስፈላጊውን የሰው ኃይል፣ ዘመናዊ የአሰራር ሥርዓት እና ድርጅታዊ አደረጃጀት ዘርግቶ ወደ ተግባር በመግባት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡

ቢሮው የተጣለበትን ሀገራዊና ከተማ አቀፍ ኃላፊነት በስኬት ለመወጣት ስራዎቹን በሶስት ዋና ዋና ዘርፎች ከፍሎ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ እነሱም የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ዘርፍ፣ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ኦፕሬሽን አገልግሎት ዘርፍ እና የስማርት ሲቲ ዘርፍ ናቸው፡፡ ቢሮው እያከናወናቸው ካሉ ተግባራት መካከል፡- በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ መንግስታዊ ተቋማትን በቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት በማስተሳሰር ላይ ይገኛል። በዚህም ለህብረተሰቡ ተደራሽና ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ የሚያስችል ስትራቴጂ ቀርጾ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ እንዲሁም በቴክኖሎጂ ዙሪያ የሚሰሩ የመንግስትና የግል ተቋማትን ዓለም አቀፍ ስታንዳርዶች ያሟሉ መሆናቸውን ይቆጣጠራል፡፡ ይሄ ቁጥጥር የሙያ ፈቃድ መስጠትን ያካተተ ሲሆን የሬጉላቶሪ፣ የስታንዳርድ ዝግጅት፣ ክትትል እና ቁጥጥር ስራዎችን ይጨምራል። ተቋሙ በቀጣዮቹ ሰባት ዓመታት የሚተገበሩ የስማርት ሲቲ ፕሮጀክቶችን እውን ለማድረግ መንግስታዊና የግል ሴክተሩ አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ እንደሚጠበቅባቸውም አሳስቧል፡፡

የቢሮው ርዕይና ተልዕኮን ስንመለከት፣ በ2025 ወሳኝ ቴክኖሎጂዎችን ተግባራዊ በማድረግ ለነዋሪዎቿ እና ለጎብኚዎቿ ምቹ የሆነች፣ ዘላቂ እና ችግሮችን መቋቋም የምትችል አዲስ አበባን ማየት ነው። ተልዕኮው ደግሞ፣ በጥናትና ምርምር የተደገፈ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማቶችን በማልማት፣ ደህንነታቸው የተጠበቁ ሲስተሞችን በማበልጸግ፣ ዲጂታል አገልግሎት በማስፋፋት፣ የከተማዋን ነዋሪዎች እና የጎብኚዎቿን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነው፡፡

## የቢሮው ስልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነት ምንድ ናቸው?

የቢሮው ስልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነት የሚከተሉት ናቸው፡፡ የከተማ አስተዳደሩን ተልዕኮ ሊያሳኩ የሚያስችሉ የኢኖቬሽንና የቴክኖሎጂ ጥናትና ምርምር መስኮችን ይለያል፣ ከተማ አቀፍ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ምርምር ፕሮግራሞችን ያካሄዳል፣ እንዲካሄዱ ያደርጋል፣ ያስተዋውቃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል። እንዲሁም የከተማ አስተዳደሩን የኢኖቬሽን፣ የስማርት ቴክኖሎጂ፣ የአዳጊ ቴክኖሎጂ፣ ከተማ አቀፍ የፖሊሲ ማሻሻያዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ህጎች እና ፕሮግራሞችን ይቀርጻል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፡፡ በከተማ አስተዳደሩ የሚሰጡ አገልግሎቶችን የተቀናጀ ለማድረግ ተገቢውን መረጃ ያሰባስባል፣ መተንተን የሚያስችል ከተማ አቀፍ የመረጃ ቋት ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፣ ቀጣይነቱንም ያረጋግጣል፡፡

በሌላ በኩል የከተማ አስተዳደሩ ተቋማት የኮምፒዩተር መረቦች፣ አፕሊኬሽኖች፣ የኔትዎርክ ኮኔክቲቪቲ እንዲቀናጁና እንዲናበቡ ያደርጋል፤ እንዲሁም ይቆጣጠራል፡፡ ለከተማ አስተዳደሩ ተቋማት የሶፍትዌር ሲስተምና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ያለማል፣ እንዲለማ ያደርጋል፣ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፡፡ እንዲሁም በከተማው አስተዳደር ተቋማት የሚለሙና የሚተገበሩ የጂኦ-ኢንፎርሜሽን ሲስተም በተመለከተ የተቋማትንና የከተማ አስተዳደሩን ፍላጎት መሠረት አድርጎ በጋራ ይሰራል፡፡

> **የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ በህጋዊ ማዕቀፍ ተደራጅቶ የሚያከናውናቸው ሁለገብ የዲጂታላይዜሽን፣ የስማርት ሲቲ እና የመሰረተ ልማት ማሻሻያ ስራዎች ከተማዋን ወደ ላቀ የቴክኖሎጂ ምዕራፍ የሚያሸጋግሩ ናቸው**

ቢሮው ከእነዚህ ኃላፊነቶች በተጨማሪ በኮምፒዩተር መረብ ዝርጋታ፣ በሶፍትዌር ሲስተም ልማት እንዲሁም በቴክኖሎጂ ዘርፍ ማማከር ለሚሰማሩ ግለሰቦችና ተቋማት የሙያ ፈቃድ ይሰጣል። የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማት፣ አስተዳደር እንዲሁም አጠቃቀም በተመለከተ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ይሰጣል፣ ያስተባብራል፡፡ የአስተዳደሩ የግዥና ንብረት አስተዳደር እንዲሁም ሌሎች የሕግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው አገልግሎት መስጠት ያቆሙ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዕቃዎችን ይለያል፡፡ ተለይተው አገልግሎት መስጠት የሚችሉትን ይጠግናል ወይም እንዲጠገን ያደርጋል፡፡ ከአገልግሎት ውጭ የሆኑትን እንዲወገዱ ለሚመለከተው አካል ይልካል፡፡ የከተማ አስተዳደሩን መረጃዎች እና ሲስተሞች ደህንነት ይቆጣጠራል፣ የደህንነት መቆጣጠሪያ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል። እንዲሁም በሲስተሞችና በመሰረተ ልማቶች ላይ የደህንነት ኦዲት ያደርጋል።

እንዲሁም የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ቢዝነስ ኃሳብ ያላቸው ግለሰቦችና ቡድኖችን ወደ ስራ ማስገባት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ ለከተማው አስተዳደር ተቋማት የክላውድ ዳታ ሴንተርና የክላውድ አገልግሎት ተግባራዊ የሚያደርግ ሲሆን፣ የአሰራር ስርዓቱንም ይዘረጋል፡፡ የአስፈፃሚ ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽ ቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን ያደርጋል፣ እንዲሁም በከተማ አስተዳደሩ የለሙ መሰረተ ልማቶችንና ሲስተሞችን ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፣ ይመራል፡፡

ከዚህ ባሻገር ቢሮው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የልህቀት ማዕከል ያደራጃል፣ በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፡፡ እንዲሁም የከተማውን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኦዲት በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፡፡ የኢኖቬሽንና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የጥገና፣ የቤተ ሙከራ ሰርቶ ማሳያ እና የስልጠና ማእከል ከማደራጀት ባለፈ ያሰለጥናል፣ በበላይነትም ይመራል፡፡

ቢሮው ሀገር በቀል ቴክኖሎጂዎችን ለማሻሻል፣ ለማሳደግና ለገበያ ለማቅረብ የሚደረጉ ጥናቶችን፣ የምርምርና ስርጸት ሥራዎችን ያበረታታል፡፡ ወደ ተግባር እንዲሸጋገሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል። የከተማ አስታዳደሩን ሥርዓተ-ትምህርት ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት አንፃር መቃኘቱን ለማረጋገጥ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ የትምህርት ተቋማት ጋር በትብብር ይሰራል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የከተማ አስተዳደሩን የኢ-መንግስት ልማት እና የዲጂታላይዜሽን ስርዓቶች ለማስተግበር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል። በከተማ አስተዳደሩ ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማትና ለፈጠራ ሥራዎች ዕድገት አስተዋጽዖ ላበረከቱ ግለሰቦች ወይም ተቋማት ሽልማትና ማበረታቻ የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፡፡

በአጠቃላይ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ በህጋዊ ማዕቀፍ ተደራጅቶ የሚያከናውናቸው ሁለገብ የዲጂታላይዜሽን፣ የስማርት ሲቲ እና የመሰረተ ልማት ማሻሻያ ስራዎች ከተማዋን ወደ ላቀ የቴክኖሎጂ ምዕራፍ የሚያሸጋግሩ ቁልፍ ውጥኖች ናቸው። ቢሮው በሶስቱም ዋና ዋና ዘርፎች የተጣለበትን ኃላፊነት በመወጣት፣ የሕዝብ አገልግሎትን የተቀናጀ፣ የተቀላጠፈና ደህንነቱ የተጠበቀ ለማድረግ የሚያደርገው ጥረት የነዋሪዎችን የኑሮ ጥራት ከማሻሻሉም በላይ የከተማዋን አጠቃላይ አሰራር ዘመናዊ ያደርጋል። በመሆኑም እነዚህን የተቀናጁ የቴክኖሎጂ ስራዎችና የስማርት ሲቲ ፕሮጀክቶችን በባለድርሻ አካላት ህብረት እውን ማድረግ፣ አዲስ አበባን ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ ለጎብኚዎቿ ደግሞ ማራኪና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነች ዘመናዊ መዲና የማድረግ ርዕይን ስኬታማ ለማድረግ ወሳኝ ድርሻ ይኖረዋል።

ፎቶ፦ ከገፀ ድር
ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ከአዲስ አበባ የቀጣይ ጉዞ ጋር የሚመጋገብ ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል

## ከዳግማዊ ምኒልክ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ጋር በመተባበር በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ

# ኮሌጁ በዲጂታል መንገድ

- ኮሌጁ አዲስ አበባን 'ስማርት ሲቲ' ለማድረግ ከተጀመረው ፕሮጀክት ጋር የተጣጣሙ ተግባራትን እያከናወነ ስለመሆኑም ተመላክቷል

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**

በሀገራችን የህክምና ታሪክ ውስጥ በተለይም የጤና ባለሞያዎችን በብቃትና በብዛት አሰልጥኖ ለጤናው ዘርፍ ከሚያበረክቱ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የዳግማዊ ምኒሊክ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ቀዳሚው ነው፡፡

በአዲስ አበባም ሆነ በሀገሪቱ ለህክምናው ዘርፍ የጤና ባለሞያዎችን እያሰለጠነ ወደ ስራው አለም ማሰማራት ከጀመረ ወደ 76 ዓመታትን ያስቆጠረው የዳግማዊ ምኒሊክ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከዚህ በፊት ካለው ረጅም የስራ ዘመን ልምድ አንፃር ከቴክኖሎጂ ጋር ያለው ግንኙነት ግን በእጅጉ የተራራቀ እንደነበር ነው ከኮሌጁ ያገኘነው መረጃ የሚያመለክተው፡፡



ፎቶ፦ ከፋይል
የዳግማዊ ምኒልክ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ምቹና ዘመናዊ ለማድረግ ከተሰሩ ተግባራት መካከል ከፊሎቹ

ሆኖም ግን ከ2016 ዓመተ ምህረት ጀምሮ የተቋሙን አገልግሎት ለማዘመንና ዲጂታላይዝ ለማድረግ ከአዲስ አበባ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ጋር በመተባበር የኔትዎርክ ፕሮጀክት መሰረተ ልማቶችንና የአይሲቲ ዲጂታላይዜሽን ስራዎችን ተግባራዊ በማድረጉ በርካታ ስራዎች መሰራታቸውን ነው በኮሌጁ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አስተዳደር (IT) ዳይሬክተር አቶ ጋዲሳ ከበደ ያስረዱት፡፡

ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ከተደረገ በኋላ የኮሌጁን አሰራር ሙሉ በሙሉ ወደ ዲጂታል ለመቀየር ከሃገሪቱም እቅድ አንፃር በተለይ ደግሞ ከአዲስ አበባ መስተዳደር ስማርት ሲቲ ፕሮጀክት አኳያ አጠቃላይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋርም ሆነ ከህክምና ጋር ያሉት ወደ ዲጂታላይዜሽን መዞር ስላለባቸው ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

ፕሮጀክቱ በውስጡ የኔትወርክ ዝርጋታዎችንና ወደ አራት የሚሆኑ ስማርት የኮምፒውተር ላብራቶሪዎችን የያዘ ነው፡፡ ይህም የኔትወርክ መሰረተ ልማቶች ያሉት ኢንትራክቲቭ ቦርዶች እንዳሉት የጠቀሱት አቶ ጋዲሳ መሰረተ ልማቶቹ መዘርጋታቸው አንዳንድ የጤና ትምህርቶችን በኢሌክትሮኒክ ትምህርት አመካኝነት ከሌላ ቦታ ሆኖ ለማስተማር ወሳኝ ነው ባይ ናቸው፡፡

ለዚህም ሲባል የኔትወርክ ፕሮጀክት መሰረተ ልማቶችንና የአይሲቲ ዲጂታላይዜሽን ስራዎችን ተግባራዊ ማድረግ ቀዳሚው እንደነበር አውስተው፣ የትምህርትና ስልጠና አሰጣጥን በቴክኖሎጂ መደገፍ (E-Learning) ተግባራዊ ማድረጉ ለመማር ማስተማሩ ስራ ምቹ ሁኔታን መፍጠሩን አስረድተዋል፡፡

የመሰረተ-ልማት ግንባታ ያሉ ዲጂታል አገልግሎቶች ስኬታማነት አስተማማኝ የኢንተርኔትና የውስጥ መስመር (LAN) ዝርጋታ ስለሚጠይቅ፣ ተቋሙ የፋይበር ኦፕቲክስ መስመሮችን የመዘርጋትና የሰርቨር (Server) አቅምን የማሳደግ ስራዎችን እያከናወነ እንደሆነም ዳይሬክተሩ ሳይጠቅሱ አላለፉም።

እንደ አቶ ጋዲሳ አባባል ከዲጂታላይዤሽ አንፃር በተቋሙ የመጀመሪያ ስራ የሆነውም የኔትወርክ መሰረተ ልማት ዘርጋታ ነው፡፡ አጠቃላይ የግቢውን መሰረተ ልማት በገመድም ገመድ አልባም መሰረተ ልማት በኔትወርክ የማስተሳሰር ስራ የተሰራ ሲሆን ይህም ተቋሙ በጣም ፈጣንና ዘመኑን የዋጁ ቴክኖሎጂዎች ብሎም የማዕከላዊ መረጃ ቋትና ደረጃውን የጠበቀ የዳታ ሴንተር እንዲኖረው አስችሎታል፡፡

የኔትዎርክ ዝርጋታው ተግባራዊ ከተደረገ በኋላ በስማርት ክፍሎች የኮምፒውተር ላብራቶሪዎችን በመጠቀም ስማርት ዲጂታል ላይብረሪ እና ስማርት የመማሪያ ክፍሎች እንዲኖሩም ተደርጓል፡፡ ይህም የሃገር አቀፍ ፈተና ማዕከል በመሆን የ12 ክፍል የማጠናቀቂያ ፈተናዎችን፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መውጪያ ፈተናዎችንና ለጤና ሚኒስቴር የC O C ፈተናዎች እንደ አንድ ማዕከል ሆኖ እንዲያገለግል ከማድረጉም ሌላ እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአንድ ጊዜ ወደ 300 ለሚጠጉ ሰዎች ተደራሽ ለመሆን አስችሏል ባይ ናቸው፡፡

> **ለህክምናው ዘርፍ ብቁ የጤና ባለሞያዎችን በማሰልጠን 76 ዓመታትን ያስቆጠረው የዳግማዊ ምኒልክ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከ2016 ዓመተ ምህረት ጀምሮ ከአዲስ አበባ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ጋር በመተባበር የኔትዎርክ ፕሮጀክት መሰረተ ልማቶችንና የአይሲቲ ዲጂታላይዜሽን ስራዎችን ተግባራዊ በማድረጉ በርካታ ለውጦችን እያስመዘገበ ነው**

ይህ አገልግሎት በብዙ ተቋማት ተደራሽ ስላልሆነ በከተማ አስተዳደሩ ስር ያሉ ተቋማት ትልልቅ ስልጠናዎችን ሲያዘጋጁና የኮምፒውተር ፋሲሊቲ ሲፈለግ ይጠቀማሉ ብለው፤ በተለይ የአዲስ አበባ ፐብሊክ ሰርቪስ ቢሮ፣ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ፣ ምግብና መድኃኒት ቁጥጥርን ጨምሮ በርካታ መስሪያ ቤቶች እንደሚጠቀሙም በአብነት ጠቅሰዋል፡፡

ከሌሎች ተቋማት በተጨማሪም በበይነ መረብ (E-learning) መድረኮች ለህክምናና ጤና ሳይንስ ተማሪዎች የትምህርት ግብዓቶችን፣ ሞጁሎችንና የመፅሃፍትን ተደራሽነት ለማቃለል የኦንላይን መድረኮች ጥቅም ላይ እየዋሉ ከመሆናቸውም ሌላ በዲጂታል ቤተ-መጻሕፍት አገልግሎትም ተማሪዎችና ተመራማሪዎች የቅርብ ጊዜ የህክምና ጥናቶችንና መጽሔቶችን (Journals) በነፃና በዲጂታል መንገድ እንዲያነቡ የኢንተርኔትና የዳታቤዝ አቅርቦቶች እየተሻሻሉ ነው።

በፈተናና ምዘና ሥርዓት ረገድም የተማሪዎችን ፈተናዎች በኮምፒውተር የታገዙ (Computer-Based Testing) በማድረግ የምዘና ሂደቱን ፈጣንና ግልጽ የማድረግ ስራዎች እየተሰሩ እንደሆነ ጠቅሰው የኮሌጁን አስተዳደራዊ ስራዎችን ለማሳለጥ በተለይም በሰው ኃይልና ፋይናንስ አስተዳደር ዘርፍ የሰራተኞችን የስራ አፈጻጸም፣ የደመወዝና የፋይናንስ ግብይቶችን ወደ ዲጂታል በመቀየር ቢሮክራሲን የመቀነስ ስራ እየተሰራ እንደሆነ አቶ ጋዲሳ አብራርተዋል፡፡

በተለይ አሁን ያለንበት ወቅት ከሀገሪቱም እቅድ አኳያ በርካታ ነገሮች ወደ ዲጂታላይዜሽን አሰራር እየተቀየሩ ነው፡፡ የትምህርት ጥራትና ቁጥጥር ባለስልጣንም ይህንን ለኮሌጁ እንደ አንድ መስፈርት ማስቀመጡን አስታውሰው፤ በተለይ ፈተናዎች ዲጂታል መደረግ እንዳለባቸው ዌብ ሳይቶች ሊኖሩት እንደሚገባና የሬጅስትራል ሲስተሞች ዲጂታላይዝ መደረግ እንዳለባቸው አቅጣጫ መውረዱን ከዚህ ውስጥ የላይብረሪ ዲጂታላይዜሽ አንዱ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ኮሌጁ የዲጂታል አገልግሎት መጀመሩ እንደ ሀገር ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ወደ ዲጂታል ስርዓት እንዲገቡ የተያዘው ውጥን እውን እንዲሆን ምን አቅም ይሰጣል ብለን ላነሳንላቸው ጥያቄም እጅግ በጣም አቅም እንደሚፈጥር ጠቅሰው ተማሪዎቹ ወደ ስራው አለም ሲሰማሩም ሆነ ወደፊት አጠቃላይ ሀገሪቱን ወደ ዲጂታላይዜሽን ሪፎርም ስትሄድ አንድ ግብዓት ይሆናል ብለዋል፡፡

ጤና ሚኒስቴር እያካሄደ ላለው የዲጂታል ጤና ሪፎርም በኮሌጁ ተምረው የሚወጡ ተማሪዎች ተመሳሳይ ነገር ይዘው ስለሚወጡ የጤና ሚኒስቴር እቅድ የተሳካ እንዲሆን ይረዳል። በተለይ አዲስ አበባ የሃገሪቱ መዲና እንደመሆኗ ከተማዋን ስማርት ሲቲ ለማድረግ የተጀመረውን ፕሮጀክትም እውን ለማድረግ ከፍ ያለ አበርክቶ አለው ባይ ናቸው፡፡

በሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጁ ተገኝተን እንደታዘብነውም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (IT) አስተዳደር ክፍል የተቋሙን የትምህርትና የምርምር አገልግሎት ዘመናዊ ለማድረግ ዋና ዋና የቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማቶችን የመገንባትና የማስተዳደር ሰፊ ስራዎችን እያከናወነ እንደሆነ ነው ከኮሌጁ ለማረጋገጥ የቻልነው፡፡

በተለይም የመሰረተ-ልማት ግንባታ እና አውታረ-መረብ ዝርጋታ፣ የመረጃ ደህንነት እና የውሂብ ጥበቃ እንዲሁም የተቋሙ ሰራተኞች እና መምህራን ለሚያጋጥሟቸው የኮምፒውተር፣ የፕሪንተር ወይም የሲስተም ብልሽቶች ፈጣን የቴክኒክ ጥገና አገልግሎት ከመስጠት በተጨማሪ በኮሌጁ ውስጥ ያሉትን ኮምፒውተሮች፣ ፕሮጀክተሮች፣ እና ሌሎች የቴክኖሎጂ እቃዎች ያሉበትን የቴክኒክ ድጋፍ እና የንብረት አስተዳደር ላይ በትኩረት እየሰራ መሆኑን ተመልክተናል፡፡

# ቴክኖሎጂን ምርኩዝ ያደረጉ የአረንጓዴ ልማት ስራዎች

**በጊዜው አማረ**

የአየር ንብረት ለውጥ ዓለም አቀፍ ስጋት በሆነበት በዚህ ዘመን ተፈጥሮን ለመጠበቅ እና ምድርን አረንጓዴ ለማልበስ የምንከተላቸው መንገዶች ዘመናዊና በቴክኖሎጂ የታገዙ መሆን ግድ ይላቸዋል። የችግኝ ማፍላት፣ የመትከል እና የመንከባከብ ስልቶች በጊዜ፣ በሰው ሃይል እጥረት፣ በግንዛቤ ማነስ እና ሌሎች ምክንያቶች ውጤታማነቱ ላይ ጥያቄ ይነሳል። ዛሬ ላይ ቴክኖሎጂን ከአረንጓዴ ልማት ጋር በማዋሃድ የሚከናወነው የችግኝ ልማት ሂደት ከዘር ምርጫ አንስቶ እስከ መትከልና መንከባከብ ድረስ ያለውን ጉዞ ሙሉ በሙሉ በመቀየር ከፍተኛ ውጤት እያስመዘገበ ይገኛል።

## ቴክኖሎጂ በችግኝ ማፍላት ወቅት

ቴክኖሎጂ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም እና የአረንጓዴ ልማትን ለማሳካት እጅግ ወሳኝ ሚና እየተጫወተ ይገኛል። ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የሚከናወን የችግኝ እንክብካቤ ከባህላዊው አሰራር በበለጠ ፍጥነት፣ ጥራት እና ቅልጥፍና ውጤት እንዲገኝ አስችሏል፡፡

ስራውን በቴክኖሎጂ ማገዝ የተሻሉ እና በሽታን የሚቋቋሙ ዘሮችን ለመምረጥ ያስችላል። የዘር ጥራትን በዲጂታል ስካነሮች እና በባዮቴክኖሎጂ መመርመር የተሻለ መብቀል የሚችሉ ዘሮችን ብቻ ለመለየት ያስችላል። ይህም ድካምና ወጪን በእጅጉ ይቀንሰዋል።

ዘሩን በማፍላት ሂደት ውስጥም ዘመናዊ ግሪን ሃውሶች (Smart Greenhouses) ጥቅም ላይ ይውላሉ። እነዚህ ሲስተሞች የሙቀት፣ የእርጥበት እና የብርሃን መጠንን ያለማቋረጥ በመከታተል ለዘር መብቀል ተስማሚ የሆነውን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራሉ።

በቴክኖሎጂ የታዘገ የችግኝ ማፍላትና እንክብካቤ ሌላው ጠቀሜታ በውሃ አጠቃቀም ላይ የሚታየው ከፍተኛ ቅልጥፍና ነው። አውቶማቲክ የጠብታ ሲስተም እና የአፈር እርጥበት መለኪያዎች (Soil Moisture Sensors) ችግኞቹ በሚፈልጉት ሰዓት እና ልክ ብቻ ውሃ እንዲያገኙ ያደርጋሉ። ይህ አላስፈላጊ የውሃ ብክነትን እና ችግኝ የሚያጠቃውን የፈንገስ በሽታ በመከላከል ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው።

የቴክኖሎጂ ሌላኛው ገጸ-በረከት አረም እና ተባዮችን በዘመናዊ መንገድ መቆጣጠር ማስቻሉ ነው። የኬሚካል አጠቃቀምን ለመቀነስ እና አካባቢን ለመጠበቅ ሲባል አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ (AI) የተገጠመላቸው ካሜራዎች እና ድሮኖች በመጠቀም ተባዮች ገና ሲጀምሩ ተለይተው እንዲወገዱ ይደረጋል። ይህም የችግኞችን ጤናማ እድገት አስተማማኝ ያደርገዋል።



ፎቶ- ኤ አይ ጄሚናይ

ቴክኖሎጂ የአረንጓዴ ልማት ስራውን ማሳካት ላይ አይተኬ ሚና በመጫወት ላይ ነው

## ችግኞች ለተከላ በሚዘጋጁበት ወቅት

ችግኞች ለተከላ ከመጓጓዛቸው በፊት ጠንካራ ወይም ሊጸድቁ የሚችሉ ስለመሆናቸው በቴክኖሎጂ የታገዘ ምርምራ ይደረግላቸዋል፡፡ እንዲሁም የኮምፒዩተር ሲስተሞች ችግኞቹን ከግሪን ሃውስ (ከተፈሉበት አዳራሽ) ወጥተው መሬት ላይ ሲተከሉ ቀስ በቀስ ተፈጥሯዊ የአየር ንብረትን እንዲላመዱ በማድረግ የመጽደቅ እድላቸውን ይጨምራሉ። ችግኞቹ ከሚፈሉበት ቦታ ወደ መትከያ ስፍራ በማጓጓዝ እና በመከታተል ሂደትም ቴክኖሎጂ ድርሻው የጎላ ነው። ጂፒኤስን (GPS) እና የብሉቱዝ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም የችግኞችን ዝውውር ለመቆጣጠር፣ እንዲሁም የትኛው ችግኝ የት እንደሚተከል በዲጂታል ካርታ በመቅረጽ ስራውን ቀልጣፋ ለማድረግ ያግዛል።

እንዲሁም ቴክኖሎጂ ችግኞቹ በመሬት ላይ የሚተከሉበትን ትክክለኛ ጊዜ እና ቦታ ለመምረጥ ያስችላል፡፡ የሳተላይት መረጃዎችን እና የአየር ሁኔታ ትንበያዎችን (Meteorological Data) በመጠቀም ዝናብ የሚጀምርበትን ትክክለኛ ወቅት ማወቅ ይቻላል። ይህም በደረቅ ወቅት ተተክለው ሳይጸድቁ እንዳይቀሩ ያደርጋል፡፡

ቴክኖሎጂ ምን ያህል ችግኞች ፈሉ? ምን ያህሉ ተተከሉ? የት ተተከሉ? ስንት ሰው ተሳተፈ? የሚለውን በቀላሉ ለመለየት ይረዳል፡፡ እነዚህን መረጃዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ በመሰብሰብ የተደራጀና ታማኝ መረጃ እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ቀደም ሲል በወረቀት እና በሰው ሃይል ብቻ ይከናወኑ የነበሩ የቆጠራ ስራዎች አሁን ላይ በዲጂታል ስርዓቶች በመተካታቸው ጊዜንና ጉልበትን እየቆጠቡ ይገኛሉ፡፡

> **ቴክኖሎጂ ምን ያህል ችግኞች ፈሉ? ምን ያህሉ ተተከሉ? የት ተተከሉ? ስንት ሰው ተሳተፈ? የሚለውን በቀላሉ ለመለየት ይረዳል። እነዚህን መረጃዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ በመሰብሰብ የተደራጀና ታማኝ መረጃ እንዲኖር ያደርጋል**

በችግኝ ተከላ ወቅት የችግኞችን ዝርያ ከቦታው ጋር አስተሳስሮ መያዝ (Geotagging) ለወደፊት እንክብካቤ እጅግ ወሳኝ ነው። የትኛው የአየር ንብረት እና አፈር ለየትኛው የችግኝ ዝርያ እንደሚመች በቁጥር እና በመረጃ ላይ ተመስርቶ ለማጥናት እድል ይፈጥራል። እነዚህ ሁሉ መረጃዎች በአንድ ላይ ተጠናቅረው ሲቀመጡ ለመንግስት አካላት፣ ለአካባቢ ጥበቃ ድርጅቶች እና ለህብረተሰቡ ግልጽ የሆነ ሪፖርት ማቅረብ ያስችላል። ይህም የዘመኑን የአረንጓዴ ልማት ስራዎች ይበልጥ ግልጽነት ያለው እና ስኬታማ ያደርገዋል።

## የቴክኖሎጂ ገጸ-በረከት ለችግኞች ጽድቀት

ችግኞች ከተተከሉ በኋላ የሚደረግ የዲጂታል ክትትል ከመሬት፣ አየር እና ጸሃይ ጋር ተላምደው እንዲጸድቁና ዛፍ እንዲሆኑ ለማድረግ ወሳኝ ነው። ችግኝ መትከል ብቻውን በቂ ባለመሆኑ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች የችግኞችን ህልውና እስከ መጨረሻው ድረስ ለመከታተል እድል እንደፈጠሩ የዘርፉ ተመራማሪ ሃካን ጉርሱ ገልጸዋል፡፡

ተመራማሪው "An Affordable System Solution for Enhancing Tree Survival in Dry Environments" በሚል ርእስ እ.ኤ.አ በ2024 በሰሩት ጥናት ድሮኖች እና የርቀት ዳሰሳ (Remote Sensing) ቴክኖሎጂዎች አረጓዴ ልማትን በከፍተኛ ደረጃ እያገዙ እንደሚገኝ ጠቁመዋል፡፡ በሰማይ ላይ የሚበሩ ድሮኖች የተተከሉትን ሰፊ የደን ልማት ቦታዎች በቅርበት በመቃኘት የእያንዳንዱን ችግኝ ገጽታ፣ መጠን እና አጠቃላይ የዕድገት ደረጃ በምስልና በቪዲዮ መመዝገብ ብሎም ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ፡፡ ይህም የውሃ እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች ጭምር ውጤት እያስገኘ ነው፡፡

ሌላው የቴክኖሎጂ ትልቁ ጥቅም የችግኞችን ጤናማነት እና የውሃ ፍላጎት አስቀድሞ መለየት መቻሉ እንደሆነ ተመራማሪው ሃካን ጉርሱ ኤም ዲ ፒ አይ ገጸ-ድር ላይ ለንባብ ባበቁት ጥናታዊ ጹሁፋቸው ላይ አመላክተዋል። ስፔክተራል የተባሉ የካሜራ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የችግኞቹን ቅጠልና የውሃ መጠን ማወቅ ይቻላል፡፡ ይህም ችግኞቹ በውሃ እጥረት እና በበሽታ እንዳይጠቁ ለመቆጣጠር ያስችላል፡፡

ይህን ፈጣን መረጃ ማግኘት መቻል ጉዳት የደረሰባቸውን ወይም ያልጸደቁ ችግኞች ወዲያውኑ በሌሎች ችግኞች ለመተካት ያግዛል፡፡ በዚህም የተነሳ ብዙ ችግኞች በሚተከሉበት ስፍራ ላይ ባዶ ቦታዎች (ጉድጓዶች) እንዳይፈጠሩ እና የጽድቀት መጠኑም ከፍ እንዲል ያደርጋል። በዚህም የድህረ ተከላ በቴክኖሎጂ የታገዘ የክትትል ስራ የሰው ሃይልንና ጊዜን በእጅጉ በመቆጠብ በዘላቂነት የተሳካ አረንጓዴ ልማት እንዲኖር እያገዘ ነው፡፡

## የሀገራት ልምድ

በአሁኑ ወቅት አግሮ-ቴክኖሎጂን፣ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስን፣ ድሮኖችን እና ሳተላይቶችን በመጠቀም የደን ልማትንና እንክብካቤን ከሚያከናውኑ ቀዳሚ ሀገራት መካከል አፍሪካዊቷ ሩዋንዳ ተጠቃሽ ነች፡፡ ሀገሪቱ በዘርፉ ባከናወነችው ተግባር በአፍሪካ ደረጃ የደን ልማትን በዲጂታል ስርዓት በመከታተል እና አረንጓዴ ኢኮኖሚን በመገንባት ከቀዳሚዎቹ ትጠቀሳለች። ሩዋንዳ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

## ከህግ... ከገጽ 3 የዞረ

የዚህ ለውጥ ተመልካች ሳይሆን አካል መሆን አለበት። ህገ ወጥነትና ሌብነት የሀገርን ኢኮኖሚ የሚጎዳ መሆኑን በመገንዘብ፣ ግብርን በአግባቡ መክፈል፣ ሕጋዊ አሠራርን መከተል፣ ጥራት ያለውን ምርትና አገልግሎት በፍትሃዊ ዋጋ ማቅረብ የንግዱ ማኅበረሰብ መሠረታዊ መመሪያዎች ሊሆኑ ይገባል።

በዚህ ሁሉ ውስጥ ሕዝብ የሚኖረው ሚና እጅግ ወሳኝ ነው። ሙስና አንድ ተቀባይና አንድ ሰጪ ሲኖሩት ይቀጥላል። ስለዚህ ለአገልግሎት ሂደት ጊዜ ቢወስድም እንኳ በገንዘብ ወይም በአቋራጭ ጉዳይን ለማስፈጸም መሞከርና የሙስና ተዋናይ መሆን መቆም አለበት። የሚሰጥ አካል ሲጠፋ የሚቀበል አካልም አይኖርም። በተመሳሳይም በየደረጃው የሚፈጸሙ የሌብነትና የሙስና ድርጊቶችን ለሚመለከታቸው የሕግ አካላት ያለመሰልቸት ማጋለጥ እንደሚያስፈልግ ፕሮፌሰር መሳይ ተናግረዋል።

የሌብነትን መሠረት ለማድረቅ የሚደረገው ትግል በአንድ ተቋም፣ በአንድ ሚኒስቴር ወይም በአንድ የሕግ አስከባሪ አካል ብቻ የሚከናወን አይደለም። ቤተሰብ እሴትን ይዘራል፤ ትምህርት ቤት ያጠናክረዋል፤ ሃይማኖት ያበረታታዋል፤ መንግሥት በሕግ ያስጠብቀዋል፤ ተቋማት በግልጽነት ይደግፉታል፤ ማኅበረሰቡ ደግሞ በማክበርና በመከላከል ያጠናክረዋል።

ይህ የባህልና የአስተሳሰብ ሽግግር በአንድ ጀምበር የሚመጣ አይደለም። የሚፈልገው ጽናት፣ ተከታታይነትና የሁሉም የተቀናጀ ተሳትፎ ነው። ነገር ግን ዛሬ በቤትና በትምህርት ቤት የሚዘራው የታማኝነት ዘር ነገ በሥራ ቦታ፣ በተቋማትና በሀገር አመራር ውስጥ ሙስናንና ብልሹ አሠራርን የሚቃወም ትውልድ ሊያፈራ ይችላል።

ሌብነትን ለመዋጋት የሚደረገው ትግል የወንጀለኛን እጅ በማሰር ብቻ አይጠናቀቅም። ሌብነትን እንደ ብልህነት የሚመለከት አስተሳሰብን መስበር፣ ታማኝነትን እንደ ክብር የሚቆጥር እሴት መገንባት፣ ሕግን በእኩልነት ማስከበርና በንጹህ መንገድ የተገኘ ሀብትን በማኅበረሰብ ደረጃ ማክበር ነው። ሌብነት ጥዩፍና ነውር፣ ታማኝነት ደግሞ ክብር መሆኑ በማኅበረሰቡ ባህል ውስጥ ሙሉ በሙሉ ሲሰርጽ፣ በሕግ፣ በታማኝነትና በንጹህ አገልግሎት ላይ የተገነባች ጠንካራና የተከበረች ሀገር መገንባት ይቻላል።

## ፍቅር... ከገጽ 11 የዞረ

ማህበረሰብ ሁልጊዜም አሸናፊ እና የሰላም ባለቤት እንደሚሆን ይጠቁማሉ፡፡

ገጣሚ ፍቃዱ አስራት በመድብሉ ላይ ካነሳቸው ሀሳቦች መካከል አንዱና ዋናው ለቀጣዩ ትውልድና ለሀገር ብሩህ ተስፋን ማቀንቀን ነው። ወጣቱ ትውልድ በፈተናዎችና ችግሮች ሳይበገር የነገን የተሻለ እውነታ በመገንባት ሂደት ውስጥ የተስፋን መብራት ማብራት እንዳለበት ያሳስባል። ህይወት ያለተስፋ ትርጉም የለውም፡፡ በመሆኑም ተስፋን እንደ ስንቅ ይዞ መጓዝ የዘላቂ ህልውና መዳረሻ ነው።

እያንዳንዱ ዜጋ ለሀገሩ እድገት የራሱን ድርሻ ማበርከት የሚችለው በበጎ ተስፋና በጠንካራ የሥነ-ምግባር ምሰሶ ላይ ሲቆም ነው። የሀገር ፍቅር የሚገለጸው በቃል ብቻ ሳይሆን፣ በተግባርና በጋራ የልማት ተሳትፎ የህዝብን ህይወት በመለወጥ ጭምር ነው።

የገጣሚው ግጥሞች እንደሚያሳዩት፣ ትውልዱ የትኛውንም መሰናክል በጽናት እና በአብሮነት አሸንፎ መውጣት ይችላል። ከራስ ይልቅ ለሀገርና ለቀጠዩ ትውልድ በማሰብ የተሻለች ሀገርንና ነገን ማስረከብ ይቻላል። ለዚህም የዘመናችን አርበኝነት ለሀገር እና ለወገን መስራትና መስዋዕት መሆንን እንደሚጠይቅ በስንኞቹ ጠቅሷል፡፡

ሞፈሬን

ላውርድ

ቀንበሬን ልጥመድ፣ መሬት ልሰንጥቅ

ታርሶ መፍካት ነው

ወድቆ መብቀል ነው

የኑሯችን ስንቅ

የዘመኑ ትጥቅ

የገጣሚው ፍቃዱ አስራት እሳቤዎች እንደሚያሳዩት፣ ሀገርን ነጻ፣ ሉዓላዊ እና የማትደፈር ለማድረግ የፍቅር፣ የይቅርታ፣ የተስፋ እና መልካም ሰው የመሆን እሴቶች ወሳኝ ናቸው። ለአብነትም የዓድዋ ታሪካዊ ድል የእነዚህ ሁሉ ማህበራዊና ሞራላዊ እሴቶች ሕያው መገለጫ ሆኖ ጎልቶ ይታያል። ኢትዮጵያውያን በወቅቱ ልዩነቶቻቸውን ወደ ጎን በመተው በሀገር ፍቅር ስሜትና በአብሮነት በመቆም እና የጋራ ጠላትን በአንድነት በመመከት ሉዓላዊነታችንን ማስከበር ችለዋል፡፡

የዓድዋ ድል የጦር መሳሪያ ብልጫ ብቻ ሳይሆን፣ የህዝብ አብሮነት፣ የሞራል ልዕልና እና ለነጻነት የነበረው ጽኑ ተስፋ ውጤት ነው። ገጣሚው እንደሚጠቁመው፣ ሀገር የምታድገው፣ የምትጠበቀውና ሉዓላዊነቷ የሚከበረው ዜጎች በበጎ አመለካከት፣ በይቅርታና በጋራ ማንነት ሲተሳሰሩ ብቻ ነው። ይህ ታሪካዊ እውነት ትውልዱ የትኛውንም ፈተና በድል እንዲወጣ የሚያስችለው የዘላቂ ነጻነት እና የሉዓላዊነት ማረጋገጫ አርአያ ነው። በዓድዋም የነበረው ይህ ነው፡፡

ዓድዋ

የጠበቀ እምነት

ግዞትን መጸየፍ የተስፋዋ ዋርካዋ

ዓድዋ

ረቂቅ ደቂቅ ህዋ... በማለት ወጣቱ ደራሲ የጋራ ድል የሆነውን ዓድዋ ይገልጸዋል፡፡

በእርግጥም ወጣቶች በአንድ ሀገር የልማት፣ የኪነ ጥበብ፣ የሰላም፣ የአብሮነት እና እድገት ውስጥ ያላቸው ድርሻ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የዓለም የወጣቶች ቀንን አስመልክተው ባስተላለፉት መልእክት ኢትዮጵያን ከወጣቶቿ ነጥሎ ማየት አይቻልም ያሉትም በዚህ ምክንያት ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ "የህዝባችን የእድሜ ስብጥር እንደሚያመላክተው ወጣቶች ከፍተኛውን ቁጥር መያዛቸው፣ ብልጽግናን ለማረጋገጥና ለማፅናትም ታላቅ እድል ነው። የኢትዮጵያ ወጣት መልካም ዓላማን አንግቦ የሚንቀሳቀስ፣ የለውጥ ዋነኛ ሞተርና የሉዓላዊነታችን ጽኑ ማገር ነው፡፡ የኢትዮጵያ ወጣት የሀገሩን ታሪክ በአዲስ ብዕርና ብራና እየፃፈ ይገኛል። ሀገራችንን የኋሊት ጠፍንገው የያዟትን አጓጉል ልማዶች፣ አላስፈላጊ ንትርኮች፣ ጭቅጭቅ እና ግጭቶች በመራቅ የአሁን ወጣት በልማት ላይ አተኩሯል፣ ድህነትን ተጠይፏል" ሲሉ በማህበራዊ የትስስር ገጻቸው ላይ አስፍረዋል።

አክለውም "የመደመር መንግሥት የወጣቶችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነትና የአመራርነት ሚና ለማጠናከር በትኩረትና በቁርጠኝነት እየሰራ ይገኛል። ሀገራዊ ርዕያችንን ዕውን ለማድረግ ሁላችንም በንቃት እየተጋን፣ በፍቅር እንድንመላለስ ጥሪዬን አቀርባለሁ" ሲሉም አክለዋል።

## ቴክኖሎጂን... ከገጽ 16 የዞረ

"Eco Forest App" የተሰኘ መተግበሪያ በማበልጸግ በደን ልማት ስራዋ ላይ ትልቅ ለውጥ ማምጣቷን "New Improved Technology To Reduce Loss of Trees Planted In Rwanda" በሚል ርእስ እ.ኤ.አ. በ2024 በኬቲ ፕሬስ ላይ የታተመው ጹሁፍ ያስረዳል፡፡

ሩዋንዳ የደን ሀብቷን ካርታ ለማዘጋጀት እና የችግኝ ተከላ ስራዎቿን ውጤታማነት ለመለካት የጂአይኤስ (GIS) እና የሞባይል ቴክኖሎጂዎችን በስፋት ትተገብራለች። ይህም የደን ሽፋኗንና የችግኖችን የጽድቀት ምጣኔ ከፍ እንድታደርግ አግዟታል፡፡

በተመሳሳይ ቻይና በዓለም አቀፍ ደረጃ በቴክኖሎጂ የታገዘ የደን ማልማት ስራ እያከናወነች ያለች ሀገር ናት። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዛፎችን ለመትከል እና ለማልማት ድሮኖችን፣ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስን እና ግዙፍ የሳተላይት የክትትል ስርዓቶችን ትጠቀማለች። በተለይም በጎቢ በረሃ ዙሪያ የሚካሄደው ግዙፉ የአረንጓዴ ግንብ (Great Green Wall) ፕሮጀክት ሙሉ በሙሉ በዲጂታል ዳታ እና በቴክኖሎጂ እየተመራ ያለ ነው።

በአረንጓዴ መናፈሻ ውስጥ ያለች ሀገር በመባል የምትታወቀው ሲንጋፖርም የከተማ ደኖቿን እና ፓርኮቿን ለመንከባከብ ስማርት ግሪን ሃውሶችን፣ አውቶማቲክ የውሃ ስርዓቶችን እና የአፈር እርጥበት መለኪያ ቴክኖሎጂዎችን በስፋት ትጠቀማለች።

### ኢትዮጵያ በቴክኖሎጂው መንገድ

የኢትዮጵያ አረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ባለፉት ዓመታት ሚሊዮኖችን አስተባብሮ እጅግ በርካታ ችግኞችን በመትከል ሀገራዊ የደን ሽፋን እንዲጨምር ያስቻለ ግዙፍ እና ታሪካዊ ዘመቻ ነው።

ይህ ጥረት ሀገሪቱ ከአየር ንብረት ለውጥ የሚመጡ ተጽዕኖዎችን ለመቋቋም፣ የብዝሃ ሕይወት መጥፋትን ለመከላከል እና የአፈር መሸርሸርን ለመቀነስ ያደረገችው ቁልፍና ስልታዊ እርምጃ ነው። ይሁን እንጂ ይህን ያህል ግዙፍ የችግኝ ተከላ እና የልማት ስራ በዘላቂነት ለማስቀጠል በቴክኖሎጂ ማገዝ የግድ ሆኗል።

ኢትዮጵያ የተሻሉ የዘር ዝርያዎችን ለመምረጥ፣ የችግኝ ማፍያ ማዕከላትን በስማርት ሲስተሞች ለመቆጣጠር እና የውሃ አጠቃቀምን ለማቀላጠፍ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም ጀምራለች፡፡ በተጨማሪም ዘንድሮን ጨምሮ ባለፉት አመታት በተከላው ወቅት የጂፒኤስ (GPS) እና የሞባይል መተግበሪያዎችን በመጠቀም የተተከሉትን ችግኞች ብዛት፣ ዓይነት እና የተከላ ቦታዎች በዲጂታል ካርታ በትክክል መመዝገብ ተችሏል። ይህም የትኛው ዝርያ በየትኛው አካባቢ የተሻለ ውጤት እንዳመጣ ለመለካት እንዲሁም የሀገሪቱን የደን ሃብት በቴክኖሎጂ በታገዘ ስርዓት ለማስተዳደር ያግዛል፡፡

ለዚህም ኢትዮጵያ ዘንድሮ በአንድ ጀምበር ችግኞችን ስትተክል የሂደቱን ተዓማኒነት ለማረጋገጥ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች፣ የጂኦስፓሻል መረጃዎች እና ሳይንሳዊ የቁጥጥር ማዕቀፎች ስራ ላይ አውላለች፡፡ በዕለቱ የችግኝ ቆጠራ እና ማረጋገጥ ሂደቱ የተጀመረው ከ130 ሺህ ከሚልቁ የችግኝ ማፍያ ጣቢያዎች የሚወጡትን ችግኞች ሥርጭት በመመዝገብ ነበር፡፡ በየቀበሌው የሚገኙ የግብርና ባለሙያዎችም በሞባይል መተግበሪያዎች አማካኝነት የተተከሉትን ችግኞች ብዛት ወደ ማዕከላዊ የክትትል ማዕከል ሲያስገቡ ነበር። ወደ ማዕከሉ የገቡ መረጃዎችም ቀድሞ ከተለዩት የመትከያ ቦታዎች እና ችግኝ የማስተናገድ ዐቅማቸው ጋር ተመሳክረው ትክክለኛነታቸው የታወቀ ሲሆን፤ በዚህም 805 ነጥብ 3 ሚሊየን ችግኞች መተከላቸው በቴክኖሎጂ ተረጋግጧል፡፡

በተጨማሪም መትከል ብቻ ሳይሆን የተተከሉት ችግኞች እስከሚፀድቁ ክትትል የሚደረግ ሲሆን፤ እያንዳንዱ የመትከያ ቦታ በጂኦስፓሻል ቴክኖሎጂ ዲጂታላይዝ ተደርጎ ትክክለኛ የችግኝ መገኛ ጣቢያው፣ የችግኙ ዓይነት እና የተተከለበት ቀን በመረጃ ቋት ውስጥ እንዲመዘገብ ተደርጓል።

ከዚህ በተጨማሪ ችግኞቹ ከተተከሉ በኋላ በ30ኛው ቀን ከመሬቱ ጋር መዋሃዳቸውን፣ በ90ኛው ቀን ሥር መስደዳቸውን እና በ180ኛው ቀን የበጋውን ወራት የመቋቋም ዐቅማቸውን ለመገምገም ኦዲት እንደሚደረግ ተገልጿል፡፡

የችግኞቹ ማደግ እና የደን ሽፋኑ መጨመር በሳተላይት ምስሎች እና በእፅዋት አረንጓዴነት አመልካች ትንተናዎች አማካኝነት ይረጋገጣል። ይህ ሁሉ አጠቃላይ መረጃ ተጠናቅሮ በዓለም ባንክ የካርቦን ብድር ሥርዓት በኩል ገለልተኛ የሦስተኛ ወገን ማረጋገጫ እንዲያገኝ ይደረጋል ተብሏል፡፡

በዚህ የተቀናጀ እና ሣይንሳዊ አሠራር ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ የትኩረት ማዕከል የሆነውን የአረንጓዴ ልማት እና የአየር ንብረት ለውጥ መከላከል ሥራዋን በቁርጠኝነት እያረጋገጠች ትገኛለች።




ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው በእነ ጌጤነሽ ሽዋሰገድ (8 ሰዎች) ስም በልደታ ክ/ማ በቀድሞ ወረዳ 3 ቀበሌ 42 በአዲሱ ወረዳ 05፣ በካርታ ቁጥር ል.5/149/11864/00፣ ሴሪ ቁጥር 034913 የተመዘገበ ይዞታ ካርታ ጠፋብኝ ብለው በቀን 21/11/2018 ዓ.ም በማመልከቻ ጠይቀውናል፣ ስለዚህ የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳይ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጅናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ**
**ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች ሳምራዊት ፍቅሬ ታምሩ በቀን 21/11/2018 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 05 ክልል ውስጥ የሚገኝ የካርታ ቁጥር ለ/ኩራ5/46/1/58323/0143/6/00 የሴሪ ቁጥር 0255103 የቦታው ስፋት በሰነድ 72 ሜ.ካ የቦታው አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነው ኦሪጂናል ካርታ የጠፋብኝ በመሆኑ ይሄው ተገልፆ ለሚመለከተው አካል ምትክ እንዳገኝ ደብዳቤ ይጻፍልኝ በማለት በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታን ወይም ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤታችን እንዲያሳውቁን እያልን በጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኃላ ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ**
**መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

በራዕይ ቁ.2 የጋ/ህ/ሥ/ማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 13 ክልል ውስጥ የሚገኘው ይዞታ ካርታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር አቃ/ቃ/ክ/ከ/ሊዝ 0584 የሴሪ ቁጥር 191128 የይዞታ ስፋት 1135.68 ካ/ሜ የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ማስመዝገባቸውን ወማ/8/677349 በቀን 24/11/18 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ በተገለፀልን መሰረት ወጪውን በማህበሩ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅ እየገለጽን በማንኛውም ምክንያት የጠፋው ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ እስከ 30 ተከታታይ የስራ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ፅ/ቤት እንዲያቀርቡ በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ**
**መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

## ትደጌ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር
**የስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያ**

ትደጌ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሐምሌ 20 ቀን 2018 ዓ.ም በተለጠፈው ማስታወቂያ መሰረት ንጋት ብርሃን ሕንፃ ላይ በሚገኘው በማህበሩ ጽ/ቤት ነሃሴ 23 ቀን 2018 ዓ.ም ከቀኑ 8:30 ሰዓት በሚያደርገው ስብሰባ በሚከተሉት አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ለመወሰን ስለሚፈልግ ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ወይም ህጋዊ ውክልና ያላቸው የታደሰ መታወቂያ እና ህጋዊ ውክልና በመያዝ እንዲገኙ በድጋሚ በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ እናሳውቃለን፡፡

**<u>የስብሰባ አጀንዳዎች</u>**

1. የማህበሩ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ማቅረብ፤
2. በቀረበው ሪፖርት ላይ ተወያይቶ መወሰን፤
3. የቦርድ አባላት ማስመረጥ እና ስልጣንና ተግባር መወሰን፤
4. አክስዮን እንዲመነጭ ተወያይቶ ስለመወሰን ፤
5. ተጨማሪ መዋጮ በማዋጣት የማህበሩ ካፒታል ማሳደግ ላይ ተወያይቶ መወሰን፤
6. የማህበሩ መመስረቻ ፅሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ በአዲሱ የንግድ ህግ መሰረት እንዲሻሻል መወሰን እና ማሻሻል፤
7. ሌሎች በተጨማሪ የሚነሱ አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ መወሰን፤

**ማስታወቂያ፦ ተጨማሪ አጀንዳ ማስያዝ ከፈለጉ ስብሰባው ከመካሄዱ ከ5 ቀን በፊት በፅሁፍ ለጽ/ቤቱ ማቅረብ ይችላሉ።**

**ትደጌ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር**

**ጉዳዩ፡- የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ ይመለከታል**

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ወረዳ 09 በሀይሌ ሞላ ዘገየ ስም የተመዘገበ የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA00005090265900103041 እና የሴሪ ቁጥር C 0304573 የሆነ ካርታ መጥፋቱን ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑ የይዞታ ካርታ በጋዜጣ 30 ቀን ውስጥ መብት አለኝ የሚል እና ካርታው መጥፋቱን ከላይ የተጠቀሱት ግለሰቦች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬትና ምዝገባ መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ማስታወቂያ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን መጥፋቱን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲያሳውቅ እየገለጽን ይህ ባይሆን ለአመልካቹ አዲስ ካርታ ወጪ ተደርጎ የሚሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአደስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ እነ ቅድስት ታዬ ንጋቱ 4 ሰዎች አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 01 ካርታ ቁጥር AA000090102372 ቁጥር ይዞታ የሴሪ ቁጥሩ 090170 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይገፄዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

እነ አለዬ ንጉሴ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 ካርታ ቁጥር ቦሌ 7/11/5/4/4922/00 ሴሪ ቁጥር 027091 የሆነው ይዞታ የቤት ባለቤት ካርታ ስለጠፋባው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ ይገፄዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 13 የቤት ቁጥር ----- የይዞታ ካርታ ቁጥር 28433 የሆነው የሻለቃ ሞሲሳ ደሬሳ ሶንቶ ስም የተመዘገበው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 04/12/2018 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑ የይዞታ ካርታ ይገፄዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በ አበበች አልቤርቶ ሪሳቶ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው የጋራ መኖሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 10 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000061002244790211 ሴሪ ቁጥሩ C095572 የሆነው ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ የሚል ግለሰብ ይሁን ሌላ አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ በጽ/ቤታችን ቀርቦ ካላስረከበ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት /ካርታ/ ተዘጋጅቶ እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት መንገሻ ሳሙኤል ስም የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000080115418 የሴሪ ቁጥሩ 044144 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 01 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋ በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይገፄዋለሁ/ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ተለዋጭ ሰርተፊኬት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ በን/ስ/ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ተስፋዬ ክንፈ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 1 የቤት ቁጥር 095 ካርታ ቁጥር 1/8/33151/01 ተመዝግቦ የተሰጣቸው በማህደሩ ላይ ቀሪ ሆኖ መገኘት የነበረበት ካርታ የጠፋ በመሆኑ ይህንኑ አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም መቃወሚያ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ በ30 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ካርታው እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቶ አበበ ግዛው አርጋው ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ቦሌ10/105/7/4/4232/00 የሴሪ ቁጥር 025037 የቤቱ ስፋት በሰነድ 72 ሜ.ካ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በእኛ ተቋም ማህደራቸው ተመዝግቦ መገኘቱ ይታወቃል፡፡

ይሁንና በአቶ አበበ ግዛው አርጋው ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ቦሌ 10/105/7/4/4232/00 የሴሪ ቁጥር 025037 የቤቱ ስፋት በሰነድ 72 ሜ.ካ የሆነው ካርታ የጠፋ ስለሆነ ቤቱን በዕዳ ይገፄዋለሁ፤ አስይገፄዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ማህደሩን የምናደራጅ እና ሀላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው ዘሀራ ያሲን ሹሬ ስም የተመዘገበ ልዩ መለያ ቁጥሩ AA000080302161 ሴሪ ቁጥሩ L 0139475 የተሰጠበት ቀን 01/10/2015 ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ ታውጆ አገልግሎት እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም በጠየቁት መሰረት የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳዮች ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጂናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይዠዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካላቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 08 የቤት ቁጥር 9999/1 በወ/ሮ ዘምዘም አብደኑር መሀመድ ስም የተመዘገበው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ቁጥር አከ008/73/1/7930 የተሰጠበት ቀን 14/08/05 ሴሪ ቁጥር 010069 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 30/11/2018 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑ የይዞታ ካርታ ይገፄዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፤

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

አመልካች በአራዳ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 13 ቀበሌ 01 በአዲሱ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 9999 በየካቲት 12 ሆስፒታል ስም የወጣው ቁጥሩ አ/11/24/05/00/00 ሴሪ ቁጥር 006051 በቀን 08/08/02 ዓ.ም ወጪ የሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ዋና ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በምትኩ ካርታ ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው 03/02/2018 በተፃፈ ማመልከቻ በመጠየቃቸው ጋዜጣ ማሳወጅ አስፈልጓል፡፡

በመሆኑም የጠየቁትን አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሰው የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይገፄዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ይህ መስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ አራዳ ክ/ከ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ እንዲያቀርቡ እያሳወቅን ካላቀረቡ ግን የጠየቁትን አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአራዳ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች አቶ አለማየሁ በዳዳ አያኖ ስም የተመዘገበ ነዋሪነቴ በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ሲሆን የቤት ካርታ ስለጠፋብኝ ካርታ ቁጥር የካ/16995/13 በሴሪ ቁጥር 1548243 የሆነ ማረጋገጫ እንዲፃፍልኝ በማለት አቤቱታ አቅርበዋል ይዞታ ቤቱን በዕዳ ይገፄዋለሁ አስይገፄዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ሀላፊነት የምንወድስ ይሆናል፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው በፀሜክስ ግሎባል ኢንተርፕራይዝ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስም በልደታ ክ/ከተማ በወረዳ 08 በልዩ መለያ ቁጥር AA000080301751 ሴሪ ቁጥር L0229553 የተመዘገበ ይዞታ ካርታ ጠፋብኝ ብለው በቀን 30/11/2018 ዓ.ም በማመልከቻ ጠይቀውናል፤ ስለዚህ የምትክ ካርታ አገልግሎት ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሱት ካርታ ቁጥሮች እና በባለጉዳይ ስም የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ኦርጂናል ካርታም ሆነ ኮፒውን/ ይገፄዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ልደታ ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ መብት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካልቀረበ በመመሪያ ቁጥር 61/2010 አንቀጽ 72 ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ልደታ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በአስናቀች አበበ አዲሱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 ወረዳ ቦሌ4/34/1/6/96/2612/01 ሴሪ ቁጥር 0116540 የሆነው ይዞታ የቤት ባለቤት ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይገፄዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካላቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቀድሞ 20 ቀበሌ 52 በአዲሱ ወረዳ --- የቤት ቁጥር 432 በካርታ ቁጥር 18299/29036/01 በአቶ/ወ/ሮ/እነ ይዘንጋው መንግስቱ ስም ተመዝግቦ ተሰጥቶ የነበረ ካርታ የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም ምክንያት ይገፄዋለሁ የሚል አካል ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ በመቅረብ አቤቱታ እንዲያቀርብ፡ ፡ይገፄዋለሁ የሚል ከሌለ ተለዋጭ ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# ስፖርቱን ያነቃቃው አረንጓዴው ሽፋን





ፎቶ፦ ከገፀ ድር

ለተለያዩ ስፖርቶች ምቹ ሆነው ከተሰሩ እና ከተፈጥሮ ጋር ከተስማሙ የመዲናዋ ልማቶች መካከል ጥቂቶቹ

**በሳህሉ ብርሃኑ**

የዓለም አካባቢ ጥበቃ ድርጅት ይፋ ባደረገው መረጃ መሠረት በአረንጓዴ ቦታዎች እጦት ሳቢያ ከተሞች ብዙ ሺህ ሰዎች ህይወታቸውን ያጣሉ፡፡ በእነዚሁ ከተሞች በአረንጓዴ ስፍራዎች እጦት ምክንያት 25 በመቶ ሰዎች ከስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ውጪ እንደሆኑም መረጃው ይገልጻል፡፡ የድምጽ ብክለት፣ የትራፊክ መጨናነቅ፣ እልህ አስጨራሽ የአኗኗር ዘይቤዎች፣ ጥቅጥቅ ያሉ የህዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርትና መሰል ችግሮች በየእለቱ በከተሞች የሚኖሩ ሰዎች የሚጋፈጧቸው የዕለት ዕለት ችግሮች ናቸው። እነዚህ የአኗኗር ችግሮች ከአረንጓዴ ስፍራዎች እጥረት ጋር ሲደመር ጉዳዩን አሳሳቢ ያደርገዋል፡፡

ይህን ከላይ የተጠቀሰውን አሳሳቢ ችግር ለዓመታት ስትጋፈጥ የቆየችው አዲስ አበባም አረንጓዴ አሻራ በተሰኘ ሀሳብ አማካኝነት የአረንጓዴ ሽፋን በመጨመሩ ለስፖርታዊ እንቅስቃሴ የተመቸች ከተማ ሆናለች፡፡ አዲስ አበባን ውብ እና ምቹ ያደረጓት የአረንጓዴ አሻራ መርሀግብር ሰፋፊ አረንጓዴ ስፍራዎችንም ጭምር በመፍጠር ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ ለሚፈልጉ ዜጎችም ትልቅ ዕድል የፈጠረ ነው፡፡

ስፖርት እና ተፈጥሮ የማይነጣጠሉ የሕይወት ሐረጎች ናቸው። ስፖርተኛው በሜዳ ላይ ላብ ሲያፈስስ፣ የሚያስፈልገው መሠረታዊ ነገር ንጹሕ አክስጅን እና ምቹ የአየር ሁኔታ ነው። ዓለም አቀፍ የስፖርት ሕክምና ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፣ በአረንጓዴ ስፍራዎች እና ከብክለት ነጻ በሆነ አካባቢ ስፖርታዊ ልምምድ የሚያደርጉ ዜጎችና ስፖርተኞች የደም ዝውውራቸው የተሻለ፣ የልብ ምታቸው ጤናማ እና ከልምምድ በኋላ የማገገም ፍጥነታቸው ከፍተኛ ነው።

በቴክሳስ ዩንቨርሲቲ የስፖርት አስተዳደር ትምህርት ክፍል ረዳት ፕሮፌሰሩ ብራያን ፒ. ማኩሎው እንደሚያረጋግጡት፣ በተለይም በረጅም ርቀት ውድድሮች የሳንባ አቅም እና የኦክስጅን ሥርጭትና ለውጤታማነት ወሳኝ ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው። በተለይም አትሌቶች ጠንካራ ልምምድ በሚያደርጉበት ወቅት ከወትሮው በእጥፍ የሚጠጋ ኦክስጅን ወደ ሳንባቸው ያስገባሉ። አየር በካርቦን እና በጥቃቅን ብናኞች ከተበከለ ደግሞ የአትሌቶች የሳንባ አቅም ይዳከማል። አረንጓዴ አካባቢዎች የስታዲየሞችን እና የስፖርት ማዘውተሪያዎችን ውበት ከመጨመር ባሻገር፣ የተፈጥሮ ጥላ እና ቅዝቃዜ በመፍጠር ለስፖርተኞች ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ።

የቴክሳስ ዩንቨርሲቲ ምሁሯ ቲና ማሪ ዋሊሴክ በፈረንጆቹ 2010 “The Relationship between Levels of Greenery and Landscaping at Track and Field Sites” ጥናትም የሚነግረን ይህንኑ ነው፡፡ ከ200 በላይ አትሌቶችን አካቶ በተሰራው የጥናት ውጤት መሠረት ተክሎችና አረንጓዴ አካባቢዎች ላይ መሰልጠንና መወዳደር ጭንቀትን እንደሚቀንስ እና ውጤትን እንደሚያሻሽል ያስረዳል። እንደዚሁም አብዛኛዎቹ የአትሌቶች መጥፎ የአፈፃፀም ምልክቶች ዝቅተኛው አረንጓዴ ደረጃ ባለው ቦታ መሰልጠናቸውና መወዳደራቸው ስለመሆኑና ውጤታማዎቹ ደግሞ አረንጓዴያማ እና የተስተካከለ የአየር ንብረት ባለበት የትራክ እና የሜዳ ቦታ በመሰልጠናቸው ስለመሆኑ ያትታል፡፡

በመሆኑም አዲስ አበባም ለአረንጓዴ ልማት የሰጠችው ትኩረት እንዲሁ ችግኝ የመትከል ስራ ብቻ ሳይሆን፣ የሀገርን የወደፊት ዕድገት የመቅረጽ፣ የትውልድን ጤና የማረጋገጥ እና የስፖርቱን ዘርፍ በጠንካራ መሠረት ላይ የመገንባት ስትራቴጂያዊ እርምጃ መሆኑን ያሳያል። የENCYCLOPEDIA.COM ገጸ ድር “Environmental Conditions and Training” በሚል አሳብ ባሰፈረው ጽሁፍ እንደተገለጸው ሞቃታማ የአየር ጠባይ ከከፍተኛ እርጥበት ማጣት ጋር ተደምሮ አትሌቶች እየተጋፈጡት ያለው መጥፎ የአካባቢ ሁኔታ ስለመሆኑም በጽሁፉ ተካቷል፡፡

እነዚህ ስራዎች በመዲናዋ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ለሚያደርጉ ስፖርተኞች ምን አይነት ትርጉም እንዳለው ከፍተኛ ስፖርት ባለሙያው አቶ በኃይሉ በቀለ አስተያየት በመዲናዋ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ ብዙ ርቅት መጓዝ የግድ ነበር፡፡ እንደዚሁም ምቹ ባልሆኑ መንገዶች ላይ ለሊት ተነስተው ጭምር ይሰሩ ስለነበር አደጋ ይደርስባቸው እንደነበር ያነሳሉ፡፡ አሁን ግን በአዲስ አበባ ከተማዋ አብዛኛው አካባቢዎች ንጽህናቸውን የጠበቁ፣ የእግረኛና የተሽከርካሪ መንገድን የለዩና ለእረፍትም ጭምር ምቹ የሆኑ ናቸው ባይ ናቸው፡፡

አረንጓዴ አካባቢ ላይ ንጹህ አየር እያገኙ መሰልጠንና ውድድሮችን ማካሄድ ምን ያህል ውጤታማ እንደሚያደርግ ለመረዳት ደግሞ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ከዚህ ቀደም ያስመዘገቧቸውን ውጤቶች ወደኋላ መለስ ብለን በአስረጅነት እንጥቀስ፡፡ የመጀመሪያውን ኦሊምፒያዊ ድል ካስገኘው አበበ ቢቂላ፣ ምሩፅ ይፍጠር፣ ኃይሌ ገብረሥላሴ፣ ቀነኒሳ በቀለ እንዲሁም ደራርቱ ቱሉ፣ መሠረት ደፋር፣ ጥሩነሽ ዲባባ፣ እያለ ቀጥሎ በትውልድ ቅብብሎሽ ውጤት ሲመጣ የነበረው ኢትዮጵያ ያሏት ምቹ የአየር ንብረትና ምቹ አካባቢዎች አትሌቶቹ ብርቱ ጥረት ታክሎበት የመጡ ናቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ አትሌቶቹ በምቹ አረንጓዴ አካባቢዎች መሰልጠናቸውና መወዳደራቸው የነበረው ድርሻ ቀላል አልነበረም፡፡

“የአረንጓዴ አሻራ” መርሐ ግብርም ሆነ በመዲናዋ እየተከናወኑ ያሉ የኮሪደር ልማቶች የከተማ ገጽታን ከማሳመር ባለፈ ለስፖርት ዕድገት እያበረከቱት ያለው አስተዋጽኦ እጅግ የላቀ ነው። የተፈጥሮ ጸጋንና አረንጓዴ ልማትን ከዘመናዊ ስፖርታዊ መሠረተ ልማቶች ጋር ማቀናጀት፤ ትውልድን በጤናማ መንፈስ ለማነጽና መዲናዋን ተመራጭ የስፖርት ቱሪዝም ማዕከል ለማድረግ የሚያስችል ስትራቴጂያዊ እርምጃ ነው። በመሆኑም ዛሬ በባለቤትነት የምንተክላቸውና የምንንከባከባቸው አረንጓዴ አሻራዎች፤ ነገ ለሚያብቡት ታዳጊዎችና አትሌቶች ንጹሕ አየርን፣ ለስፖርታችን ዘላቂ ልማትን፣ ለመጪው ትውልድ ደግሞ ኩራት እና ሕያው ሀብትን የሚያስተላልፉ የድል ምዕራፎቻችን ናቸው።

“የልጅነት ጊዜያችንን ስናስታውስ ስፖርት መስሪያ ቦታዎችን ሜዳ ፍለጋ እንንከራተት ነበር፤ ዛሬ ግን ልጆቻችንን ይዘን የምንወጣባቸው ውብ ፓርኮችና ንጹህ የኮሪደር መንገዶች በደጃችን መገኘታቸው ስፖርትን የዕለት ተዕለት ሕይወታችን አካል አድርጎታል” ይላሉ በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ነዋሪ የሆኑት አቶ ናትናኤል ኃይሉ፡፡ በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው የግል ሥራ ባለቤት እና የሁለት ልጆች አባት የሆኑት አቶ ናትናኤል፣ በመዲናዋ እየተስፋፉ የመጡት ሰፊ የእግረኛ መንገዶች፣ የብስክሌት መተላለፊያዎች እና አረንጓዴ ፓርኮች ለአካላዊ ጤንነታቸው ብቻ ሳይሆን ከቤተሰብ ጋር ጥራቱን የጠበቀ ጊዜ ለማሳለፍ ትልቅ ዕድል እንደፈጠሩላቸው ይገልጻሉ።

ልክ እንደ አቶ ናትናኤል ሁሉ ከልጆቻቸው ጋር እየተዘዋወሩ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን ማዘውተራቸው የልጆቻቸውን አእምሮና አካል በንቃት ለማሳደግ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳበረከተላቸው የሚገልፁ ወላጆች በርካቶች ናቸው። ሰፊ የመኪና፣ የእግረኛ እና የብስክሌት መንገድ፣ የህዝብ መናፈሻዎች፣ አረንጓዴ ስፍራዎች፣ ፋውንቴይኖች፣ እነዚህ ስራዎች ታዲያ በመዲናዋ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ለሚፈልጉ ዜጎች ምቹ ድባብ እየፈጠሩ ነው የሚባለም ለዚሁ ነው፡፡

ዓለም አቀፍ እንግዶችን እና አትሌቶችን ይበልጥ የሚማርከው የከተሞች ጽዳት፣ የአየር ንጽሕና እና የአረንጓዴ ስፍራዎች መስፋፋት ነው። በሌላም በኩል ንጹሕና አረንጓዴ አካባቢ መኖሩ ኢትዮጵያ የዓለም አትሌቶች መጥተው የሚያሠለጥኑባት እና የሚወዳደሩባት የስፖርት ቱሪዝም ማዕከል እንድትሆን ዕድል ይፈጥራል። ኢትዮጵያ በአትሌቲክስ ያላትን ዓለም አቀፍ ገጽታ ለማስቀጠል እና ወደፊትም ትልልቅ ዓለም አቀፍ ውድድሮችን ለማስተናገድ በምታደርገው ጉዞ፣ የአረንጓዴ ልማት ምቹ፣ ንጹሕና አስተማማኝ አካባቢን ለመፍጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። ዛሬ የሚተከሉት ችግኞች ነገ ለሚያብቡት ስፖርተኞች ንጹሕ አየርን፣ ለስፖርት ደግሞ ዘላቂ ዕድገትን የሚያመጡ የአረንጓዴ አሻራዎች ናቸው።

ከዓመታት በፊት ከ3 በመቶ በታች የነበረው የከተማዋ አረንጓዴ ሽፋን ባለፉት ስምንት ዓመታት በተከናወነው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ከ23 በመቶ በላይ ማደጉ ለአካባቢ ጥበቃ በዘለለ ለከተማዋ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችም አዲስ ድል የፈጠረ ነው። የተሻሻለው የከተማዋ የአየር ንብረት እና በብዛት የተስፋፉት ፓርኮች፣ አረንጓዴ አካባቢዎች እና ክፍት የስፖርት ማዘውተሪያዎችን ምቹ አድርገውታል። ይህ የካርቦን ልቀት ቅነሳ እና የኦክስጂን መጠን መጨመር ሯጮች፣ ብስክሌተኞች እና የጤና ባለሙያዎች ከብክለት ነጻ በሆነ ንጹህ አየር ውስጥ ልምምድ እንዲያደርጉ ያስቻለ ሲሆን፣ ለወጣቶች ስፖርት እድገት እና ለህብረተሰቡ ጤናማ የአኗኗር ዘይቤ መሠረት በመሆን የከተማዋን የስፖርት መዳረሻነት ከፍ አድርጎታል።